አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3592 | ቅዳሜ መስከረም 16 ቀን 2019 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




## የፅናት ፍሬ

10



ፎቶ- ከገፀ ድር

በአዲስ አበባ የመስቀል ደመራ በዓል በመስቀል አደባባይ ሲከበር

## በሕብረ-ባሕል ያጌጠው በዓል

14



ፎቶ- ከገፀ ድር

የመስቀል ደመራ የኢትዮጵያውያን የጋራ ማንነት ከሚታይባቸው በዓላት መካከል አንዱ ነው

## አዲስ አበባ በስፓርት ቱሪዝም ምዕራፍ

24



ፎቶ- ከገፀ ድር

አዲስ አበባ ለስፖርታዊ ማዘውተሪያ ስፍራዎች ግንባታ ትኩረት ሰጥታ በመስራቷ የተለያዩ ስፖርታዊ ኩነቶችን የማዘጋጀት ዕድል አግኝታለች

# የቅጠል ተራ ፍካት

- የመኖሪያ መንደሩ ጎስቋላ አካባቢዎችን ወደ ውብ እና ምቹ ስፍራነት የመለወጥ ማሳያ መሁኑ ተመላክቷል

በስንታየሁ ምትኩ

በአዲስ አበባ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ፤ በንግድ ማዕከሏ መርካቶ የሚገኘውና በተለምዶ "ቅጠል ተራ" በመባል የሚታወቀው አካባቢ ያረጀና የተጎሳቆለ ገጽታ ይታይባቸው ከነበሩ አካባቢዎች አንዱ ነው፡፡ ስፍራው የተፋፈጉ፣ ከእንጨት፣ ከአፈርና ከቆርቆሮ የተገነቡ፣ በየስንጣቂው በፕላስቲክ የተወተፉ፣ በእድሜ ብዛት ቀለምና ግርማቸውን ያጡ፣ ጣሪያቸው ንፋስ እንዳይወስደው ከላይ ድንጋይ የተጫነባቸው ቤቶች የሞሉበት ሆኖ ቆይቷል፡፡

በተደጋጋሚ በሚከሰት የእሳት አደጋ ምክንያት ከከባድ የንብረት ውድመት ባሻገር የሰው ህይወት የሚያልፍበትም፣ የኤሌክትሪክ መስመሮቹ እንደ ሸረሪት ድር የተጠላለፉ ከመሆናቸውም ባሻገር ሻማ እና ኩራዝ ለመብራት አገልግሎት የሚውልበት አካባቢም ነበር፡፡ በቦታው የእሳት እና ሌላ ድንገተኛ አደጋ ቢያጋጥም የአምቡላንስ መኪና ይቅርና ለሰዎች እግር መንገድ እንኳን ማግኘት እጅግ አስቸጋሪ አድርጎት ቆይቷል፡፡

ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ፎቶ ከገጸ ድር

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በመርካቶ የበጎነት መንደር የተገነቡ ቤቶችን ለተጠቃሚዎች ሲያስተላልፉ

# የብርሃን ህብር በውቢቷ ከተማ



ፎቶ- ከፋይል

በመስቀል አደባባይ በድምቀት የተከበረው የ2018 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል በከፊል

በመለሰ ተሰጋ

ያለሁበት የመስቀል አደባባይ አንድ ስም፣ ብዙ ታሪክና ትዝታን ያዘለ ድንቅ ስፍራ ነው፡፡ እዚህ በኅብረ ቀለማት የደመቀ የከተማ ውበት እንደ ዐባይ ፏፏቴ ጅንን ብሎ፣ በብርሃን ጎርፍ አምሳል ይወርዳል፤ ይነጉዳል፡፡

በእርግጥ ቀኑ እየመሸ ነው፤ ግን ፀሐይ የጠለቀች አትመስልም፤ ይልቅ በጨረቃ ተከልላ ብርሃኗን በእርሷ በኩል እየፈነጠቀች በአዲስ አበባ ሰማይ ሥር አብራ ለማምሸት የፈለገች ይመስላል። እዚህ

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

# ያልተቋረጠው የጠላቶቻችን ሴራ እና የኢትዮጵያ የባህር በር እውነት

- ኢትዮጵያ በጠላቶች ሴራ የባሕር በር አልባ መሆኗ በንግድ፣ በደህንነት እና በሎጂስቲክስ ላይ ጉዳት እንዳደረሰባት ተገልጿል

በቶለሳ መብራቴ

የኢትዮጵያ የባሕር በር ታሪክ የሚጀምረው በጥንታዊው የአክሱም ሥልጣኔ ዘመን ሲሆን፣ ሀገሪቱ በወቅቱ ጥንታዊዋን የወደብ ከተማ አዱሊስን በመጠቀም በቀይ ባህር፣ በህንድ ውቅያኖስ፣ በሜዲተራኒያን እና በሩቅ ምስራቅ ሀገራት መካከል ይካሄድ የነበረውን የንግድና የዲፕሎማሲ መስመር በበላይነት ትመራ ነበር። አዱሊስ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ፣ የባህል እና የባህር ኃይል መነሻ በመሆን እንደ ሮም፣ ፐርሺያና ቻይና ካሉ የዘመኑ ታላላቅ የዓለም ኃይሎች ጋር እኩል እንድትሰለፍ አድርጓታል። ከአክሱም መንግሥት መውደቅ በኋላም ቢሆን

ወደ ገጽ 4 ዞሯል




አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## የባንዳዎች ስር ከታሪካዊ ጠላታችን የሚመዘዝ ነው!

ኢትዮጵያ የብዙ ዘመናት እድሜ ባለጸጋ፣ የሉዓላዊነት እና የነጻነት ተምሳሌት የሆነች ሀገር ናት። ይሁን እንጂ የዚህች ታላቅ ሀገር ረጅም ታሪክ ከውጭ ከሚመጡ ተፅዕኖዎች እና ከውስጥ ከሚፈጠሩ መሰናክሎች ጋር የተቆራኘ ነው። ዛሬም ቢሆን የሀገራችንን ሰላም እና ዕድገት ለማጨናገፍ የሚደረጉ ጥረቶች ከታሪካዊ ጠላቶች እና ከእነሱ ጋር ከወገኑ የውስጥ ባንዳዎች የሚመነጩ መሆናቸውን በአጽንኦት መገንዘብ ይገባል። ኢትዮጵያ እጅግ ሰፊ ለም መሬት፣ የውሃ ሃብት፣ ማዕድናት እና ብዝሃ ሕይወት ያላት ሀገር ናት። ሀገራችን በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ ከሚገኙ እምቅ አቅም ያላቸው ሀገራት ግንባር ቀደም ነች። ይሁን እንጂ፣ ይህ ትልቅ የተፈጥሮ እና የሰው ሀብት ባለጸጋነቷ ከሕዝቧ የኑሮ ደረጃ ጋር ያለመጣጣሙ ሀቅ ፍንትው ብሎ የሚታይ ነው። ኢትዮጵያ በሰላም እጦረት እና በውስጣዊ አለመረጋጋት ሳቢያ አቅሟን በሚገባት ልክ መጠቀም አልቻለችም።

ለኢትዮጵያ ሰላም ማጣት እና አለመረጋጋት በቋሚነት የሚሰራው ዋነኛው የውጭ አካል የግብፅ መንግስት መሆኑን ታሪካዊ እና ወቅታዊ መረጃዎች በግልጽ ያሳያሉ። የአባይ ወንዝ ፍሰትን በተመለከተ ካይሮ የምትከተለው ፖሊሲ የኢትዮጵያን የመልማት ሙብት ሙሉ በሙሉ ለመገደብ ያለመና በምቀኝነት ላይ የቆመ ነው። ይህች ሀገር በታሪክም ሆነ በዘመናችን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለመሸርሸር፣ የውስጥ ባንዳዎችን በመደገፍ እና የዲፕሎማሲ ጫናዎችን በመፍጠር ረገድ ግንባር ቀደም ሆና ቆይታለች። የካይሮ መንግስት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማዳከም ያልሞከረው መንገድ አለ ማለት አይቻልም። በቀጥታ ጦር ከማዝመት ጀምሮ የውስጥ ባንዳዎችን በመደገፍ ሀገራችንን እረፍት እስከመንሳት የዘለቁ እርምጃዎችን ሲወስድ ኖሯል፡፡

በኢትዮጵያ የብሔራዊ ጥቅም እንዳይሳካ ማድረግ የግብፅ ስልታዊ ስራ ሆኖ ቀጥሏል። የህዳሴ ግድብ ግንባታን ከመጀመሪያው አንስቶ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ እና በዲፕሎማሲ መስኮች ሁሉ ለማደናቀፍ የተደረጉት ጥረቶች የዚህ እውነት ማሳያዎች ናቸው። በምስራቅ አፍሪካ ቀንድ ሰላም እንዳይሰፍን እና ሉዓላዊነታችንን ተጠቅመን እንዳንለማ የሚደረገው ዘመቻ ሁሉ ከዚህ ታሪካዊ ጠላት ጸረ-ኢትዮጵያ አቋም የሚመነጭ ነው። ለዚህ ደግሞ ያለግጭት መኖር የማይችለውን የኤርትራ መንግስት በመሳሪያነት ይጠቀማል፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚንቀሳቀሱ ባንዳዎች የጥፋት ስራቸው ሲመዘዝ ከውጭ ጠላቶች ጋር በጥልቀት የተሳሰረ ነው። እነዚህ የውጭ ተላላኪዎች ከጠባብ የጥቅመኝነት አስተሳሰብና ተግባር ውጭ ለሀገር የሚቆረቆሩበት አንዳችም እንጥፍጣፊ ሞራል የላቸውም። ይህ የባንዳዎች መረብ ከአስመራ እስከ ካይሮ ባሉት ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች የሚመራ እና የሚደገፍ መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው።

ከጉያዋ ወጥተው የውጭ ኃይሎች ተላላኪ የሆኑት ባንዳዎች አቅማቸው ከመፍጨርጨር አልፎ አያቅም። ኢትዮጵያ በታሪኳ ስንትና ስንት የውጭ ወረራዎችን እና የውስጥ ከዳተኞችን ድል አድርጋ ያለፈች ሀገር ናት። እነዚህ የውጭ ርዝራዦች የሚፈጥሩት ጊዜያዊ ሁከት የሕዝባችንን የጸና አንድነት ሊያናውጠው አቅም የለውም። የኢትዮጵያ ኃይል የሚመነጨው ከሕዝቧ ጥንካሬ እና ከታሪካዊ ጽናቷ እንጂ ከከዳተኞች ሴራ አይደለም። ይህንን መሰረታዊ እና ቁልፍ ነጥብ በጥልቀት መረዳት መፍትሔው ላይ ለመድረስ እና በጋራ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ለመቆም ወሳኝ ጉዳይ ነው። ግብፅ ለብሔራዊ ጥቅማችንና ሰላማችን ታሪካዊ ጠላት መሆኗን ከመሸኮርመም ወጥተን በግልጽ መገንዘብ ይገባናል። ኢትዮጵያውያን በጋራ አቋም ብሔራዊ ጥቅማችንን ላለማስደፈር ወቅቱ የሚጠይቀውን የሀገርን ሰላምና አንድነት የማስጠበቅ የአርበኝነት ተግባራችን በተግባር ማሳየት ይገባናል!

# የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

## ዓለም ሀብቱን ምን ያህል እንዲያውቀው አድርገነዋል?

**በሰናይ ምግባሩ**

የኢትዮጵያን ብዝሃነት ከሚያሳዩት መካከል ሀይማኖታዊ በዓላት ይጠቀሳሉ፡፡ ለዚህ ማሳያው በዛሬው ዕለት እየተከበረ ያለው የመስቀል ደመራ በዓል ነው፡፡ በዕለቱ የሚከናወኑ ሁነቶች ደስታን የሚፈጥሩ፣ አይረሴነትንም የሚጭሩ ናቸው፡፡

በውስጡ አንድነትን፣ አብሮነትን፣ ተስፋን ጨምሮ በጎ እሴቶችን ይዟል፡፡ የሀይማኖቱ አስተምህሮ እንደሚያሳየው፣ መስቀሉን ፈልጎ ለማግኘት የተሄደበት ርቀት ጽናት ከለፉና ከጣሩ ጊዜ ሊወስድ ይችላል እንጅ ማሳካት ይቻላል የሚል መልዕክትም የሚያስተላልፍ ነው፡፡

እነዚህንና መሰል ነገሮችን ከግምት በማስገባት መስቀል ደመራ በዩኔስኮ በማይዳሰስ ቅርስነት መመዝገቡ ይታወቃል፡፡ በቅርስነት ተመዘገበ ማለት ሀብትነቱ የዓለምም ጭምር ነው እንደማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ ትልቁ ቁም ነገር በዚህ ልክ የሚገለጸው ይኸን በዓል “የጋን ውስጥ መብራት” መሆን የለበትም፡፡ በየትኛውም የዓለም ክፍል ያለ በልኩ እንዲያውቀው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ልክ የቤት ስራ ወስዶ ከመስራት አንጻር አሁንም ውስንነቶች አሉ ብል ማጋነን አይሆንም፡፡ ይህ ሲባል ግን አንድን ወገን (መንግስትን) ብቻ መውቀስ ተገቢ ነው ማለት አይደለም።

ሁሉም የየድርሻውን በመውሰድ ሚናውን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

መንግስት እና ሌሎች የበዓሉ አጋፋሪዎች በየዓመቱ መስከረም 16 የሚከበረውን የመስቀል ደመራ በዓል በደመቀ እና ባማረ ሁኔታ እንዲከበር እና ዝግጅቱንም ለዓለም ማህበረሰብ በሚደርስ መንገድ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በመዲናችን አዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ላይ የሚከበረው ይኸው በዓል ምቹ መሰረተ ልማት እንዲኖረው የተሄደበት ርቀት ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ ነገር ግን በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎችም በዚህ ልክ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር አሁንም ቀላል የማይባል የቤት ስራዎች እንዳሉ ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዓላቸውን ለማክበር ከተለያዩ የዓለም አካባቢዎች የሚመጡ እንግዶችን ሲመለሱ ለሌሎች የማስተዋወቅ ስራ እንዲሰሩ በሚያስችል መልኩ በአግባቡ ተቀብሎ በጥሩ ስሜት ተመልሰው እንዲሄዱ የማድረግ የኢትዮጵያውያን የእንግዳ ተቀባይነት ባህል በተግባር ማሳየት ይጠበቅብናል፡፡ ይህ ሲሆን ራሳቸው ለሌሎች ሀገራት ዜጎች የማስተዋወቅ ስራውን በመስራት ትልቅ አጋዥ ይሆናሉ፡፡

ከዚህ ውጭ መንግስት ይህን ቅርስ ለማስተዋወቅ ከሚሄድበት ርቀት በላይ እኛም የማህበራዊ ሚዲያው የሰጠንን ዕድል በመጠቀም በተለያዩ የውጭ ቋንቋዎች ጭምር ተገቢውን ግንዛቤ መፍጠር ይጠበቅብናል፡፡

በተለያዩ ሀገራት የምንኖር ኢትዮጵያውያንም በዚህ መልኩ አይተኬ ሚናችሁን መጫወት ይጠበቅባችኋል ብዬ አስባለሁ፡፡ እናንተስ ምን ትላላችሁ? ሀሳባችሁን ለሌሎች አጋሩ እያልኩ መልካም በዓል ተመኘሁ፡፡

ADDIS MEDIA NETWORK
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

**እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
እዮብ ተፈራ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ጓዴ
ለይላ መሀመድ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሽዋርካብሽ ቦጋለ
አብርሃም ገብሬ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ
ቶሌሳ መብራቴ

## የብርሃን... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ- ከፋይል

በመስቀል አደባባይ በድምቀት የተከበረው የ2018 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል በከፊል

መስቀል አደባባይ፣ በተናጠል የነበሩ ብዙ ነጠላ እንጨቶች ቀስ በቀስ ችቦ ይሆናሉ፤ ብዙ ችቦዎች ደግሞ ትልቅ ደመራን ይፈጥራሉ፤ ደመራው ሲለኮስ ቀይ፣ ብርቱካንማ፣ ቢጫና ሰማያዊ የእሳት ቀለማት ዙሪያ ገባውን ካሉ መብራቶች ጋር ተስማምተው አካባቢውን የብርሃን ባሕር ያስመስሉታል፡፡ ነጫጭ የለበሱ ኢትዮጵያውያን ደግሞ በረድፍ ተሰልፈው የልብን ስብራት በሚጠግን ያሬዳዊ ዜማ ስፍራውን ገነት ያስመስሉታል፡፡

ነፍስና ሥጋን የሚያስታርቀው ይህ የደመራ ብርሃን ከከተማዋ አስደማሚ ለውጥ ጋር ተወዳጅቶ የሌሊቱን ጨለማ እንደ ጉም አብንኖ፣ እንደ ውኃ አትንኖ እንደ መስከረም ሰማይ ጥርት ሲያደርገው እንደ እኔ በተመስጦ ከተመለከቱ አዲስ አበባ፣ ልክ እንደ ማለዳ ጀንበር አሊያም እንደ መስከረም ፈክታ ትታያለች፡፡

አዎ፣ መስከረም በውብ አበቦች፣ በጠሩ ወንዞች፣ በደመቁ አዕዋፍ፣ አረንጓዴን በተጎናፀፉ ተራሮች፣ ተስፋን በለበሱ ሰዎች እና እንደ ደመራ በመሳሰሉ ተናፋቂ የአደባባይ በዓላት የታጀበ ነው፤ መስከረም! የሀገሬ ሰው ከ13ቱ ወራት አብልጦ ለመስከረም ልዩ ፍቅር አለው፡፡ ለዚህ ሳይሆን አይቀርም ከምርጦቹ ወራት መርጦ የልጆቹን ስም "መስከረም" ብሎ የሚሰይመው፡፡ ታዲያ መስከረምና አዲስ አበባ፣ በተለይም አዲስ አበባና የመስቀል ደመራ ሲገናኙ ልብ እንደ ባሕር ሰፍቶ ምድር በደስታ ትጠባለች። ባለቅኔው ገጣሚ አያ ሙሌ "ደስ ይላል መስከረም" በተሰኘ ግሩም ሥራው...

ቡቃያው ጣል ከንበል ሲል፣

ሽሩባዋ ወርዶ እንዲያ ሲዘናፈል፤

ልቤ እንደ በቆሎ ያድራል ሲፈለፈል፣

በቀጭን ተሰርታ ስትል ዘንከት ዘንከት፣

ጃሎ ሲል ሊያነጋ አገር በመለከት፤

ለመስቀል ጠንስሶ፣

በማድጋ ገንቦ ለእንግዳ ቀንሶ፤

በሞቴ አፈር ስሆን እያለ ሲያጋፍር፣

ጥርስ እንጎቻ አስፍቶ አሞጭ በመሰለው እርጎ ፍርፍር...

እንደ ቢራቢሮ አበባ ለአበባ ዐደይ እንቡር እንቡር

በፍቅር ለመከረም ደስ ይላል መስከረም! እንዳለው፣ አዲስ አበባም በመስከረም የብርሃን ሸማን ተጎናጽፋ ቀን እንደ ፀሐይ ሌት እንደ ጨረቃ ትደምቃለች፡፡ ደግሞም ወዶ ተዋሕዶ፣ ያንጀት ተፈቃቅዶ፣ አንድ ልብ አቅዶ፣ አንድ ላይ ለመከረም ደስ ይላል መስከረም፤ እንዲል፡፡

ደመራ፣ በጨለማ መካከል ብርሃንን የሚያስታወሰን ድንቅ በዓል ነው። የደመራው ብርሃን ከሚነድ እንጨት የሚወጣ ብቻ አይደለም፤ በተስፋ፣ በእምነትና በመተሳሰብ የተቀመመ የሥጋና የነፍስ ጣፋጭ ምግብ እንጂ፡፡

ወዲህ ደግሞ ብርሃን የአንድ ከተማ ልብስ መሆኑን የሚያስረግጥ የምሁራን እሳቤም አለ፡፡ ለዚህ ሀሳብ በዌስት ሚኒስተር ዩኒቨርሲቲ የከተማ ዲዛይን ፕሮፌሰር ማሪዮን ሮበርትስ እና በዚሁ ተቋም ውስጥ በከተማ ልማት እና እድሳት ዘርፍ ከፍተኛ ተመራማሪ አዳም ኤልድሪጅ (ዶ/ር) "Planning the Night-time City" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በ2009 ለህትመት ያበቁትን የምርምር መጽሐፋቸውን ዋቢ እናድርግ፡፡

በዚህ መጽሐፍ በግልጽ እንደሰፈረው ዘመኑን የዋጁ ውብ የሕዝብ ቦታዎች፣ የደመቁ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች እና ተመልካችን ሳይቀር የሚማርኩ የማኅበራዊ ሕይወት ተግባራት የአንድን የከተማ ሌሊት እንደ ጨረቃ ያደምቁታል።

በምሽት ወቅት፣ ብርሃን በራሱ የከተማዋ ሥነ ሕንፃ አካል ይሆናል። ሕንፃዎች የሚታዩ ምልክቶች ይሆናሉ፤ የመንገድ መብራት ምሰሶዎች የእንቅስቃሴ መስመሮችን ይወስናሉ፤ አደባባዮች ለሕዝባዊ ሕይወት መድረክ ይሆናሉ፤ ድልድዮች እና ወንዞች በብርሃን የታጀቡ የከተማ ገጽታዎች መሆናቸውን ይመሰክራሉ፤ ወዲያ ወዲህ ከሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች የሚወጡ ብርሃናት ደግሞ እንደ እንቁ ጌጥ ልብን በሐሴት ያረሰርሳሉ፤ የከተማዋንም ፈገግታ ያደምቃሉ፡፡

በእርግጥም ዓለም አዲስ አበባን ጨምሮ ብዙ እና ውብ የምሽት ከተሞችን ታድላለች። ኒው ዮርክ ከሰማይ ላይ ስትታይ በሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎቿ እና በመንገዶቿ ላይ በሚፈስሰው ብርሃን በጠቢባን ቡርሽ የተኳለች የከተማ ሥዕልን ትመስላለች። ፓሪስ ደግሞ በታሪካዊ ሕንፃዎቿ፣ በመንገዶቿና በወንዞቿ ዙሪያ በሚዘረጋው የምሽት ብርሃን የፍቅር

> "እንጨት ከእንጨት ሲደመር ችቦ፣ ችቦ ከችቦ አብሮ ሲቆም ደመራ ይሆናል፤ ልክ እንዲሁ የፒያሳው ብርሃን ከሜክሲኮ፣ የሜክሲኮው ከመስቀል አደባባዩ... የአንዱ ብርሃን ከሌላው ሲደመር አዲስ አበባ ልክ እንደ ደመራው ምሽቱን ትፈካለች"

ከተማነቷን ትገልጣለች።

ዱባይም በሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎቿና በዘመናዊ የብርሃን ማስዋብ ሥራዎቿ ሌሊትን እንደ ቀን ማብራት የቻለች ከተማ ሆና ትታያለች። ቶኪዮም በብርሃን ጎርፍ ተጥለቅልቃ ታነጋለች፡፡ ታዲያ እነዚህ ከተሞች አንድ የሚያገናኛቸው ነገር አላቸው፤ ይሄውም ጨለማን በብርሃን አሸንፈው ሌሊት ከጨረቃ ጋር እኩል መድመቃቸው ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ ታዋቂው የንግድ አውሮፕላን አብራሪና ደራሲ ማርክ ቫንሆናከር በምሽት በረራዎቹ ወቅት የዓለማችን ዋና ዋና ከተሞች ድባብ ምን እንደሚመስል ለመግለጽ እ.ኤ.አ በ2022 "Imagine a City" በሚል ርዕስ ያሳተመውን መጽሐፍ መመልከት በቂ ነው፡፡

አዲስ አበባ ግን ቀደም ባሉት ዓመታት ምሽቱን በአየር ላይ ሆኖ ለሚመለከታት ብሩህ ከሆነው ታሪኳና ክብሯ ባሻገር በቦሌና በአንዳንድ አካባቢዎች ያለው ድምቀት እንደተጠበቀ ሆኖ አልፎ አልፎ ብልጭ ብልጭ ከሚሉ መብራቶች ባለፈ ጨለምለም ያለች እንደነበረች ብዙዎች ይመሰክራሉ፡፡

በእርግጥ አዲስ አበባ የቅኝ ግዛትን ጨለማ ታሪክ ያደረጉ የዓድዋ ድል ጀግኖች እናት መሆኗ አይዘነጋም፡፡ ለዚህ ደግሞ እ.ኤ.አ በ1994 "Long Walk to Freedom" በሚል ርዕስ ከታተመው የደቡብ አፍሪካዊው የነፃነት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላ መጽሐፍ ውስጥ አንድ ታሪክን እንምዘዝ፡፡ እ.ኤ.አ በ1962 ማንዴላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ፣ ፈረንሳይን፣ እንግሊዝንና አሜሪካንን ከመጎብኘት ይልቅ ኢትዮጵያን ማየት እንደሚያጓጓቸው በመጽሐፋቸው ላይ ሰፍሯል፡፡

የነፃነት ታጋዩ ኔልሰን ማንዴላ፣ ያኔ ከአውሮፕላኑ ጋር ከመሬት ከፍ ሲሉ የኢትዮጵያ ደኖችና ተራሮች እየተመለከቱ የጣሊያንን ወረራ ለመቋቋም የተዋጉ እነዚያን ጀግኖች ያስቡ ነበር። በዚህ የታሪክ ሀቅ ውስጥ በወቅቱ በከተማዋ ከነበረው ጨለማ ባሻገር ዘመን የማይጋርደው ዓለምን በብርሃን ያጥለቀለቀ የማይጠፋ የታሪክ ችቦ እንዳለ እንረዳለን፡፡ አሁን ደግሞ ከተማዋ በልማት ብርሃን ደምቃ ስትታይ ከገዘፈው ታሪኳ ጋር ሲደመር ወተት በመሰለ ጥርስ ላይ ፈገግታን እንደ መጨመር ነው፡፡

ይህ ትዕይንት በመስቀል ደመራ ወቅት ሲሆን ደግሞ ከልብ አንጠልጣይ መጽሐፍ ውስጥ አዲስና ውብ ገጽን እንደ መግለጥ ነው፡፡ ደማሙ ብዕረኛ ሠዓሊና ገጣሚ ገብረክርስቶስ ደስታ፡-

ዐደይ አበባ ነህ የመስቀል ደመራ፣

ጠረንህ አልባብ ነው አየርህ የጠራ።

የአገር ልብስ አንተ ነህ ነጭ እንደ በረዶ፣

ሰው የሚያጌጥብህ ጥበብህን ወስዶ።

አንተ ነህ መስከረም፣

ዘመን የምታድስ አስጊጠህ በቀለም፤ እንዳለው፣ አዲስ አበባም ዛሬ ከደመራው ብርሃን ጋር የበለጠ ተውባ ትታያለች፡፡ አዎ፣ እንጨት ከእንጨት ሲደመር ችቦ፣ ችቦ ከችቦ አብሮ ሲቆም ደመራ ይሆናል፡፡

ልክ እንዲሁ የፒያሳው ብርሃን ከሜክሲኮ፣ የሜክሲኮው ከመስቀል አደባባዩ፣ የሾሮ ሜዳው ከስድስት ኪሎ፣ የስድስት ኪሎው ከአራት ኪሎ፣ የአራት ኪሎው ከካዛንቺሱ፣ የመገናኛው ከሲኤምሲው...እንዲህ እንዲህ እያለ የአንዱ ብርሃን ከሌላው ሲደመር አዲስ አበባ ልክ እንደ ደመራው ምሽቱን ትፈካለች፤ ትደምቃለች፤ ትዋባለች፤ ታጌጣለች፡፡

# የባሕር... ከገጽ 1 የዞረ

በዛጉዌና በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ዘመናት ኢትዮጵያ እስከ ምፅዋና ዘይላ ወደቦች ድረስ ያለውን የባሕር በር ግዛቷንና የባሕር ወሰኗን አስከብራ ትኖር እንደነበር የታሪክ ድርሳናት በግልጽ ያረጋግጣሉ።

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ አውሮፓውያን አፍሪካን እንደ ቅርጫ ለመቀራመት ባደረጉት እንቅስቃሴ፣ የቅኝ ግዛት ኃይሎች የኢትዮጵያን የባሕር በር ተፈጥሮአዊ ትስስር ለመቁረጥና ሀገሪቱን ከዓለም አቀፍ የንግድ መስመር ለማግለል የተለያዩ ስትራቴጂካዊ ሴራዎችን ጠነሰሱ። በዚህም መሠረት ጣሊያን፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ የቀይ ባሕርንና የኤደን ባሕረ-ሰላጤን የባሕር ዳርቻዎች በመቆጣጠር ኢትዮጵያ ወደ ባሕር እንዳትጠጋ ያገለለ ከበባ እንዳደረጉባት ታሪካዊ ድርሳናት ዋቢ ይሆናሉ። በተለይም ጣሊያን የባሕር ዳርቻውን ግዛት ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥራ "ኤርትራ" ብላ በመሰየም ኢትዮጵያን ከባሕር በር ለመቁረጥ ያደረገችው ጥረት የሀገሪቱን የታሪክ ጉዞ እጥፋት ያስከተለ ትልቅ ማነቆ ሆኖ አልፏል።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማጠቃለያ በኋላ ኢትዮጵያ ያጣችውን ታሪካዊ የባሕር በር መብት ለማስከበር ባደረገችው ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ጥረት፣ በ1940ዎቹ እና 1950ዎቹ በዓለም አቀፍ ውሳኔ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በኮንፌደሬሽንና በኋላም በመዋሃድ የወደብ ባለቤትነቷን መልሳ አረጋግጣ ነበር። በእነዚያ ዘመናት ምፅዋና አሰብ የኢትዮጵያ ዋና ዋና የንግድና የባሕር ኃይል ማዕከላት ሆነው በማገልገላቸው ሀገሪቱ ከአፍሪካ ቀዳሚ ከሆኑት ዘመናዊ የባሕር መርከብ ድርጅቶችና የባሕር ኃይል አንዱን ለመገንባት በቅታ ነበር። ሆኖም በ20ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ በነበሩት የውስጥ ፖለቲካዊ ግጭቶች፣ የስርዓት መለወጦችና ጂኦ-ፖለቲካዊ ውጣ ውረዶች ምክንያት እ.ኤ.አ. በ1993 ኤርትራ ስትገነጠል ኢትዮጵያ ዳግመኛ የባሕር በር አልባ እንድትሆን ተደረገ፤ ይህም ሀገሪቱን በዓለም ላይ በሕዝብ ብዛት የመጀመሪያዋ የባሕር በር አልባ ሀገር ያደረጋት የታሪካዊ ጠላት ሴራ ውጤት ሆኖ በታሪክ መዝገብ ላይ ሰፍሯል።

በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪው አቶ ቴዎድሮስ ረታ እንዳስረዱት፣ የኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤትነት ጥያቄ የጊዜያዊ ፖለቲካዊ ፍላጎት ውጤት ሳይሆን የሀገሪቱን ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ጂኦ-ፖለቲካዊ ህልውና የሚወሰን መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ በቀይ ባሕርና በህንድ ውቅያኖስ ስትራቴጂካዊ ቀጠና አቅራቢያ የምትገኝ የታሪክና የስልጣኔ ባለቤት ሀገር ሆና ሳለች፣ በታሪክ አጋጣሚዎችና በታሪካዊ ጠላቶች ሴራዎች ምክንያት የባሕር በር አልባ ሆና ለሶስት አስርት ዓመታት መቆየቷ በንግድ፣ በደህንነት፣




ፎቶ- ከገፀ ድር

ኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤትነቷን መልሳ ለማረጋገጥ እያደረገች ያለው ጥረት ውጤት እንዲያፈራ ሁሉም የበኩሉን ድርሻ መወጣት አለበት

በሎጂስቲክስ እንዲሁም በቀጣናዊ ተፅዕኖ ፈጣሪነቷ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶባታል።

የባሕር በር ማጣት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚና ደህንነት ላይ ያሳደረው ጉዳት እጅግ ግዙፍ ሲሆን፣ ሀገሪቱ በየዓመቱ ለወደብ አገልግሎትና ለሎጂስቲክስ ክፍያ የምታወጣው በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ለአገር ውስጥ ልማት፣ ለትምህርት፣ ለጤናና ለተለያዩ መሠረተ-ልማቶች ሊውል የሚችል ሀብት ነው። የወደብ ኪራይ ወጪ በየጊዜው መጨመር በምግብ፣ በኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎች እና በመሰረታዊ ሸቀጦች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ንረት የሚያስከትል በመሆኑ፣ እንዲሁም በቀይ ባሕርና በኤደን ባህረ-ሰላጤ አካባቢ የሚካሄደው ዓለም አቀፍ ንግድና የጂኦ-ፖለቲካዊ ውድድር በሀገራችን ደህንነት ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ስላለው፣ የባሕር በር ጥያቄ የቅንጦት ወይም የታሪክ ቁስል ማስታወሻ ሳይሆን የኢትዮጵያ የብልጽግናና የህልውና ጥያቄ መሆኑን አቶ ቴዎድሮስ አብራርተዋል።

የኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርሲቲ የዓለም አቀፍ አጋርነትና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዝዳንት ሙለታ ሁሴን በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ከዕለት ተዕለት የፖለቲካ ክርክር የላቀ ከዘመናት የዘለቀ የታሪክ፣ የደህንነት፣ የኢኮኖሚና የጂኦ-ፖለቲካ ጉዳይ መሆኑን አመላክተዋል። የዓለም ንግድ፣ የኃይል መስመሮችና የወታደራዊ ስትራቴጂዎች የሚገናኙበት የቀይ ባሕርና የባብ ኤል-መንደብ ቀጠና ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ደህንነትና ለንግድ መስመሮች መረጋጋት ወሳኝ እንደሆነ ያብራሩት አቶ ሙለታ፤ ዓድዋ የሀገር ሉዓላዊነት ምልክት፣ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ደግሞ የልማትና የኢኮኖሚ ራስን መቻል ምልክት ከሆነ፣ የባሕር በር ጉዳይ ደግሞ የኢኮኖሚና ጂኦ-ግራፊያዊ ራስን መቻል ፕሮጀክት መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ወደ ባሕር በር እንዳትጠጋ በታሪክ አጋጣሚዎች የተለያዩ እንቅፋቶች ሲደቀኑባት መቆየታቸውን የሚያስታውሱት አቶ ቴዎድሮስ፣ አሁንም ቢሆን የውጭ ኃይሎች የውስጥ መከፋፈሎችን፣ የብሔርና የኃይማኖት ጉዳዮችን እንዲሁም ያልተጣሩ አሳሳች መረጃዎችንና አሉባልታዎችን በመጠቀም ሀገሪቱ ዓላማዋን እንዳታሳካ የሚደረጉ ጥረቶች እንዳሉ ይጠቁማሉ።

የሰላምና ደህንነት ምሁር ሙሉጌታ አየለ (ዶ/ር) እና የማህበራዊ ልማት አጥኚ አቶ ለሚ ስሜ ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋር ባደረጉት ቆይታ ይህንኑ ሃሳብ የሚያጠናክር ማብራሪያ ሰጥተዋል። ሙሉጌታ አየለ (ዶ/ር) እንዳስረዱት፣ የኢትዮጵያን ሀገራዊ እድገት፣ የዲፕሎማሲ ተሰሚነትና የልማት ስራዎች ለማስተጓጎል በግብጽና በኤርትራ አስተባባሪነት የሚካሄደው ሴራና የውስጥ ወኪሎችን በመጠቀም የሚያደርጉት የተቀናጀ እንቅስቃሴ፣ በየዘመኑ የሚነሱ የደከመችና የተንሳቆለች ኢትዮጵያን ለመፍጠር የሚሸርቡት ሴራ ማሳያ ነው።

እንደ ሙሉጌታ (ዶ/ር) ገለጻ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከሰቱ አብዛኛው ግጭቶችና አለመግባባቶች የድንበር ወይም የሌላ ጉዳይ ሳይሆን ኢትዮጵያ በሰላም እንዳትቀጥል የሚሹ ታሪካዊ ጠላቶች በሚሰጡት አጀንዳ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከብዙ አገራት ጋር ጦርነት ገጥማ ታውቃለች፤ ነገር ግን አንዳቸውም አሸንፏት አያውቁም፡፡

አቶ ለሚ ስሜ በበኩላቸው፣ የኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠል በዋናነት የግብጽ እጅ ያለበት ሲሆን፣ አገር ሆና ከተመሰረተችም በኋላ በሀገሪቱ ውስጥ ምንም አይነት ምርጫና ተቋማዊ አወቃቀር ሳይኖረው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረጉ የልማት እንቅስቃሴዎችን በስጋትና በምቀኝነት በመመልከት የጥፋት ኃይሎችን ሲደግፍ መቆየቱን ጠቅሰዋል።

በሌላ በኩል፣ ግብፅ በምስራቅ አፍሪካና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የታጠቁ ቡድኖችን በማደራጀትና በገንዘብ በመደገፍ የራሷን የጥፋት አጀንዳ ስታስፈጽም መቆየቷን የጠቀሱት አቶ ለሚ፣ የግብፅ ዋና ብሔራዊ ጥቅም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ማስተጓጎልና እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ለማደናቀፍ ከውስጥና ከውጭ ቡድኖች ጋር መሰለፍ መሆኑን ገልጸዋል።

አቶ ቴዎድሮስ አክለው እንዳመለከቱት፣ ታሪካዊ ጠላቶች ኢትዮጵያ በውስጣዊ ልዩነቶችና አለመግባባቶች በተወጠረች ቁጥር አጋጣሚውን በመጠቀም ሀገሪቱ ስትራቴጂካዊ ጥቅሞቿን እንድታጣ ይሰራሉ። በመሆኑም እነዚህን ውጫዊ ተፅዕኖዎችና ሴራዎች ማክሸፍ የሚቻለው የውስጥ አለመግባባቶችን በሰለጠነ ውይይት በመፍታትና ትኩረታችንን ወደ የጋራ ስትራቴጂካዊ ጥቅሞቻችን በማዞር ብቻ እንደሆነ አጽንዖት ሰጥተዋል።

አሁን ላይ ኢትዮጵያ የምታደርገው የባሕር በር ጥያቄ በዓለም አቀፍ ህጎች፣ በሰላማዊ መንገድና በሰጥቶ መቀበል መርህ (Win-Win) በሚያደርጉ የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ስምምነቶች ላይ የተመሠረተ መሆኑን አቶ ቴዎድሮስ አስገንዝበዋል። ጥያቄው የጎረቤት ሀገራትን ሉዓላዊነትና ግዛት ሳይጋፋ፣ የጋራ የኢኮኖሚ እድገትና የቀጠናዊ ትስስርን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት የደረሱባትን የውጭና የውስጥ ጫናዎች በፅናት በመቋቋም ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ማጠናቀቅ፣ ሀገራዊ ምርጫንና የሀገራዊ ምክክር መድረኮችን ማካሄድ ችላለች። አሁን ላይ ሀገሪቱ ከመሸኮርመም የወጣና ብሔራዊ ጥቅሟን የሚያስከብር ጠንካራ የዲፕሎማሲ አቋም በመያዝ ላይ የምትገኝ ሲሆን፣ ህዝቡ የአሳሳች መረጃዎችን ምንጭ በመገንዘብ፣ ከስሜታዊነት በመራቅና የውስጥ አንድነቱን በመጠበቅ ወደ ባሕር በር የሚደረገውን ጉዞ ማፋጠን ይኖርበታል።

የባሕር በር ጥያቄ የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የብሔር ወይም የኃይማኖት አጀንዳ ሳይሆን የጠቅላላ ሀገርና የህዝብ የህልውና ጉዳይ ነው። እንደ ዓድዋ ድል እና እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁሉ የባሕር በር አጀንዳም የመላው ኢትዮጵያውያን የጋራ መሰብሰቢያ መሆን አለበት። የባሕር በር አጀንዳ የትናንት ቁስልን የምናክምበት ሳይሆን የነገውን ትውልድ ብልጽግና፣ ደህንነትና አብሮነት የምናረጋግጥበት ታሪካዊ መነሻ በመሆኑ፣ የውስጥ አለመግባባቶችንና ጥቃቅን ልዩነቶችን ወደ ጎን በመተው በጋራ ሀገራዊ ጉዳዮቻችን ላይ በአንድነት መቆም ያስፈልጋል።

# ደመራ የአብሮነት ማሳያ

- **የመስቀል ደመራ ከኃይማኖታዊ ይዘቱ ባሻገር ይቅርታን፣ አንድነትንና ፍቅርን የሚያሰፍን ጥልቅ እሴት መሆኑ ተመላክቷል**

**በቶለሳ መብራቴ**

በኢትዮጵያ የደመራ በዓል ከኃይማኖታዊ ይዘቱ ባሻገር ኅብረተሰቡን በአንድነት የሚያስተሳስር እና ማኅበራዊ መደጋገፍን የሚያጠናክር ትልቅ እሴት ነው። የመስቀል በዓል ዋዜማ የሚከበረው ደመራ፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የአንድነትና የመታደስ ታላቅ ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ በዓል በትውልድ ቅብብሎሽ የመጣ የማኅበረሰባችንን ሥነ-ልቦናዊ፣ ማኅበራዊ እና ባህላዊ አንድነት የሚያጸና መሠረት ነው። በየሰፈሩ የሚደረገው የደመራ አከባበር በተለይም አብሮነትን፣ መተሳሰብን እና ዕርስ በዕርስ መቀራረብን በማጠናከር ረገድ የሚጫወተው ሚና እጅግ የጎላ ማኅበራዊ ፋይዳ ያለው ነው።



ፎቶ- ከፋይል

በመስቀል አደባባይ በድምቀት የተከበረው የ2017 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል በከፊል

በየሰፈሩ የሚካሄደው የደመራ ዝግጅት የሚጀመረው በዓሉ ከመድረሱ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ነው። የሰፈሩ ወጣቶች፣ አዋቂዎች እና ሕፃናት ሳይቀሩ የደመራ እንጨትና የችቦ ቁሳቁሶችን በማዘጋጀት፣ ቦታ በመምረጥ እና ደመራውን በአንድነት በመትከል ይሳተፋሉ። ይህ የጋራ እሴት የማኅበረሰቡን የትብብር መንፈስና የአብሮነት ባህል የሚያጎለብት ከመሆኑም በላይ፣ እያንዳንዱ ሰው የደስታው አካልና ባለቤት እንደሆነ እንዲሰማው ያደርጋል። የዕድሜ፣ የጾታ ወይም የኢኮኖሚ ልዩነት ሳይደረግ የሚፈጠረው ይህ አብሮነት፣ ሰዎች በዕለት ተዕለት ማኅበራዊ ሕይወታቸው በሚገጥሟቸው ደስታና ኀዘናቸው ላይ አብረው እንዲቆሙ ዕድል የሚፈጥር በዓል ነው።

ወጣት ታከለ እምሩ የአዲስ አበባ ከተማ ጉርድ ሾላ አከባቢ ነዋሪ ነው፤ በየዓመቱ ደመራ በተቃረበ ቁጥር ከሰፈር ጓደኞቹ ጋር በመሆን የሰፈር ሰዎችን በማስተባበር በዓሉ በድምቀት እንዲከበር ያደርጋል፡፡ በዓሉ በደመቀ መልኩ እንዲከበር ለማድረግ ታከለና ጓደኞቹ ስራቸውን ይከፋፍላሉ። በጎ ፈቃደኛ የሆኑ በየአካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎችንና ነጋዴዎችን ያናግራሉ፤ ለበዓሉ ማድመቂያ የሚሆን የገንዘብና የቁሳቁስ አስተዋጽኦ በፈቃደኝነት ላይ ተመስርተው ይሰበስባሉ። ከተሰበሰበው ገንዘብም ለደመራው የሚሆን እንጨት መግዣ፣ የችቦ ዝግጅት እንዲሁም ሰፈሩን በባህላዊና ኃይማኖታዊ ውበት የሚያሸበርቁ ቁሳቁሶችን ለማዘጋጀት ያውሉታል። ይህ አስተባባሪነቱ በሰፈሩ የሚገኙ አረጋውያንን እና አቅመ ደካሞችን ጭምር ያካተተ በመሆኑ፣ እያንዳንዱ ነዋሪ የበዓሉ ባለቤት እንደሆነ እንዲሰማውና በደስታ እንዲካፈል ያደርጋል።

ታከለና የሰፈሩ ወጣቶች በጋራ ያቆሙት ደመራ ሲበራ፣ የአካባቢው ነዋሪዎች ህፃናት፣ ወጣቶችና አበው በአንድነት ተሰብስበው በእልልታና በባህላዊ ጨዋታዎች ያደምቁታል። ባዘጋጁት መርሃ ግብር መሰረት ጎረቤት ከጎረቤት ጋር ተጠያይቆ፣ በጋራ ማዕድ ተካፍሎ በዓሉን በፍጹም ሰላምና ፍቅር ያሳልፋል። የወጣት ታከለ እምሩ በየዓመቱ የሚያሳየው ይህ የቁርጠኝነትና የበጎ ፍቃደኝነት ስራ፣ የሰፈሩን አንድነት ከመጠበቁም በላይ ለቀጣዩ ትውልድ መልካም አርአያና የባህል እሴት ማስተላለፊያ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል።

እንደ ወጣት ታከለ ገለጻ፣ ደመራ ሲለኮስና እሳቱ ሲይበራ የማኅበረሰቡ አባላት ያበሰሉትን ዳቦ፣ ጠላ እና ቡና ይዘው ወደ ደመራው ስፍራ ያመራሉ። በቦታው የሚደረገው የምግብና የመጠጥ መጋራት በራሱ ትልቅ የአንድነት፣ የአብሮነት እና የመተሳሰብ መንፈስ ይፈጥራል፡፡

በኮተቤ አካባቢ የሚኖረው አንዱዓለም ጋሻው፣ የደመራ በዓል ሊደርስ ጥቂት ቀናት ሲቀሩት የሰፈሩ ሰዎች በአንድነት የደመራውን ዝግጅት በጋራ እንዲያካሂዱና የፍቅርና የወንድማማችነት መንፈስ እንዲጎለብት ያደርጋል።

አንዱዓለም የደመራ በዓል ኃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቱን እንደጠበቀ ሆኖ፣ የመገናኛና የመሰብሰቢያ ትልቅ መድረክ ተደርጎ እንደሚቆጠር ይናገራል። በዓሉ ጎረቤታሞች ማህበራዊ ትስስራቸውን የሚያጠናክሩበት አጋጣሚ ነው። በደመራው ዙሪያ የሚደረገው ስብሰባና የጋራ ዝግጅት የሰፈሩን ህዝብ ይበልጥ የሚያቀራርብ ከመሆኑም በላይ አብሮ የመኖርንና የጋራ ደስታን የመካፈል የቆየ ባህል እንደሆነ ገልጸዋል።

ከዚህም በላይ የደመራ ወቅት የተቀየሙና የተጣሉ አካላትን በማስታረቅ የሰላምና የፍቅር መንፈስ የሚነግስበት አጋጣሚ ተደርጎ እንደሚታይ አንዱዓለም ተናግሯል። አንዱዓለምና የማህበረሰቡ አባላት የተቀየሙትን በማቀራረብና በማስታረቅ በዓሉ በሙሉ ደስታና ይቅርታ እንዲከበር ያደርጋሉ፤ ይህም በዓሉ

> **“የመስቀል ደመራ በትውልድ ቅብብሎሽ የመጣ የማኅበረሰቡን ሥነ-ልቦናዊ፣ ማኅበራዊ እና ባህላዊ አንድነት የሚያጸና መሠረት ነው”**

ከኃይማኖታዊና ባህላዊ ይዘቱ ባሻገር ጥልቅ ማህበራዊ እሴት እንዲኖረው ያደርገዋል።

በዘመናዊው የሕይወት ዘይቤና በከተሞች መስፋፋት ምክንያት ሰዎች በሥራ እና በሕይወት ሩጫ በመጠመዳቸው ምክንያት ዕርስ በዕርስ እንዳይገናኙና እንዳይጠያየቁ ያደርጋቸዋል። ሆኖም የደመራ በዓል ሰዎች ለጊዜውም ቢሆን የዕለት ተዕለት ውጥረትና ጭንቀታቸውን ትተው በአንድ ስፍራ እንዲሰበሰቡ ያደርጋል። በደመራ ምክንያት በመሰባሰብ በመቀራረብ የሰፈርን ሰላምና ጸጥታ ለማስጠበቅ፣ ማኅበራዊ ትስስርን ለማጠናከር እና ነዋሪዎች ዕርስ በዕርስ እንዲጠበቁ ለማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። ደመራ ሕፃናትና ወጣቶች የማኅበራዊ ሕይወትን፣ ባህልንና ማኅበራዊ እሴቶችን የሚማሩበት ትልቅ አውድ ነው።

በአሁኑ ወቅት በከተሞች የሚታየው ፈጣን ዕድገት እና የሰዎች አኗኗር ዘይቤ መለወጥ የማኅበረሰብ አባላት ዕርስ በዕርስ የመራራቅ ሥጋት ደቅኖባቸዋል። ግለኝነት በሚስፋፋበትና ሰዎች በቴክኖሎጂ መስኮቶች ብቻ በሚገናኙበት በዚህ ዘመን፣ በየሰፈሩ የሚደመረው ደመራ ሰዎች ጠንካራ አንድነትና ትስስር እንዲኖራቸው ያደርጋል። ጎረቤት የጎረቤቱን ችግርና ደስታ በቀጥታ የሚያይበት፣ የሚያናግርበት እና የሚያካፍልበት መድረክ በመሆኑ የከተሞችን ማኅበራዊ ሕይወት ሕያው አድርጎ ያቆያል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ተመራማሪ እና የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት ደሳለኝ አምሳሉ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፣ እንደ ደመራ ያሉ የአደባባይ በዓላት ህዝባዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ፋይዳቸው የጎላ ነው። በዓላቱ በህብረተሰቡ መካከል ያለውን ማህበራዊ ትስስር ከመገንባትና ከመጠበቅ ባሻገር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ እና ፍልስፍናዊ እሴቶች እንዳሏቸውም ያመላክታሉ።

ደሳለኝ(ዶ/ር) ማህበረሰብን የሚያስተሳስሩ አወቃቀሮችን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፍሏቸዋል። የመጀመሪያዎቹ መደበኛ ተቋማት የሚባሉት የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና የትምህርት ስርዓቶች ሲሆኑ፣ እነዚህም ማህበረሰቡን በመደበኛ መንገዶች የሚያስተሳስሩ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ኃይማኖት እና ባህልን የመሰሉ ኢ-መደበኛ ተቋማት ህብረተሰቡን በአስተሳሰብ፣ በእምነት እና በማንነት አንድ በማድረግ ረገድ የማይተካ ሚና ይጫወታሉ።

እንደ ደመራ ያሉ በዓላት ህዝቡን በሀሳብ እና በእምነት ደረጃ ብቻ ሳይሆን በአካል በማገናኘት ረገድ አዎንታዊ የማህበረሰብ ግንኙነት ይፈጥራሉ። ሰዎች በአደባባይ ተገናኝተው ባህላዊ አልባሳትን ሲለብሱ፣ ሰላምታ ሲለዋወጡ እና አብረው ምግብ ሲካፈሉ ማህበራዊ አብሮነቱ እና ዕርስ በዕርስ የመቀራረብ እሴቱ በከፍተኛ ሁኔታ ይጎለብታል።

በአሁኑ ወቅት በከተሜነት እና በሉላዊነት ምክንያት የሰዎች የአኗኗር ዘይቤ እየተቀየረ ቢመጣም፣ የባህል ለውጥ ተፈጥሮአዊ ሂደት በመሆኑ ከተሜነት ባህልን ማጥፋት እንደሌለበት ደሳለኝ (ዶ/ር) ያብራራሉ።

በየሰፈሩ የሚደረገው የደመራ በዓል አከባበር ከኃይማኖታዊ ሥርዓትነት ያለፈ ትልቅ ማኅበራዊና ባህላዊ ፋይዳ ያለው የሀገራችን ውድ እሴት ነው። በየሰፈሩ የሚቀጣጠለው የደመራ እሳት የማኅበራዊ ሕይወታችን ብርሃን ሆኖ፣ የሰዎችን ልብ በፍቅር የሚያሞቅ፣ ቅሬታንና ጠብን የሚያቃጥል እንዲሁም የአንድነትንና የመተሳሰብን ፍሬ የሚያፈራ ነው። ስለሆነም ይህንን የመተሳሰብ፣ የመደጋገፍ እና የአብሮነት ገመድ ሳይበጠስ አጥብቆ የሚይዘውን የደመራ አከባበር ባህላችንን ተንከባክበን ጠብቆ ለወደፊቱ ትውልድ ማስተላለፍ የሁላችንም ማኅበራዊ ኃላፊነት ነው።

## የቅጠል... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ፦ ከገፀ ድር
ወደ "መርካቶ የበጎነት መንደር" የተቀየረው ቅጠል ተራ የቀድሞ እና የአሁን ገጽታ

የአካባቢው ነዋሪዎች የትላንቱን ህይወታቸውን ሲያስታውሱ በፊታቸው ላይ ቁጭት ይነበባል፤ አካባቢው የተጎሳቆለ፣ ለሰው ልጅ ኑሮ የማይመችና መራር ህይወት የሚገፋበት እንደነበርም በምሬት ይመሰክራሉ። ከዚሁ ሰፈር በነበሩት አሮጌና ደሳሳ ቤቶች ምትክ የተገነባውን አዲስና ዘመናዊ መኖሪያ ቤት ከተረከቡት ነዋሪዎች መካከል ወይዘሮ አመለወርቅ ብርሃኑ አንዷ ናቸው። "ድሮ እኮ አንዳች ደስታ ወይም ድግስ ሲኖረን ወዳጆቻችንን እንጋብዝ ነበር፤ አብረውን እንዲደሰቱልን ስንጠራቸው የሰፈሩን መቆሸሽ፣ የፅዳት ጉድለቱንና መጎሳቆሉን እያዩ 'ወደዚያ ቦታማ አንመጣም፣ አንበላም፣ አንጠጣምም!' እያሉ ይሸሹን ነበር" በማለት ይኖሩበት የነበረውን፣ ክብራቸውን የማይመጥን አኗኗር በቁጭትና በስሜት ያወሳሉ።

ሁሉንም ነገሮች አሟልቶ የተገነባውና ለነዋሪዎች የተላለፈው አዲሱ ዘመናዊ ቤት የእፎይታ አየር እንዲተፍሱ ካደረጋቸው መካከል ወይዘሮ አዱኛ ይመር ሌላኛዋ ናቸው። ወይዘሮ አዱኛ ከዚህ ቀደም ያሳለፉት መራር ህይወት ተነግሮ የሚያልቅ እንዳልሆነ በስሜት ይናገራሉ። "በወቅቱ ለመግለፅ የሚከብድ የፅዳት ጉድለት ባለበት ቤት ውስጥ ነበር የምንኖረው፤ መፀዳጃ ቤት እንኳን ስለሌለን ሽንት በ'ፖፖ' ነበር የምንደፋው" ሲሉ ያንን አስቸጋሪ ጊዜ ያስታውሳሉ። "ለረጅም ዓመታት እጅግ ብዙ ውጣ ውረድና ፈተና አሳልፈናል፤ የቀድሞውና የአሁኑ አኗኗራችን በፍፁም የሚነፃፀር አይደለም" በማለት ያሳለፉትን መራር ህይወትና የዛሬውን እፎይታ በደስታ ስሜት በእንባ ተሞልተው ገልጸውታል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመርካቶ "ቅጠል ተራ" አካባቢን ወደ ዘመናዊ መንደርነት ለመለወጥ ከዛሬ አራት ወራት በፊት የጀመረውን ፕሮጀክት አጠናቅቆ ለነዋሪዎች አስረክቧል፡፡ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ ዘመናዊና ውብ ሆነው የተገነቡትን መኖሪያ ቤቶች ለነዋሪዎች ባስተላለፉበት ወቅት እንደተናገሩት "ቅጠል ተራ" ተደጋጋሚ የእሳት አደጋ የተከሰተበትና ብዙዎችም ለጉዳት የተዳረጉበት አካባቢ እንደነበር ተናግረዋል፡፡ ይህንን አካባቢ መልሶ በመገንባት በተሰራው ስራ አካባቢው ውብና ፅዱ ሆኗል፡፡ መኖሪያ ቤቶችንና ሱቆችን ጨምሮ እንዲነሱ የተደረጉት 130 አባዎራዎችና እማወራዎች ናቸው፡፡ በመልሶ ግንባታው ከ960 በላይ መኖሪያ ቤቶችና ሱቆች ተገንብተዋል፡፡ "መኖሪያ ቤቶቹ እንዲሁ መኖሪያ ቤት የሚባሉ አይደሉም፤ ብዙ ትርጉም ያላቸው ናቸው፡፡ ፅዱ የመኖሪያ ስፍራ፣ መፀዳጃ ቤት፣ የማብሰያ፣ ውሃ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ማግኘት ለነዋሪው አዲስ ታሪክ ነው" ብለዋል፡፡

ወይዘሮ አዱኛ በማብራሪያቸው፣ "አዲሱ ዘመናዊ መንደር ከቀድሞ ጋር ለንፅፅር የማይቀርብ ነው፡፡ የአኗኗር ዘይቤያችን የሚቀይሩና በህይወታችን ላይ መሻሻል የሚያመጡ ናቸው። ለዚህም ቤቱን በአጭር ጊዜ ገንብቶ ላስረከበን የከተማ አስተዳደሩ ምስጋና እናቀርባለን። "ከንቲባችንን እድሜና ጤና ይስጥልን፤ ከነበርንበት ጨለማ አውጥታ ወደዚህ ብርሃን አሸጋግራናለች።" ብለዋል። "የሆነው ሁሉ ህልም ነው የሆነብኝ" በማለት ከዚህ በኋላ ፈጣሪን እድሜ ብቻ እንዲሰጣቸው እንደሚለምኑ ተናግረዋል።

አካባቢው ለበርካታ ዓመታት በመንግስት አካላት ቢጎበኝም ምንም ዓይነት ዘላቂ መፍትሔ ሳያገኝ መቆየቱን የሚያስታውሱት ሌላኛዋ ነዋሪ ወይዘሮ አመለወርቅ በበኩላቸው፤ አሁን ላይ ይህን ዘመናዊና ጽዱ ቤት በማግኘታቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል፡፡ "እፎይታ ያገኘሁትና እንቅልፍ ወስዶኝ መተኛት የጀመርኩት አሁን ነው። አሁን እየተጦርኩ ነው፤ መጠለያ ቤት አግኝቻለሁ። ፈጣሪ ይመስገን፤ ለከንቲባዋም ምስጋና ማቅረብ እወዳለሁ" ሲሉ ተናግረዋል።

ከግንባታው በፊት አካባቢውን በአካል ተገኝተው ማየታቸውን የተናገሩት ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ መኖሪያ ቤቱ ጉስቁልና ብቻ ሳይሆን ወደ ቤቶቹ ለመግባት የሚያስችል መንገድ አልነበረም፡፡ ዛሬ በብሎኮቹ መካከል ደረጃውን የጠበቀ አስፋልትና የእግረኛ መንገድ እንዲገነባ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የልጆች መጫወቻ፣ የስፖርት መስሪያ፣ ፖሊስ ጣቢያ... ሁሉንም የልማት አይነቶች አቀናጅቶ የያዘ ነው፡፡ ከ371 በላይ የስራ ዕድል የሚፈጠርባቸው ሱቆችም ተገንብተዋል፡፡

መልሶ ግንባታው የመሬት አጠቃቀምንና ፍትሃዊነትን ማስፈን ያስቻለ እንደሆነ የተናገሩት ከንቲባዋ፣ ለእያንዳንዱ ትናንሽ መሬት በመስጠት ከመከፋፈልና ሀብቱን ውስን ከማድረግ ይልቅ በጋራ በመጠቀም ሁሉንም ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል፡፡ 130 ቤቶች የነበሩበትን ከ960 በላይ አባወራዎች እና እማወራዎች እንዲጠቀሙበት ማድረግ ያለውን ሀብት ሰብስቦ በማድረግ መጠቀም እንደሚቻል ማሳያ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ከንቲባዋ እንደተናገሩት፣ የተጎሳቆሉ መንደሮችን በመልሶ ግንባታ ወደ ፅዱ፣ ውብና ለመኖሪያ ምቹ የሆነ አካባቢ የመቀየር ስራው በቅጠል ተራ ብቻ የሚቆም አይደለም፡፡ በገዳም እና ጣሊያን ሰፈሮች ተጀምሯል፤ በሌሎች አካባቢዎችም ይቀጥላል፡፡ ከዚህ በኋላ የቀበሌ ቤቶች ላይ የመልሶ ግንባታ ሲካሄድም ነዋሪዎች ለጊዜው በተሻለ መኖሪያ ቤት እንዲቆዩ እንደሚደረግ ተናግረዋል፡፡

ከቅጠል ተራ ወደ "መርካቶ የበጎነት መንደር" የተቀየረዉ የመኖሪያ ስፍራ በ11 ሺህ ካሬ ሜትር ላይ የተገነቡ ከመሬት በታች አንድ ጨምሮ ባለ ዘጠኝ ወለል ዘጠኝ ብሎኮች፣ ከ960 በላይ ቤቶችና ሰፊ የስራ እድልን የሚፈጥሩ 371 የንግድ ሱቆችን አካትቶ የተገነባ ነው፡፡ በተጨማሪም በውስጡ የህጻናት የመጫወቻ ስፍራ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ (የኳስ ሜዳ፣ ቅርጫት ኳስ፣ የእጅ ኳስ፣ የመረብ ኳስ)፣ የመኪና ማቆምያ ፓርኪንግ፣ የኤሌክትሪክ መኪና ቻርጅ ማድረጊያ፣ የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገድና ሌሎች ዘመናዊ መሰረተ ልማቶችን ያካተተ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በኢትዮጵያ ፐብሊክ ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ጥናት ኮሌጅ የከተማ ልማት መምህርና ምክትል ዲን ሂርጶ በሪሶ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ማብራሪያ፣ ከተማ የሚታደስበት የተለያዩ አማራጮች አሉ፡፡ አንደኛው ነዋሪው ባለበት ሳይፈናቀል እንደ መንገድ፣ ውሃ፣ ኤሌክትሪክ ያሉ መሰረተ ልማቶችን የማስተካከልና ደረጃቸውን የማሳደግ ስራ ነው፡፡ በቅጠል ተራ እንደተደረገው ነዋሪዎች ሳይፈናቀሉ ባሉበት የሚከናወን የከተማ ልማት፣ የገነቡትን ትዝታ የሚያስቀጥልና ማህበራዊ ትስስር የማይነካ በመሆኑ ሊበረታታ የሚገባው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የደቀቁና ያረጁ ቤቶች የሚይዙት ቦታ ወደላይ ሳይሆን ወደጎን ነው። በእነዚህ ቦታዎች ላይ ያሉ ቤቶች ፈርሰው አዲስ ዘመናዊ ቤቶች መገንባት ሰፊ የልማት መሬት እንዲገኝ ያደርጋል። መንግስት ማግኘት ያለበትን ገቢ እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡ የቦታው መታደስ የአካባቢውን ገፅታ እንደሚቀይር የከተማ ልማት ምሁሩ ሂርጶ ያስረዳሉ፡፡ እንደ ቅጠል ተራ አይነት የደቀቁ ሰፈሮች ጨለማና በቂ ብርሃን የሌለባቸው በመሆኑ ለወንጀል ድርጊዎች የተጋለጡ ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ የአካባቢው መፅዳት፣ መብራትና የተለያዩ ዘመናዊ መሰረተ ልማቶች መሟላት እንደ ወንጀል ያሉ ማህበራዊ ችግሮችን ይቀርፋል፡፡ ወደ ከተማ የሚመጡ ቱሪስቶች በነጻነት የሚንቀሳቀሱበትን አካባቢ ይፈጠራል። ይህም የቱሪስት ስበትን ይጨምራል፡፡ ኢንቨስትመንትና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲነቃቃ ያደርጋል፤ የከተማዋን ገፅታም ይቀይረዋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ነዋሪዎች ህይወታቸውን በተሻለና ምቹ አካባቢ የሚመሩበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በነዋሪው ሕይወት ላይ የሚመጣው ለውጥ ተደምሮ በከተማና በሀገር ደረጃ ለውጥ እንዲመጣ እንደሚያደርግ ነው የከተማ ልማት ምሁሩ ሂርጶ የሚያስረዱት፡፡ አዲስ አበባ ከአራትና አምስት ዓመት ወዲህ ያላት ገፅታ በጣም የተለየ ነው፡፡ ሁሌም አዲስ ነገሮች እየታዩ ነው፡፡ በሌሎች ዓለም ከተሞች የሚታዩ ጥሩ ነገሮች በአዲስ አበባም እየተስተዋሉ ነው፤ እንዲህ አይነት ስራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው አክለዋል፡፡

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
Addis Ababa City Administration

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳ ን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ይገልፃል፡፡

እንኳን
ለብርሃነ መስቀሉ
አደረሳችሁ!

ከተማችን አዲስ አበባ የነዋሪዎችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥና ከተማዋን የሚመጥን ገፅታን እንድትላበስ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ ትገኛለች፡፡

በተጨማሪም የባህል፣ የቱሪዝም፣ የዓለም ዓቀፍ ኮንፈረንስ፣ የንግድ፣ የታሪክ፣ የብዝሓነት እና የአንድነት ማዕከል ሆና ጉዞዋን በላቀ ልዕልና ቀጥላለች፡፡

በተለይ ባለፉት አምስት ዓመታት በሁሉም ዘርፎች ቃልን በተግባር በመለወጥ  በጥራት እና በፍጥነት የመጨረስ ተምሳሌት የሆነችው አዲስ አበባ በሰው ተኮር ስራዎቿ የተራቡትን ያጎረሰች፣ ህፃኖቿን የደገፈች፣ ተማሪዎቿን ያስታወሰች፣ ማዕድ ያጋራች በአጠቃላይ የኑሮ ጫናን ለማቅለል ሸክም በመጋራት አንባዎችን ያበሰች፣ በዚህም ዘላቂና ቀጣይነት ያለው ለውጥ በማስመዝገብ እንደ አዲስ የተፈጠረች ከተማ መሆኗን ዓለምን በማስደመም አሁንም አዳዲስ ስኬቶችን ይበልጥ እያሳየች ትገኛለች፡፡

ከተማ አስተዳደሩ ለህዝብ የገባውን ቃል በተግባር ለመፈፀም በሚያደርጋቸው ጥረቶች ሁሉ የከተማችን ነዋሪዎች የተለመደው ሁለንተናዊ ድጋፋችሁ እንዳይለየን በማለት ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡



**መልካም የመስቀል በዓል!**
**የአዲስ  አበባ ከተማ አስተዳደር**



ላይፍ ኀ/የተ/መ/ ቁጠባና ብድር የህብረት ሥራ ማህበር
LIFE SAVING AND CREDIT COOPERATIVE Ltd.

አሮጌው ዘመን አልፎ አዲሱ ዓመት ሲተካ አደይ አበባ ሲፈነዳ ዘመድ ከዘመዱ እንኳን አደረሳችሁ እየተባባለ ልዩ የአዲስ ዓመት ስጦታ ሲያበረክት፤ ላይፍ ቁጠባና ብድርም በየዓመቱ አዳዲስ የቁጠባና ብድር አማራጮችን ለማህበረሰቡ እያበረከተ ይገኛል፡፡

ያኔ በመቶ ሺዎች ካፒታል ስራውን ሀ ብሎ የጀመረው ላይፍ ቁጠባና ብድር አባላቱን ቤትና መኪና እያምበሸበሸ ከስኬት ማማ ላይ አድርሶ ዛሬ ላይ አንድ ቢሊየን ተቀማጭ ካፒታል ላይ ደርሷል፡፡

እርሶም በ2019 ዓ.ም በብርሃነ መስቀሉ ስኬታማ በዓል እንዲያሳልፉ የሁል ጊዜ ምርጫዎ ላይፍ ቁጠባና ብድር ይሁን ይሎታል፡፡

ለቤት፣ ለመኪና፣ ለንግድ ማስጀመሪያና ማስፋፊያ በአጭር ጊዜና ቀልጣፋ አሰራር በከፍተኛ የብድር ጣሪያ እስከ 20 ሚሊየን ብር እኛ ጋር ያገኛሉ፡፡

በበዓል ክልብ ለሚወዱት የሚበረከቱት ልዩ ስጦታዎችን እንንገሮት፤ የቤት ቁጠባ፣ የመኪና ቁጠባ፣ የንግድ ማስጀመሪያ አልያም ማስፋፊያ እና የህፃናት ቁጠባን በስጦታ ያበርክቱ፡፡

ከኛ ጋር አዲስ ቤተሰብ ለመሆን የቱ ቅርንጫፍ ይቀርቦታል? ዋናው ቢሮ 6 ኪሎ ቅርንጫፎቻችን አራዳ ጊዮርጊስ፣ ደጃች ውቤ፣ ሀያ ሁለት፣ ጀሞ 1፣ ቡራዩ፣ ለገጣፎ በክልል ከተሞችም አዳማና መቀሌ  እንገኛለን፡፡

*መልካም የመስቀል ጹመራ በዓል ይሁንላችሁ!*
*ላይፍ ኃ/የተ/መ/ ቁጠባና ብጽር የህብረት ስራ ማህበር!*




SIKET BANK
እንኳን ለደመራ እና መስቀል
በዓል በሰላም አደረሳችሁ።
በዓሉ የሰላም፣ የጤና እና የስኬት
እንዲሆንላችሁ እንመኛለን።
መልካም በዓል!
ስኬት ባንክ የስኬትዎ መሰረት!
www.siketbank.com
8342
ስኬት ባንክ የስኬትዎ መሰረት!
SWIFT SSHCETAA


ተደራሽ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ.የተ.የህ.ሥ.ማህበር
Tederash Saving & Credit Cooperative Society Ltd.
እንኳን ለ2019 ዓ.ም
ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሳችሁ!
አቶ አለማየሁ በየነ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ
ተደራሽ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የህ/ስ/ማ በዓሉ የሰላም
የጤናና የፍቅር እንዲሆንላችሁ ይመኛል።
የምንሰጣቸው አገልግሎቶች
1 የቁጠባ አገልግሎት
• መደበኛ ቁጠባ
• የፍቃደኝነት ቁጠባ
• የጊዜ ገደብ ቁጠባ
• የንግድ/የቀን ገቢ ቁጠባ
• የቤት ቁጠባ
• የመኪና ቁጠባ
• የሴቶች ልዩ ቁጠባ
• የወጣቶች/ተማሪዎች ቁጠባ
• የህጻናት/ልጆች ቁጠባ
• የድርጅት ቁጠባ
• የኤሌክትሪክ መኪና ባትሪ ቁጠባ
2. ከወለድ ነፃ የፋይናንስ አገልግሎት/ Interest Free Service
3. የብድር አገልግሎት
• በአዲስ ንግድ ስራ ለሚሰማሩ እና ለነባር ንግድ ማስፋፊያ
• ለቤት ግንባታ፤ ግዥና እድሳት
• ለኮንዶሚኒየም ክፍያ
• ለመኪና ግዥ
• ለኢንቨስትመንት
• ለስራ ፈጠራ
• ለማህበራዊ ጉዳይ፦ ለሕክምና፤ ለትምህርት ስልጠና ለንብረት ግዥና ዕድሳት፤ ለቀለበትና ጋብቻ
• ለብድር መድህን ዋስትና እንዲሁም የተለያዩ ኑሮን ለማሻሻል ለሚያስችሉ ጉዳዮች መበደር ይችላሉ።
መልካም በዓል!
ስልክ 7078/0970444411/88/00, አድራሻ ዋና ቢሮ አራት ኪሎ ኢትዮጵያ ፖስታ ቤት
ትንሽ ቆጥበው ትልቅ ይሁኑ!
ተደራሽ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የህ/ስ/ማህበር
እንኳን
ለብርሃነ መስቀል
አደረሳችሁ!

# የሀገር ከፍታ መሠረቶች

**• የ"ጉባ ብስራቶች" የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ አቅም እንደሚያሳድጉ ተገልጿል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

ኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ሀገራዊ እድገትና ብልፅግናን ማምጣት የቻሉ ስኬቶችን እያስመዘገበች ትገኛለች:: ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ጨምሮ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ፣ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማልማትና በማስፋፋት፣ የስንዴ ምርታማነትን በማሳደግ፣ በአረንጓዴ አሻራ፣ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ፣ በከተማ ልማትና በሌሎች ስራዎችም ተጨባጭ ውጤቶች መጥተዋል። በዚህም በራስ አቅም የመቆም፣ የመስራትና ለውጥ የማምጣት አህጉራዊ ተምሳሌነቷን እያረጋገጠች ትገኛለች::



ግራፊክስ ፦ እዮብ ተፈራ
ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጉባ ላይ ያበሰሯቸው ሰባቱ ፕሮጀክቶች

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የ2019 አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግ ባስተላለፉት መልዕክት ዓመቱ የጉባ ብሥራቶች የበለጠ ተግባራዊ የሚሆኑበት እንደሆነ ተናግረዋል:: የጉባ ብስራቶች ከአንድ ዓመት በፊት ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በይፋ በተመረቀበት ወቅት ግድቡ በሚገኝበት ቦታ ጉባ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ይፋ ያደረጓቸው ግዙፍና ስትራቴጂካዊ ፕሮጀክቶች ናቸው:: የኒውክሌር ማበልጸጊያ (ለሰላማዊ ጥቅም የሚውል የኒውክለር ሀይል ልማት)፣ የጋዝ ፋብሪካ፣ የነዳጅ ማጣሪያ፣ በአፍሪካ ግዙፉ አየር ማረፊያ፣ 2ኛውን የጋዝ ፋብሪካ ግንባታ፣ የማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ቤቶችን መገንባት በሚቀጥሉት አምስትና ስድስት ዓመታት የሚተገበሩ የጉባ ፕሮጀክቶች መሆናቸው በወቅቱ መናገራቸው ይታወሳል::

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ማህበር ከፍተኛ ተመራማሪ ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ ሰባቱ የጉባ ብስራት ፕሮጀክቶች የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ወደፊት ለማስፈንጠር መሰረታዊና ወሳኝ ናቸው:: ከፕሮጀክቶቹ መካከል እንደ የጋዝ ፋብሪካ፣ የኒውክለር ሀይል ማበልፀግ የመሳሰሉትን ከሀይል አቅርቦት ጋር የተያያዙትን ብናነሳ በዘመናዊ የኢኮኖሚ ስርዓት ግንባታ ውስጥ ሀይል ዋና የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተርና ግብዓት ነው:: በአሁኑ ወቅት ሀይል የማይፈልግ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የለም:: በኢኮኖሚ የበለፀጉ ሀገራት የሀይል አቅርቦታቸው ከፍተኛ ነው:: ኢትዮጵያም ይህን ለማሳደግ የምታደርገው ጥረት ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማምጣት፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትንና የውጭ ምንዛሬ ምንጭ በመሆን ከፍተኛ ፋይዳ አለው::

የአፈር ማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታውንም ብናነሳ ኢትዮጵያ ለግብርናው የሚያስፈልጋትን ከውጭ በምንዛሪ እየገዛች ስትሸፍን ቆይታለች። ከ80 በመቶ በላይ የኢትዮጵያ ህዝብ በግብርና የሚተዳደር ቢሆንም የማዳበሪያ ፋብሪካ አልነበረም:: በዚህም የተነሳ ኢትዮጵያ ለማዳበሪያ ግዥ በየዓመቱ በቢሊዮን የሚቆጠር የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሪ ወጪ ታደርጋለች። ይህም ከወጪ ንግድ ገቢ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ የሚሻማ ሲሆን፣ መንግሥት ለአርሶ አደሩ የሚያቀርበውን ድጎማ ለመሸፈንም በየዓመቱ በቢሊዮኖች የሚቆጠር ብር ይመድባል። ለአብነትም ለ2017/18 ምርት ዘመን ብቻ ለአፈር ማዳበሪያ ግዥ 84 ቢሊዮን ብር ድጎማ መደረጉን የግብርና ሚኒስቴር በይፋዊ የማህበራዊ ትስስር ገጹ (ፌስቡክ) በ2017 ዓ.ም ያወጣው መረጃ ያመለክታል::

ከአንድ ዓመት በፊትም በሶማሌ ክልል በዓመት ሶስት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ዩሪያ ማዳበሪያ ማምረት የሚያስችል የዩሪያ ማዳበሪያ ፋብሪካ እና የነዳጅ ማጣሪያ ፋብሪካ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) የመሰረት ድንጋይ ተጥሎ ግንባታው እየተከናወነ ይገኛል:: የዩሪያ ማዳበሪያ ፋብሪካ ፕሮጀክቱን በ40 ወራት ወይም በሶስት ዓመት ከአራት ወር ጊዜ ለማጠናቀቅ እየተሰራ ይገኛል::

በግንቦት ወር 2018 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፋብሪካው ግንባታ ያለበትን ሁኔታ በፋብሪካው ግንባታ የ60 በመቶ ድርሻ ካለው የዳንጎቴ ግሩፕ ሊቀ መንበር አሊኮ ዳንጎቴ ጋር በመሆን ከጎበኙ በኋላ፣ የፕሮጀክቱ መጠናቀቅ የኢትዮጵያን አንድ ቁልፍ ችግር የሚፈታ መሆኑን ተናግረዋል። ከፍተኛ ተመራማሪው ሞላ (ዶ/ር) እንደሚገልፁት፣ የማዳበሪያ ፋብሪካው ለሀገር ውስጥ የሚያስፈልገውን አቅርቦት በመሸፈን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን በማዳንና የግብርና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል::

በጉባ ይፋ ከተደረጉ ብስራቶች መካከል ሌላኛው በአፍሪካ ግዙፍ የሆነው የአየር ማረፊያ ግንባታ ነው:: ጥር 2 ቀን 2018 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፍያ ግንባታ ስራ የመሰረት ድንጋይ ማስቀመጣቸው ይታወሳል:: በወቅቱ ባደረጉት ንግግርም፣ የአየር ማረፊያው የኢትዮጵያ የዝመና ጉዞ፣ የብልፅግና፣ የመለወጥ፣ ራሷን ችላ በሁለት እግሯ የመቆም መሻትን የሚገልጥ ስራ እንደሆነ መግለፃቸው አይዘነጋም:: በፕሮጀክቱ የመጀመሪያው ምዕራፍ 60 ሚሊዮን መንገዶችን ማስተናገድ የሚችል የአየር ማረፊያ ግንባታ በፈረንጆች አቆጣጠር 2030 ይመረቃል:: በሁለት ምዕራፎች የሚገነባው የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ እና ሌሎች የተጀመሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታቸው ሲጠናቀቅ ከአስር ዓመት በኋላ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2036 ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀዳሚ ኢኮኖሚ ትገነባለች ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ተናግረዋል::

በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፉ ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ የሚያነሱት ከፍተኛ ተመራማሪው ሞላ (ዶ/ር)፣ ዘመናዊ፣ በርካታ መንገደኞችንና እቃዎችን ማመላለስ የሚያስችል የአየር ማረፊያ መኖር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን በማነቃቃት እድገት ያመጣል:: የሚመረተውን ምርት ወይም አገልግሎት በሚፈለገው አካባቢ በፍጥነት ማድረስ ያስችላል:: የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትንም ይስባል::

አዲሱ የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ትልቅ አንድምታ ያለው መሆኑን በተባበሩት መንግስታት በአስተዳደር፣ በድህነት ቅነሳና ዘላቂ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ የፖለሲ አማካሪ፣ በአፍሪካ ሰብዓዊ ኔትዎርክና የተለያዩ የጥናትና ምርምር ተቋማት ቦርድ ሰብሳቢና አባል በመሆን የሰሩት ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ መረጃ እንደሚያሳየው፣ በ2017 በጀት ዓመት አየር መንገዱ 7 ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር ገቢ አግኝቷል:: በ2018 በጀት ዓመት ደግሞ 9 ነጥብ 1 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቱን ተቋሙ ያወጣው መረጃ ያሳያል:: አሁን ላይ አየር መንገዱ በዓመት ከ20 ሚሊዮን በላይ መንገደኞችን እያገለገለ ሲሆን በአዲሱ አየር ማረፊያ ግንባታ ምክንያት 110 ሚሊዮን ሰዎችን ማስተናገድ ይችላል። ይህም አቅሙን በብዙ እጥፍ በማሳደግ ለኢኮኖሚው የሚያበረክተውን ድርሻ ከፍ እንዲል ያደርገዋል::

የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ቆስጠንጢኖስ እንደሚገልፁት፣ አየር ማረፊያ በሚገነባበት ወቅት የስራ ተቋራጮችን ጨምሮ ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል ይፈጥራል:: ለአየር ማረፊያው ግንባታ የሚያገለግሉ ዕቃዎችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ይገነባሉ:: በዚህም ትልቅ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይፈጠራል። ከዚህ ባሻገር እንዲህ ዓይነት ግዙፍ አየር ማረፊያዎች ሲገነቡ በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን አገልግሎት በማቅረብ ተጠቃሚ ይሆናሉ:: ሆቴሎች ስለሚገነቡ በርካታ የስራ ዕድሎች ይፈጠራሉ:: በአዲስ አበባ በርከት ያሉ ስብሰባዎች የሚደረጉበትና ከተማዋ በኮንፈረንስ ቱሪዝም ተመራጭና ተጠቃሚ የምትሆንበት ዕድል ይጨምራል:: የዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ መዲናነቷን ያጠናክራል:: አዳዲስ የተሰሩ የቱሪስት መዳረሻዎች ይጎበኛሉ:: ምክንያቱም አዲሱ አየር ማረፊያ 270 በላይ አውሮፕላኖችን ማቆም ያስችላል::

የጉባ ብስራቶች ከቃል ወደ ተግባር እየተቀየሩ መሆናቸውን ሌላ ማሳያ የሚሆን የመኖሪያ ቤት አቅርቦትን ለመፍታት እየተደረገ ያለው ጥረት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ከሁለት ሳምንት በፊት በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ይፋ እንዳደረጉት፣ በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የተለየ የቤት መግዣ ብድር መልሶ ማጠናከሪያ ኩባንያ ለማቋቋም የሚያስችል የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን (IFC) ተከናውኗል:: በ100 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ካፒታል የተቋቋመው እና ዓለም አቀፉ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን ደግሞ 200 ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ አስተዋፅኦ የሚያደርግበት ይህ ተቋም፤ በባንክ ዘርፉ ውስጥ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት አለመመጣጠንን የሚቀርፍ እና የቤት መግዣ ብድር ፋይናንስን የሚያስገኝ ነው። ይህ አጋርነት በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገነቡ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ቤቶችን ለማቅረብ እንዲሁም በፋይናንስ ስርዓቱ ውስጥ የግል ዘርፉን ተሳትፎ ለማሳደግ የተያዘውን ግብ ለማሳካት የሚያስችል ወሳኝ እርምጃ ነው::

በአጠቃላይ ፕሮጀክቶቹ ያላቸው ሀገራዊ ፋይዳ ከፍ ያለ በመሆኑ በተያዘላቸው ጊዜ በጥራት እንዲጠናቀቁ ማድረግ እንደሚገባ ከፍተኛ ተመራማሪው ሞላ (ዶ/ር) ያስረዳሉ። ከሀገራዊ ለውጡ በፊት ባሉ ዓመታት ብዙውን ጊዜ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ፣ ወጪና ጥራት ከማጠናቀቅ አኳያ ክፍተቶች ይታዩ ነበር። ደካማ የፕሮጀክት አስተዳደር በመኖሩ ተጨማሪ ሀብትና ጊዜም ይጠይቁ ነበር። ከዚህ አኳያ የጉባ ብስራት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜና በጀት በጥራት እንዲጠናቀቁ ማድረግ ይገባል::

በቅርብ ዓመታት የኮሪደር ልማትና የተለያዩ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን በቀን 24 ሰዓት በሳምንት ሰባት ቀናት በማከናወን ማጠናቀቅ የተቻለበት መንገድ ለፕሮጀክት አፈጻጸም ትልቅ ትምህርት መሆን እንደሚችል ከፍተኛ ተመራማሪው ሞላ (ዶ/ር) ያነሳሉ። በአንድ ሀገር ልማት የሚከናወነው በሶስት ሀይሎች ነው፤ በመንግስት፣ በባለሀብቱና በህብረተሰቡ አማካኝነት። ህብረተሰቡ ጉልበቱን በማበርከት፣ ባለሀብቱ ኮንትራት በመውሰድ አሊያም መዋዕለ ንዋዩን በማፍሰስ ሲሳተፍ፣ መንግስት ስራዎች የሚሰሩበትን መንገድ ማመቻቸትንና ገንዘብ ማቅረብን ጨምሮ በተለያየ መልኩ ድጋፍ ያደርጋል:: ከዚህ አኳያ የሶስቱ አካላት ተቀናጅቶ መስራት ወሳኝ ነው። የግሉ ዘርፍ ፕሮጀክቶቹ በባለቤትነትና በሀገር ተቆርቋሪነት ስሜት በጥራትና በተቀመጠላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ መስራት አለበት:: ማህበረሰቡ በጉልበትም ሆነ በሚፈለገው መልኩ በእኔነት ስሜት ለመሳተፍ ዝግጁ ሆኖ መገኘት እንዳለበት ተናግረዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በአዲሱ ዓመት ባስተላለፉት መልዕክት፣ በሁሉም መስክ የተያዙት እቅዶች እንዲሳኩ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ልሂቃን፣ የኃይማኖት አባቶች፣ የጸጥታ ተቋማት፣ የአምራች ኢንዱስትሪዎች፣ የንግዱ ማኅበረሰብ፣ አርሶ አደሩ፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ መገናኛ ብዙሃን፣ መንግስት ሰራተኛው ሚናቸው ወሳኝ እንደሆነ አስረድተዋል::

በጥቅሉ ኢትዮጵያ በቅርብ ዓመታት ያስመዘገበቻቸው ሁለገብ ስኬቶችና የ"ጉባ ብሥራቶች" ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚያሸጋግሩ ወሳኝ እርምጃዎች መሆናቸውን ነው የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች የሚናገሩት:: እንደ የኒውክለር ኃይል ማበልጸጊያ፣ የጋዝ እና የነዳጅ ማጣሪያ፣ የአፈር ማዳበሪያ ፋብሪካ እንዲሁም ግዙፉ የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ያሉ ፕሮጀክቶች የሀገሪቱን መሠረታዊ የኢኮኖሚ ማነቆዎች በመፍታት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬን ያድናሉ፤ ተጨማሪ የኢንቨስትመንት እና የስራ ዕድሎችንም ይፈጥራሉ።

እነዚህ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው ጊዜ፣ በጀት እና ጥራት ተጠናቅቀው ሥራ ላይ ሲውሉ የሀገር ውስጥ ምርታማነትን ከመጨመራቸውም በላይ ኢትዮጵያ በራስ አቅም በመቆም የአፍሪካ ግንባር ቀደም ኢኮኖሚን የመገንባት ርዕይዋን ያፋጥናሉ። ይህን ታላቅ ሀገራዊ ጉዞ ስኬታማ ለማድረግ የመንግሥት፣ የግሉ ዘርፍ እና የጠቅላላው ማህበረሰብ የተቀናጀ ጥረት እና ባለቤትነት ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

# የፅናት ፍሬ

• የንግሥት እሌኒ የመስቀሉ ፍለጋ ጽናት ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ግንባታ ትልቅ ትምህርት እንደሚሰጥ ተገልጿል

**በስንታየሁ ምትኩ**

በኢትዮጵያ በታላቅ ድምቀት በአደባባይ ከሚከበሩ በዓላት መካከል የመስቀል ደመራ አንዱ ነው፡፡ የበዓሉ አጀማመር ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተቀበረበት ተቆፍሮ መገኘትና የመስቀሉ አንዱ ክፋይ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በግሸን አምባ መቀመጥ ጋር የተገናኘ እንደሆነ በመስቀሉ ዙሪያ የተፃፉ የታሪክ ሰነዶች ያሳያሉ፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የስምሪት ክፍል ኃላፊ አለቃ አዕምሮ ዘውዴ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ መስቀሉን ለማግኘት የተደረገው ጥረት ፍሬ ያፈራው በንግስት እሌኒ አማካይነት ከተቀበረ ከ300 ዓመታት በኋላ ነበር፡፡ ንግስት እሌኒ ልጇ ቆስጠንጢኖስ ሲወለድ “ልጄ አድጎ ክርስቲያን ቢሆን፣ አይሁድ የቀበሩትን መስቀል ፈልጌ አስቆፍሬ አወጣለሁ” ብላ ለእግዚአብሔር ስለት ገብታ ነበር። ልጇ አድጎና የአባቱን መንግስት ተረክቦ በነገሰ ጊዜ፣ እናቱ እሌኒ የተሳለችውን ስለትና ምኞቷን ነገረችው። ልጇም “አይዞሽ፤ እግዚአብሔር ይገልጥልሻል” በማለት አበረታታት።

ንግስት እሌኒ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ የታሪክ አዋቂዎችንና የሀገር ሽማግሌዎችን ብትጠይቅም መረጃ የሚነግራት አጣች። ኪርያኮስ የሚባሉ አረጋዊ ዘንድ ሄዳ እንድትጠይቅ ይነግሯታል፡፡ ወደ አረጋዊውም ሄዳ ስትጠይቃቸው መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ለመናገር ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ቅዱስ ያሬድ በድጓው እንደገለፀው “እሌኒ ኪርያኮስን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል የት እንዳለ ፈጥነህ ንገረኝ” ትለው ነበር፡፡ ባዶ ቤት በማሰር ውሃ የሚያስጠማ ምግብ እየሰጠች፤ እንዳይጠጣ ከለከለችው፡፡ ከውሃ ጥም የተነሳ፣ “ከሶስቱ ትላልቅ ተራሮች አንዱ ላይ እንደተቀበረ ሲናገሩ እሰማለሁ” ሲሉ ጥቆማ ሰጧት። አይሁድ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ላለመናገር ተማምለው ስለነበር፣ አረጋዊው ኪራኮስም በግልጽ ለመናገር ተቸግረው ነበር። ንግስት እሌኒም ጥበብን በመጠቀም መረጃውን ከተቀበለች በኋላ ቦታውን ለመለየት የሚረዳ መንገድ ቀየሰች።

በንጉሱ አዋጅ ህዝቡ እንጨት ይዞ እንዲሰበሰብ ተደረገ። ደመራው ተደመረ፤ እጣን ተጨመረበት፤ በሊቀ ጳጳሱ መሪነትም ጸሎት ተደረገ። የእጣኑ ጭስ ወደ ሰማይ ወጥቶ ከተመለሰ በኋላ፣ ከሶስቱ ተራሮች መካከል መስቀሉ ወዳለበት ቦታ ሰገደ። ይህንን ምልክት በመያዝ ንግስት እሌኒ ሱባኤ በመያዝ መስከረም 16 ቀን እጣን እንዲጨስ በማድረግ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ካወቀች በኋላ በማግስቱ መስከረም 17 ቀን መስቀሉን ለማግኘት ቁፋሮው ተጀምሮ መጋቢት 10 ቀን ተገኝቷል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰቀል በግራና በቀኝ አብረው ተሰቅለው የነበሩ ሁለት ሽፍቶች የተሰቀሉበትን ጨምሮ ሶስት መስቀሎች ተገኝተዋል፡፡ ከእነዚህ መስቀሎች መካከል ትክክለኛውን የክርስቶስ መስቀል የተለየው፣ በሽተኞች ሲነኩት ፈውሷል፤ ሙታንን በህይወተ ስጋ እንዲነሱ አድርጓል፡፡ በዚህም መስቀሉ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ እንዲቀመጥ አድርጋለች፡፡



ፎቶ፦ ከገፀ ድር

በአዲስ አበባ የመስቀል ደመራ በዓል በመስቀል አደባባይ ሲከበር

በእነዚህ ወራት ንግስት እሌኒ እና አጋሮቿ ታላቅ መስዋዕትነትና ድካም ከፍለዋል። የቤተ ክርስትያን አባቶች እንደሚገልፁት፣ ንግስት እሌኒ ከሮም ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ መስቀሉን ለመፈለግ የእግር ጉዞ ከመጀመሯ በፊት የህሊና ጉዞ አድርጋለች፡፡ እግዚአብሔር ሀይልና ብርሃን እንዲሆናት፣ የተደበቀው ነገር እንዲወጣ በፆሎት ለምናለች፡፡

በብዙ ጥረት ንግስት እሌኒ ካገኘችው በኋላ በዓለም ላይ ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ደስ ብሏቸዋል፤ መስቀሉንም ተከፋፍለው ወስደውታል፡፡ ስለ መስቀሉ መገኘት ሲነሳ፣ መስቀሉ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ቁርኝት፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የመስቀል በዓልን በልዩ ሁኔታ የምታከብርበትን ምክንያት ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ ግማደ መስቀሉ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ የተደረገው በአጼ ዳዊት ዘመነ መንግስት ሲሆን፤ ንጉሱ ካለፉ በኋላ ልጃቸው ዘርዓያቆብ ግሸን አምባ ላይ እንዲያርፍ ማድረጋቸውን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መስቀሉን ለማግኘት እጣን የጨሰበትና ቁፋሮ የተጀመረበት መስከረም 16 እና 17 ቀን በኢትዮጵያ ደመራ በመደመርና በማብራት፣ በዝማሬ፣ በእልልታ፣ በትርኢት፣ በደስታ በርካታ ህዝብ ወደ አደባባይ በመውጣት ተሰባስቦ በልዩ ሁኔታ የሚከበርበት ስርዓት ተዘርግቷል፡፡

የመስቀል ደመራ በዓል በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዘንድም ትልቅ ቦታ የሚሰጠው እና በታላቅ ድምቀት የሚከበር በዓል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ካህን አባ እስራኤል ጎይቶም ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት መስቀል የክርስትና እምነት የድህነት ምስጢር ማዕከል ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ሁሉ ለማዳን ደሙን ያፈሰሰበትና መስዋዕትነት የከፈለበት ነው፡፡ በሮማውያን አገዛዝ ዘመን ወንበዴ የሚባሉትን በተመሰቃቀለ እንጨት ተሰቅለው የሚቀጡበት ነበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰቀለበት በኋላ የመስቀሉ ታሪክ ተቀየረ፤ የድህነት ምልክት እንደሆነ አባ እስራኤል ያስረዳሉ፡፡

## የንግስት እሌኒ መንገድ ምን ያስተምረናል?

የክርስቶስን መስቀል ከተቀበረበት ለማውጣት ንግስት እሌኒ ከሄደችበት ርቀት፣ ካደረገችው ተጋድሎና ጥረት ብዙ የምንማረው ቁም ነገር እንዳለ የሃይማኖት አባቶች ይናገራሉ፡፡

መስቀሉን ለማግኘት ያደረገችው ጥረት፣ ድካምና መስዋዕትነት ዘላቂ ሰላም የሚገኘው በትጋት፣ በፅናት፣ በመስዋዕትነትና አንድነት መሆኑን እንደሚያሳይ አለቃ አዕምሮ ይናገራሉ፡፡

ዘላቂ ሰላምና ልማት በአንድ ጀምበር የሚመጣ አይደለም። እሌኒ መስቀሉን ለማግኘት ከመስከረም 17 እስከ መጋቢት 10 ቀን ድረስ እንደደከመች ሁሉ፣ እኛም ለሀገራችን ሰላም “ምን አገባኝ” ሳንል በትጋት መስራት አለብን። በልባችን የተቀበሩትን ፍቅር፣ አብሮነትና መቻቻል ቆፍረን ማውጣት፤ ጥላቻን፣ ዘረኝነትን፣ ‘እኔ እበልጣለሁ’ ማለትንና ጦርነትን ደግሞ መቅበር ይኖርብናል። ንግስት እሌኒ ሃይማኖቷንና የተሳለችውን ስለቷን ጠብቃ፣ ተስፋ ሳትቆርጥ ለ300 ዓመት እየተጋዘ ትልቅ ተራራ የፈጠረውን ቆሻሻ ለማስቆፈር ከመስከረም 17 እስከ መጋቢት 10 ቀን ድረስ በመልፋቷ ውጤት እንዳገኘች አለቃ አዕምሮ ገልጸዋል፡፡

አባ እስራኤል በበኩላቸው፣ ንግሥት እሌኒ ለ300 ዓመታት ተቀብሮ የነበረውን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል ለማግኘት ያደረገችው ረጅም ጉዞ፣ ትልቅ ዋጋ ያለው የመዳን ምልክት የሆነው መስቀል አፈር ውስጥ በስብሶ እንዳይቀር በመንፈሳዊ ምሪት ተነሣሥታ ያከናወነችው ነው። መስቀሉን ለመፈለግ ረጅም ጉዞ አድርጋለች፤ በፍለጋውም ወቅት በርካታ የሰው ኃይል ተሳትፏል፤ ቀላል የማይባል መስዋዕትነት ተከፍሏል ይላሉ።

“መስቀል የሰላምና የድኅነት ምልክት ነው፤ዕረፍት ያገኘንበትና የታረቅንበትም ነው። በቤታችን፣ በማኅበረሰባችንና በሀገራችን እንዲኖሩ የምንፈልጋቸው ሰላም፣ ፍቅር፣ አንድነትና ዕርቅ የመስቀሉ ምልክት የሆኑ፣ ለሕይወታችንና ለአብሮነታችን እጅግ አስፈላጊ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህን ነገሮች ስናጣ ግን እንደ ቀልድ ነው የምናጣቸው። ንግሥት እሌኒ ከሮም ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ባለመታከትና ተስፋ ባለመቁረጥ ባደረገችው ጥረት የክርስቶስን መስቀል እንዳገኘችው ሁሉ፣ እኛም ለሰላም፣ ለፍቅር፣ ለመግባባትና ሀገርን ለመገንባት ተስፋ ሳንቆርጥ በጽናት መስራት ይኖርብናል፤ ተስፋ ሳንቆርጥ እስከፈለግናቸው ድረስ የምናገኛቸው ናቸው” ብለዋል አባ እስራኤል። እንደ ሀገር በምክክር ሀገራዊ መግባባትና ዘላቂ ሰላም ለመገንባት የተደረገው ጥረት ከፍተኛ ትጋት፣ መስዋዕትነትና ፈተና ማለፍን የጠየቀ ሂደት ነው፡፡ ከስምንት ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና ልማት እንዲረጋገጥ ሀገራዊ መግባባት መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ ታዋቂ ግለሰቦችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለበርካታ ጊዜያት ሲወተውቱ ቆይተዋል። ይህ ጥያቄም ተቀባይነት አግኝቶ በሀገሪቱ ለዘመናት ሲንከባለሉ የመጡና አለመግባባትን የፈጠሩ ቁርሾዎችን በዘላቂነት ለመፍታት በታህሳስ ወር 2014 ዓ.ም ሂደቱን የሚያስተባብር ተቋም በመንግስት ተነሳሽነት እንዲቋቋም ተደረገ፡፡

በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሂደቱን በበላይነት በመምራት፤ ኢትዮጵያውያንን እንዲሳተፉ፣ አጀንዳዎች እንዲለዩና በተለዩት ነጥቦች ላይ ምክክሮች እንዲካሄዱ አድርጓል። ከሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የተወከሉ አራት ሺህ የማህበረሰብ ተወካዮች በስምንት አጀንዳዎች ላይ ሰፊ ውይይት አካሂደዋል።

የተለያየ አመለካከት ያላቸው ወገኖች በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ በመሰባሰብ፣ የችግሮቻቸውን መነሻ ምክንያት በጋራ ለመረዳትና መግባባት ላይ ለመድረስ ያደረጉት ጥረት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ሆኗል። ይህም ኢትዮጵያውያን ለረጅም ጊዜ የቆዩ ቅሬታዎችን፣ የፖለቲካ ልዩነቶችንና የታሪክ ክፍፍሎችን ከግጭት ይልቅ በሰላማዊ ምክክር ለመፍታት ትልቅ ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡

ከኮሚሽኑ የተገኘው መረጃ እንደሚያመላክተው፤ ይህ ሀገራዊ የምክክር ጉዞ ቀላልና አጭር አልነበረም። ሂደቱ ተቋም ከመመስረትና አሰራርን ከመቅረጽ ጀምሮ ባለድርሻ አካላትን መለየት፣ አጀንዳ ማሰባሰብ፣ የሕዝብ ተሳትፎና ፍትሃዊ ውክልናን ማረጋገጥ፣ አጀንዳዎችን አደራጅቶ ማዘጋጀትና በሀገር አቀፍ ደረጃ አጠቃላይ የምክክር ጉባኤዎችን እስከ ማካሄድ የደረሱ በርካታ ውስብስብና ጥንቃቄ የሚሹ ደረጃዎችን ያለፈ ነበር፡፡

ሌላው መስቀሉን ለማግኘት የተደረገው ጥረት መልካም ነገሮችን መቅበር እንደማይገባ፣ ይልቁንም የተቀበሩትን ቆፍሮ ማውጣት እንደሚገባ ያስተምራል። አለቃ አዕምሮ እንደሚገልፁት፣ መስቀሉ ከ300 ዓመታት በላይ ተቀብሮ ቢኖርም ከተቆፈረ በኋላ ተአምራት ማድረጉ አልቀረም። “በእኛም ማህበረሰብ፣ በየሰፈራችንና በየመስሪያ ቤታችን የቀበርናቸው ወርቃማ እሴቶች አሉ። ለምሳሌ፡- በሽምግልና ሰዎችን፣ ባልና ሚስትን፣ የተጣሉትን ማስታረቅና ችግሮችን በሰላም መፍታት ትልቅ ባህላችን ናቸው። እነዚህን ወርቃማ ባህሎች አለመጠቀም ማለት መቅበር በመሆኑ፣ የተቀበሩ መልካም ነገሮችን ቆፍረን ማውጣትና ለሀገር ብርሃን እንዲሆኑ ማድረግ ይገባናል” ብለዋል፡፡

አለቃ አዕምሮ እንደሚናገሩት፣ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና ልማትን ለማምጣት እያንዳንዱ ሰው የሰላም ችቦ ይዞ መውጣት አለበት፡፡ ንግስት እሌኒ ብዙ መስዋዕትነት ከፍላ፤ መጨረሻ ላይ የታየው ብርሃን፣ አንድነትና ሰላም ነው፡፡ ኢትዮጵያውያንም ትናንት ሲያጋጩን የነበሩ ነገሮችን በፍቅርና ይቅርታ በመዝጋት፣ ዛሬና ነገን አሻግረን በመመልከት መቀራረብ አለብን። በደመራ ዕለት እያንዳንዱ ሰው ችቦ ይዞ እንደሚወጣ ሁሉ፣ ለሀገራችን ዘላቂ ሰላም እና ለምክክሩ ስኬት እያንዳንዱ ዜጋ የራሱን “የሰላም ችቦ” ከልቦናው እና ከቤቱ ይዞ መውጣት አለበት። የሰላም ቃል በማውጣትና በጸሎት በመደገፍ የተጀመረው በጎ ጅምር፣ በሀገራዊ ምክክር የተገኙ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑና ሰላማችን የተሟላና ዘላቂ እንዲሆን መትጋት ያስፈልጋል፡፡

አባ እስራኤል እንደሚናገሩት፣ በመስቀል ውስጥ የሚገኘው ሰላምና ፍሬ በዋዛ የሚገኝ አይደለም፤ ይልቁንም ጽኑ ቁርጠኝነትንና ታማኝነትን ይጠይቃል። የክርስትና እምነት ከውጫዊ ምልክቶች ይልቅ የልብ ቀናነትን ይሻል። ውስጣዊ ቅንነት ሲኖረን ደግሞ ለእውነት እንቆማለን፤ ለሌሎችም የመዳን ምልክት እንሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋን እንቀበላለን።

አለቃ አዕምሮ በበኩላቸው፣ መስቀል ደመራ የተጣላና የተራራቀ የሚቀራረብበት፣ የሚታረቅበትና ማህበራዊ ትስስር የሚጠናከርበት ታላቅ በዓል ነው። ይህ በዓል ከሃይማኖታዊ ይዘቱ ባሻገር ለሀገራችን የቱሪዝም ምንጭ በመሆን በኢኮኖሚም ተጠቃሚ ያደርጋል። ይህ ታላቅ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴት ያለው በዓል በውስጡ የያዛቸው እሴቶች ተጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅሙን ማግኘት እንዲቻል የሃይማኖት ተቋማት፣ መንግስት፣ መገናኛ ብዙሃንና መላው ማህበረሰብ የድርሻቸውን መወጣት ይገባቸዋል፡፡




## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ
## የግዢ መለያ ቁጥር 01/2019 ዓ.ም

የአባይ ምንጭ ቅድመ አንደኛና የልማት ምንጭ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለ2019 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውል ከዚህ በታች በሎት በዝርዝር የተገለፁትን እቃዎች ሎት 1 የፅህፈት መሳሪያዎች፣ ሎት 2 የፅዳት ዕቃዎች፣ ሎት 3 የደንብ ልብስ፣ ሎት 4 አላቂ እና ቋሚ የቢሮ ዕቃዎች፣ ሎት 5 የቢሮ ፈርኒቸር እቃዎች፣ ሎት 6 የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፣ ሎት 7 አጋዥ መጽሐፎች፣ ሎት 8 የደንብ ልብስ ስፌት እና ሎት 9 የህትመት ስራዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በጨረታው መሳተፍ የምትፈልጉ

1. የንግድ ምዝገባ ሰርተፍኬት 2. በዘርፉ የተሰማሩበት የታደሰ የንግድ ፍቃድ 3. በአቅራቢነት ዝርዝር የተመዘገቡበት ሰርተፍኬት 4. የቫት ተመዝጋቢ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሰርተፍኬት ማቅረብ የምትችሉ ከሎት 8 ውጪ በዝርዝር ለተገለፁት እቃዎች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ናሙና ማቅረብ ወይም ማሳየት የሚችል ናሙና ማቅረብ ለማይችሉት እቃዎች በምስል የተደገፈ /ፎቶ ግራፍ/ በማቅረብ ለጨረታ ማስከበሪያ

1. ለሎት 1 የጽህፈት መሳሪያ 5000
2. ለሎት 2 የጽዳት እቃ 7500
3. ለሎት 3 የደንብ ልብስ 7500
4 .ለሎት 4 አላቂና ቋሚ የቢሮ እቃዎች 5,000
5. ለሎት 5 የቢሮ ፈርኒቸር እቃዎች 2000
6. ለሎት 6 የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች 3000
7. ለሎት 7 አጋዥ መጽሐፎች 500
8. ለሎት 8 የደንብ ልብስ ስፌት 500
9. ለሎት 9 የህትመት ስራዎች 500

በት/ቤቱ ስም በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ማሲያዝ ይኖርባችኋል፡፡ ተጫራቾች የጨረታ አሸናፊ ሆነው የተገኙባቸውን እቃዎች ከአጠቃላይ ዋጋ 10% ለውል ማስከበሪያ ማስያዝ የሚችል ማንኛውም ተጫራች ከላይ የተዘረዘሩትን ሰነዶች ዋናውን እና ፎቶ ኮፒውን በሁለት ፖስታ በማሸግ ት/ቤቱ ለእዚሁ ጨረታ ባዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ላይ በመሙላት መወዳደር የምትችሉ ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ10 /አስር /ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በአባይ ምንጭ ቅድመ አንደኛና ልማት ምንጭ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ግዢ ክፍል ለምንገዛቸው እቃዎች የተዘጋጀ የጨረታ ሰነድ የማይመለስ 200.00 ብር /ሁለት መቶ ብር / በመግዛት ከላይ በዝርዝር የተገለጸውን ሰነድ ዋናውንና ኮፒውን እንዲሁም ዋጋ የሞላችሁበትን ሰነድ በፖስታ በማሸግ ት/ቤቱ ለእዚህ ጨረታ ባዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ በማስገባት እንድትወዳደሩ ተጋብዛችኋል፡፡ ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በ10 ኛው ቀን 11፡30 ሰዓት ላይ ተዘግቶ በ11ኛው ቀን በ4፡00 ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ጨረታው ሲከፈት የማይገኙ ተጫራቾች በሌሉበት ጨረታው እንደሚከፈት እያሳወቅን የተጠቀሰው ቀን ቅዳሜ እና እሁድ እንዲሁም የበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተጠቀሰው ሰዓት ይከፈታል፡፡

**ማሳሰቢያ፡- ት/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።**

**አድራሻ፡- በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 1 ጦር ሀይሎች በመኮንኖች ክበብ 200 ሜትር ገባ ብሎ**

**ስልክ ቁጥር፡- 0113-20-03-51**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ በልደታ ክ/ከተማ ት/ጽ/ቤት የአባይ ምንጭ ቅድመ አንደኛ እና የልማት ምንጭ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት**





## የቋሚ እና የኮንትራት የሥራ የቅጥር ማስታወቂያ

የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት በቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ከፐ/ሰ/የሰ/ሀ/ል/ጽ/ቤት/10031/2018 በቀን 18/12/2018 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ሰራተኛ (ሞግዚት) እና ጽዳትና ተላላኪ በቋሚና በኮንትራት ቅጥር እንድንፈጽም አሳውቆናል፡፡

በዚህም መሰረት በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 አስተዳደር ፐ/ሰ/የሠ/ሀ/ል/ጽ/ቤት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የስራ መደቦች ላይ ሠራተኞችን አወዳድሮ በቋሚነት እና በኮንትራት መቅጠር ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከታች የተዘረዘሩ መደቦች ላይ መስፈርቱን የምታሟሉ አመልካቾች በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት መታችሁ ማመልከት የምትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

| ተ.ቁ | የስራ መደብ መጠሪያ | የስራ ደረጃ | የቅጥር ሁኔታ | ብዛት | ደመወዝ | ተፈላጊ ችሎታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሴክሬታሪ ታይፒስት I | VI | ቋሚ | 1 | 8,029 | ሴክሬተሪያል ሳይንስ፣ ሴክሬተሪ፣ ሴክሬተሪ አድምንስትሬሽን፣ ሴክሬተሪ ኤንድ ኦፊስ ማኔጅመንት ሴክሬተሪያል ማኔጅመንት፣ ሴክሬተሪያል ሳይንስ ኤንድ ኦፊስ ማኔጅመንት፣ ሴክሬተሪያል ሳይንስ ኤንድ ኦፊስ ዱይቲስ፣ አድምንስትሬቲቭ ኤንድ ሴክሬተሪያል ቴክኖሎጂ፣ አድምንስትሬቲቭ ሴክሬተሪ ፣ አድምንስትሬቲቭ ኦፊስ ሴክሬተሪ ቴክኖሎጂ፣ ኮምፒውተራይዝድ ሴክሬተሪያል ሳይንስ ኤንድ ኦፊስ ማኔጅመንት፣ ከስተመር ኮንታክት ኤንድ ሴክሬተሪያል ኦፐሬሽን፣ ማናጅመንት የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም የቴክኒክና ሙያ (10+3) ወይም በሌቭል 3፣4፣5 ደረጃ ያላት/ያለው | |
| 2. | የማህበራዊ ፍ/ቤት ሬጅስትራል | VII | ቋሚ | 1 | 8,478 | በህግ ዲፕሎማ 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት | |
| 3 | የህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ሰራተኛ (ሞግዚት) | VII | ቋሚ | 3 | 8,478 | በህፃናት አያያዝ፣ እንክብካቤ እና ተዛማጅ የሙያ መስክ ዲፕሎማ እና በሌቭል IV ያለው/ ያላት በሙያው 2 ዓመት ያገለገለ | |
| 4 | ጽዳት ሰራተኛና ተላላኪ | II | ኮንትራት | 5 | 6,365 | 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ 1 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ወይም ያላት 9ኛ ክፍል ያጠናቀቀ 3 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ወይም ያላት 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ 4 ዓመት የስራ ልምድ ያለው ወይም ያላት | |

**ማሳሰቢያ ፡-**

ከላይ የተጠቀሱትን መመዘኛ የምታሟሉ አመልካቾች የስራ ልምድና የትምህርት ማስረጃ ሲኦሲ (COC) ዋናውን እና የማይመለስ 1/አንድ/ ፎቶ ኮፒ ጋር በማያያዝ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 አስተዳደር ፐ/ሰ/የሠ/ሀ/ል/ጽ/ቤት 3ኛ ፎቅ በመምጣት መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የወረዳ 5 ፐ/ሰ/የሰ/ሀ/ል/ጽ/ቤት**

# የመዲናዋ የኪነ ጥበብ መሰናዶዎች

**በአብርሃም ገብሬ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች መካከል የአዳዲስ መጻሕፍት ህትመት፣ የመጽሐፍ ምርቃት፣ የሙዚቃ ዝግጅት እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም መረጃ ይሆንዎት ዘንድ እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጻሕፍት

የኢፌዲሪ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም የፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ወታደራዊ የህይወት ጉዞና ህይወት ዙሪያ የሚያጠነጥን መጽሐፍ ለንባብ በቃ፡፡ “ድል ቁርሱ” (ከኲየራ ወንዞች መሀል የፈለቀ የጦር ሊቅ) የተሰኘ ኢትኖግራፊ፣ የፖለቲካ እና ወታደራዊ ታሪኮችን የያዘው የፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ መጽሐፍ ባሳለፍነው ሳምንት በሸራተን አዲስ በይፋ ተመርቆ ለንባብ በቅቷል፡፡ መጽሐፉ በደራሲ በአማን ታደሰ የተፃፈ ሲሆን፣ በ355 ገፆች ተቀንብቦ ለአንባቢ ቀርቧል። የመጽሐፉ ሽያጭ ገቢው ለመከላከያ ኢኖቬሽን እና ኢንተርፕርነር ሺፕ ማዕከል የሚውል መሆኑም ተሰምቷል። መጽሐፉም በተለያዩ የመጻሕፍት መሸጫ መደብሮች ይገኛል ተብሏል፡፡

“የዘገየ ሣቅ” የተሰኘው የዶ/ር ተሾመ ሽብሬ ከልክሌ ግለ ታሪክ መጽሐፍ በይፋ ተመርቆ ለንባብ በቃ፡፡ በትናንትናው ዕለት በወመዘክር መርስዔ ሐዘን ወልደቂርቆስ አዳራሽ ውስጥ የተመረቀው የዶ/ር ተሾመ ግለ ታሪክ መጽሐፍ፣ የዶክተሩን ህይወትና በሕክምናው ዓለም ስላሳለፉት ሕይወት ይተርካል ተብሏል፡፡



ፎቶ ፦ ከገፀ ድር
ከመዲናዋ የጥበብ መሰናዶዎች በከፊል

## ወደ ሀገር ቤት የተመለሰው ታዋቂው የኦሮምኛ ሙዚቃ አቀንቃኝ

ዳዊት መኮንን እጅግ ተወዳጅ እና አንጋፋ የአፋን ኦሮሞ ሙዚቀኞች አንዱ ነው። ድምፃዊው በተለይም በ1980ዎቹ እና 1990ዎቹ እንዲሁም በ2000 ዓ.ም. መጀመሪያዎች ያወጣቸው የሙዚቃ ሥራዎቹ በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቦታ አላቸው። እጅግ ከሚታወቅበት እና አይረሴ ሥራዎቹ መካከል፡- "አጃዒባ" (Ajaaiba)፣ "ሶላኔ" (Soolanee)፣ "አን ዱፌን ጅራ" (An Dhufeen Jira) ፡- ተጠቃሾች ናቸው።

የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ተናጋሪ ባልሆነው ህዝብ ጭምር የሚታወቀው አርቲስት ዳዊት መኮንን ከ27 ዓመታት የስደት ቆይታ በኋላ በትናንትናው ዕለት ወደ ሀገሩ የተመለሰ ሲሆን፣ ለአርቲስቱ የመንግስት ሥራ ኃላፊዎች ፣ አባገዳዎች እና ሀደ ስንቄዎች እንዲሁም የሙያ አጋሮቹ እና አድናቂዎቹ በሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በመገኘት አቀባበል አድርገውለታል፡፡

## ሙዚቃ

ታዋቂዎቹ የካየን-ላብ የጃዝ ሙዚቃ ባንድ የሙዚቃ ስራቸውን ሊያቀርቡ ነው። ሃያት ሪጅንሲ ሆቴል በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል ውስጥ የፊታችን ሰኞ ምሽት የሙዚቃ ሥራቸውን ያቀርባሉ፡፡ የካየን-ላብ የጃዝ ሙዚቃ ባንድ የኢትዮጵያን የሙዚቃ ፍልስፍና ላይ ያተኮሩ የተለያዩ ሙዚቃዎችን በዓለም ዙርያ በመጫወት ይታወቃሉ፡፡ ሙዚቀኞቹ የፊታችን ሰኞ በሃያት ሪጅንሲ ሆቴል የሙዚቃ ሥራቸውን የሚያቀርቡ ሲሆን፣ የሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ታዳሚዎች ዝግጅቱ ላይ እንደሚታደሙ ይጠበቃል፡፡

አንጋፋው ሙዚቀኛ ግርማ በየነ የሙዚቃ ሥራዎቹን የፊታችን ሐሙስ እንደገና ሊያቀርብ መሆኑ ተሰምቷል። ከ1960ዎቹ አንስቶ በሙዚቃ ሥራ ውስጥ የሚገኘው ሙዚቀኛ ግርማ በየነ የፊታችን ሐሙስ መስከረም 21 ቀን 2019 ዓ.ም መስቀል አደባባይ በሚገኘው ሃያት ሪጅንሲ ሆቴል ፈንድቃ የባህል ማዕከል ውስጥ የሙዚቃ ሥራዎቹን በድጋሚ ለአድናቂዎቹ ያቀርባል። ሌላኛው አንጋፋ ሙዚቀኛ ዳዊት ይፍሩ ግርማ በየነን በኪቦርድ እንደገና አጅቦ እንደሚጫወት ተሰምቷል፡፡ ዝግጅቱ ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት ይጀምራል፡፡

## የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። በብሔራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 7፡30 “12ቱ እንግዶች” እንዲሁም በ11:30 “በር የሌለው ቤት” ቴአትሮች ይታያሉ። እሑድ ደግሞ በ7፡30 “ንጉስ አርማሕ” እንዲሁም በ11፡30 ደግሞ “እምዬ ብረቷ” ይታያሉ፡፡ ተመልካቾችም ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ“ሁሉ በጄ” መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ ደግሞ “እሳት ወይ አበባ” ዘወትር ቅዳሜ በ11፡00 ሰዓት እንዲሁም “ባልቻ አባነፍሶ” ቴአትር እሑድ በ8:00 ሰዓት የሚታዩ ሲሆን፣ ትኬቱን በኦንላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

በሌ ፍላሚንጎ በህፃናትና ወጣቶች የቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስ እሑድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት “የንባብ ከተማ” የተሰኘው አዲስ የልጆች ቴአትር ለእይታ ይበቃል፡፡ እሑድ በ8፡00 ሰዓት “ወህኒ አምባ” ቴአትር እንዲሁም 11፡30 ደግሞ “አትጥሪኝ” የተሰኙ ቴአትሮች ለተመልካች ይደርሳሉ፡፡

እንዲሁም በሀገር ፍቅር ቴአትር ረዕቡ በ11፡00 ሰዓት “አሉ” የተሰኘው አዲስ ቴአትር፣ ሐሙስ 11፡30 ሰዓት “ነገሩ አይቆምም”፣ እሑድ በ8፡00 ሰዓት ሰዴታ (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12፡00 ሰዓት “የመጨረሻው ፍርድ” ለቴአትር አፍቃሪያን ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል። ዲያግራሙ ሶስት ቋሚ አምዶች አሉት። በእያንዳንዱ አምድ ውስጥ ያሉ ቁጥሮች ድምር 17 መሆን አለበት፡፡ ማለትም የመጀመሪያው 10+7=17 ይሆናል፡፡ ቀጥሎም 9+6=17 ነው፡፡ በዚህ አመክንዮ ቀጣዩ 15+2=17 ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ የሚገባው ትክክለኛ ቁጥር “**2**” ነው፡፡




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# በሕብረ-ባሕል ያጌጠው በዓል

• እንደ መስቀል ያሉ በዓላት ለጋራ ሃገራዊ ትርክት ጉልህ ፋይዳ እንዳላቸው ተጠቁሟል



ፎቶ ፦ ከገጸ ድር
የመስቀል ደመራ የኢትዮጵያውያን የጋራ ማንነት ከሚታይባቸው በዓላት መካከል አንዱ ነው

**በአብርሃም ገብሬ**

መስቀል በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከሃይማኖታዊ ክብረ በዓልነቱ ባሻገር፣ ቋንቋና አካባቢ ሳይለይ ሕብረተሰቡን በጋራ የሚያስተሳስር የወል ሀገራዊ ዕሴት ነው፡፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በደማቅ ከሚከበሩ መካከልም ነው፡፡ ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ የመስቀል በዓል መልከ ብዙ ገጽታዎችን ይዞ ይከበራል፡፡ የተራራቁ ቤተሰቦች በዓሉን አስታክከው ይጠያየቃሉ፡፡ የተጣሉ ሰዎች እርቀ-ሰላም ያወርዳሉ፡፡ እንዲሁም ‘ልጅህን ለልጄ' የሚባባሉም አሉ፡፡ ይህ መስቀል ከሃይማኖታዊ ዳራው ባሻገር ከማህበረሰቡ ትውፊቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝቶች እንዳለው አመላካች ነው፡፡ የዝግጅት ክፍላችንም በዓሉ የኢትዮጵያዊያንን የወል እሴቶች እንዴት አቅፎ እንደያዘ የሚያሳይ አጭር ዳሰሳ አድርጓል፡፡

መስቀል ከኃይማኖታዊ በዓልነቱ ባለፈ በተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔሮች እና ብሔረሰቦች ዘንድ በባሕላዊ ይዘት ይከበራል፡፡ ይህ ኃይማኖታዊ እና ባሕላዊ ትውፊት የሚስተዋልበት በዓል የውጭ ሃገር ዜጎችን ቀልብ መግዛት የቻለም ሆኗል። መስቀል እንደ አካባቢው ባህልና ወግ መከበሩ እና በዚህ አከባበር ሂደት ውስጥ መልከ ብዙ ክዋኔዎች መስተዋላቸው ኢትዮጵያውያን አንድ የመስቀል በዓል በብዙ የባህል አውድ ውስጥ የሚያከብሩት የጋራ ዕሴታቸው ሆኗል፡፡ የጋራ ዕሴት ማለት ተመሳሳይነት የግድ የሚያንጸባርቅ ማለት እንዳልሆነ አንዱ ማሳያ የመስቀል በዓል ሕብረ ባህላዊነት ጥሩ አስረጅ ነው፡፡

ዩኔስኮ የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች በሚያስተዋውቅበት “ዩኔስኮ አይ ሲ ኤች” (UNESCO ICH) ገጸ ድር ላይ ስለ መስቀል በዓልና አከባበር አስመልክቶ በሰፈረው ጥናታዊ ጽሑፍ፣ “እንደ መስቀል ያሉ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት አብዛኞቹ ማህበረሰቦች በጋራ የሚያከብሯቸውና እርስ በእርስ የሚያስተሳስሯቸው ናቸው፡፡ በዓሉ ሀይማኖታዊ መሆኑ ቢታወቅም የተለያዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች በየራሳቸው ባህል፣ ትውፊትና እምነት አካሄድ ያከብሩታል። በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል መንፈሳዊ ይዘቱ የገዘፈ ነው፡፡ በአንጻሩ በደቡብ ኢትዮጵያ መስቀል ከመንፈሳዊ ይዘቱ በበለጠ ባህላዊ ጎኑ ልቆ ይታያል” ሲል በዓሉ ካለው ሃይማኖታዊ ፋይዳ ባሻገር በርካታ ማህበራዊ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ተመላክቷል፡፡

በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የበዓሉ አከባበር ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚከበር ይታወቃል፡፡ ሙሽሮች በብዛት ሰርጋቸው የሚፈጽሙት በመስቀል ነው፡፡ ሩቅ ይኖር የነበረ ወዳጅ ዘመድ ለመስቀል ተገናኝቶ ይጠያየቃል። ስለዚህ መስቀል የተጣሉ ሰዎች የሚታረቁበት፣ የተቸገሩ ሰዎች ድጋፍ የሚያገኙበት በዓል ነው፡፡ በአጠቃላይ መስቀል በኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ወግና ልማዱ፤ ትውፊቱና ዕሴቱ ጎልተው የሚንጸባረቁበት ዓመታዊ ክብረ በዓል ነው፡፡ ይህንን ታሳቢ በማድረግ የመስቀል በዓል አከባበር ከኢትዮጵያውያን አልፎ የዓለም ቅርስ ከሆነ ሰነባብቷል፡፡ መስቀል በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሳይንስ የትምህርትና ባህል ማዕከል (ዩኔስኮ) በዓለም ቅርስነት መዝግቦታል።

አሜሪካዊው የሶሲዮሎጂ ምሁር ዶናልድ ሌቪን (ፐ/ር) በፈረንጆቹ 2000 ለንባብ ያበቁት ‘Greater Ethiopia' የተሰኘ መጽሐፍ አላቸው፡፡ በዚህ መጽሐፋቸው የኢትዮጵያውያን የቋንቋና የአካባቢ ድንበር ሳይጋርዳቸው በጥልቅ የተሳሰሩባቸውን ዕሴቶች በጥልቀት ዳስሰዋል፡፡ ምሁሩ እንደ መስቀል ያሉ በዓላትና ክዋኔያዊ ትውፊቶች የኢትዮጵያን የወል ዕሴት በሚገባ እንደሚያሳዩ አትተዋል፡፡ በተለይም ሃይማኖታዊ በዓላትና አከባበራቸው በተለያዩ አካባቢዎች ተቀራራቢ መሆኑ ኢትዮጵያውያን በረዥም ዓመታት የገነቡት ጥልቅ ዕሴት ውጤት መሆኑን ምሁሩ ያሰምሩበታል፡፡

የባህልና ሰላም ተመራማሪ ወሰን ባዩ (ዶ/ር) የመስቀል አከባበር ኢትዮጵያውያንን በማስተሳሰር ረገድ ምን አይነት ፋይዳና አንድምታ እንዳለው ለአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል በሰጡት አስተያየት፤ የኢትዮጵያውያን የዕርስ በዕርስ መስተጋብር በስፋት ከሚንጸባረቅባቸው በዓላት መካከል ዋነኛው መስቀል ነው፡፡ የበዓሉ ታሪካዊ ዳራ መንፈሳዊ ቢሆንም ኢትዮጵያውያን የባህላቸው፣ የትውፊታቸው፣ የማኅበራዊ ዕሴታቸው አካል አድርገው ነው የሚያከብሩት፡፡ አከባበሩ ልዩ ሊሆንና የዓለምን ትኩረት ሊስብ የቻለውም በዚህ ምክንያት ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ ወሰን (ዶ/ር) ገለጻ፣ እንደ መስቀል ያሉ በዓላት የኢትዮጵያን ሕዝብ ያስተሳሰሩ እሴቶች ናቸው። ብሔርም ሆነ አካባቢን ሳይለዩ እንደ አካባቢው ሁኔታ የሚከበሩት እንደነዚህ አይነት በዓላት ሃገራዊ ፋይዳቸው እጅግ ትልቅ ነው፡፡ የማንነታችን መገለጫዎች ናቸው። በእነዚህ በዓላት አማካይነት ነው ማንነታችን ጎልቶ የሚንጸባረቀው፡፡

የቋንቋና የመልክዓ ምድር ልዩነት ሕዝቡን ሳያራርቁት በጋራ ሆኖ ሃገራዊ በዓላትን በአደባባይ እንደሚያከብር ያወሱት ወሰን (ዶ/ር)፣ ለዚህ ማሳያ መስቀል በተለያዩ የሃገራችን አካባቢዎች በደመቀ ሁኔታ መከበሩ ነው፡፡ በበዓሉ የሚንፀባረቁ ዕሴቶች ደግሞ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር አንድነቷን ጠብቃ ለረዥም ዓመታት እንድትዘቅል አድርጓታል፡፡ የቋንቋንና የብሔርን ልዩነት ተሻግረው የሚያስተሳስሩን እንደ መስቀል ያሉ በዓላት ለጋራ ሃገራዊ ትርክት ጭምር ጉልህ ፋይዳ እንዳላቸው አስገንዝበዋል፡፡

“የመስቀል በዓል አከባበር የሀገር ቅርስ ነው” ያሉት ወሰን (ዶ/ር)፣ በዓሉ የአንድ የህብረተሰብ ክፍል አሊያም የእምነት ተከታይ ብቻ አይደለም፡፡ ዩኔስኮ በዓለም የማይዳሰሱ ቅርሶች ውስጥ ሲመዘግበው ይህንን በማሰብ ነው፡፡ መንግስትም ሆነ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የመስቀል በዓል አከባበር ከሃይማኖታዊ ዳራው ባሻገር ማህበረሰቡን በማስተሳሰርና የኢኮኖሚ ምንጭ በመሆን ረገድ ፋይዳው የጎላ መሆኑን ሰፋ ያለ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መስራት ይገባል፡፡ በተለይም የተለያዩ የሃገራችን አካባቢዎች ያሉት የመስቀል በዓል አከባበሮች ጎልተው እንዲወጡ ማድረግ ቢቻል አከባበሩን ይበልጥ ሳቢና አጓጊ ያደርገዋል፡፡

የመስቀል በዓል አከባበር በየዓመቱ ሲከበር እሴት እንዲጨምር ማድረግ እንደሚያስፈልግ ምሁራን ያስገነዝባሉ። በተለይ ከከተሞች ባሻገር በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ያለው የመስቀል በዓል አከባበር ምን እንደሚመስል ማሳየት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

በአጠቃላይ የመስቀል በዓል አከባበር በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች እንደየ ወግና ልማዱ የሚከበር ታላቅ በዓል በመሆኑ ሃገራዊ አንድምታው እንደ ቀላል የሚታይ አይደለም፡፡ በዓሉ ኢትዮጵያውያን በረጅም ዘመናት ታሪካቸው ውስጥ ገንብተው ያቆዩት የጋራ ማንነት፣ ፍቅርና አንድነት ጎልቶ የሚታይበት ታላቅ የባህል ሀብታችን ነው፡፡ በዓሉ ከሃይማኖታዊ ዳራው ባሻገር ማኅበራዊ መስተጋብርን በማጠናከር፣ እርቀ-ሰላምን በማውረድና ሕብረ-ባሕላዊ ውበትን በማንጸባረቅ ረገድ ያለው ሀገራዊ ፋይዳ እጅግ የጎላ ነው፡፡ ይህንን የዓለም ቅርስ የሆነ እሴታችንን ጠብቆ ለማቆየትና ይበልጥ ሳቢ ለማድረግ፣ የዓመታዊ ክብረ በዓሉን ባህላዊና ማኅበራዊ ገጽታዎች በስፋት ማስተዋወቅና ትውልድ ተሻጋሪነቱን ማረጋገጥ የሁላችንም የጋራ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል፡፡

# በልማቱ የተገለጠው የቱሪዝም አቅም

- **የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች ባህላዊና ኃይማኖታዊ በዓላትን ከዘመናዊ መሰረተ ልማቶች ጋር በማቀናጀት ለከተማዋ ጠንካራ የቱሪዝም አቅም ፈጥረውላታል**

**በቶለሳ መብራቴ**

አዲስ አበባ ረጅም ታሪክ፣ ማህበራዊ መሰረት እና የበለፀገ ባህላዊ ሀብት ያላት የኢትዮጵያና የአፍሪካ መዲና ናት። መዲናዋ ከዚህ ስሟ ጋር በሚመጣጠነው የቅርብ ጊዜ የልማት ስራዎቿ ምቹነትን፣ ሳቢነትንና ተቀባይነትን ተጎናፅፋለች፡፡ በተለይ መስከረም ሲጠባ የሚበሰረው አዲሱ የኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ (እንቁጣጣሽ)፣ የመስቀል ደመራ፣ ኢሬቻና ሌሎች ኃይማኖታዊ እንዲሁም ህዝባዊ በዓላት የከተማዋን ነዋሪዎች ከመሰብሰባቸው ባለፈ ከየአቅጣጫው የሚመጡ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን በከፍተኛ ደረጃ ይስባሉ።

በመስከረም ወር የሚፈጠረው ይህ የማህበረሰብ እንቅስቃሴ እና የባህል ድምቀት ለከተማዋ ልዩ መንፈሳዊና ማህበራዊ ውበት ይሰጣታል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በከተማዋ በስፋት እየተተገበሩ ከሚገኙት ዘመናዊ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች ጋር ሲጣመር ደግሞ እነዚህ በዓላት ከተለመደው ባህላዊና ኃይማኖታዊ ይዘታቸው ባሻገር ለከተማዋ ኢኮኖሚ እና ለቱሪዝም መነቃቃት ግዙፍና አዲስ አቅም የመፍጠር እድላቸው እጅግ የሰፋ ሆኗል።

አሁን ባለው የከተማ ዕድገት እይታ ይህ መስቀል አደባባይን ጨምሮ ሌሎች የልማት ስራዎች የከተማዋን ሁለንተናዊ ገጽታ፣ አኗኗርና የሰለጠነ ገጽታ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ እንግዶች የሚያሳዩ ዋና መስኮት ሆነው የሚያገለግሉ ሆነዋል። ወደ መዲናዋ የሚመጡ ጎብኚዎች የበዓላቱን ስነ-ስርዓት ከመታደም ባሻገር የከተማዋን የዕለት ተዕለት የሕዝብ አኗኗር፣ ባህላዊ እሴቶች፣ የምግብና መጠጥ ባህል፣ የሙዚቃ ሀብት፣ የስነ-ሕንፃ ውበት እና የከተማዋን የተፈጥሮ ከባቢ በጥበብ የመቃኘት ፍላጎት አላቸው። በመሆኑም የበዓላት ማክበሪያ ስፍራዎችንና አደባባዮችን ከዘመናዊ የከተማ ልማት ጋር አቀናጅቶ ማልማት፣ በዓላቱን ከአንድ ቀን ጊዜያዊ ስነ-ስርዓትነት አውጥቶ ሙሉ ዓመት መጎብኘት ወደሚችሉበት ሁለንተናዊ የቱሪዝም መዳረሻ ማዕከላትነት የመቀየር አቅም አለው።

በዚህ ረገድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አማካኝነት በስፋት የተተገበሩት የኮሪደር እና ወንዝ ዳርቻ ልማቶች በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ላይ አዲስ ህይወት የዘሩ ዋና ዋና መሰረተ ልማቶች ናቸው። የኮሪደር እና ወንዝ ዳርቻ ልማቶቹ የመንገድ መሰረተ ልማቶችን ማሳመርና ማስፋፋት ብቻ ሳይሆን፣ ሰፋፊና ንጹህ የእግረኛ መንገዶችን፣ ለዕረፍት የሚያገለግሉ የሕዝብ መቀመጫዎችን፣ አረንጓዴ የዛፍ ተክሎችንና አበባዎችን፣ ዘመናዊ




ፎቶ፡- ከገጸ ድር

የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች እንደ የመስቀል ደመራ እና ኢሬቻ ያሉ የአደባባይ በዓላት ተጨማሪ ድምቀት ናቸው

የመብራት እና የመረጃ ሰጪ ምልክቶችን እንዲሁም የተለያዩ የመዝናኛ ቦታዎችን ያካትታሉ። ይህ አይነቱ የተቀናጀ የልማት ስራዎች ጎብኚዎች ከአንድ የመዝናኛ እና የንግድ አካባቢ ወደ ሌላ በእግር እየተጓዙ ከተማዋን በአቅራቢያ እንዲቃኙ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር እንዲቀላቀሉ እና በሙሉ ደህንነትና ምቾት ከተማዋን እንዲለማመዱ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። የእግረኛ መንገድ ተደራሽነት መጨመር የቱሪስቶችን የከተማ ውስጥ እንቅስቃሴ በመጨመር ለከተማዋ ቱሪስት ፍሰት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

በተመሳሳይ መልኩ የወንዝ ዳርቻ ልማቶች የመዲናዋን የቱሪዝም ገጽታ እና የአካባቢ ጥበቃ በመቀየር ረገድ ሌላ ትልቅ አቅም ሆነው ወጥተዋል። ቀደም ሲል ተዘንግተውና ለብክለት ተጋልጠው የነበሩትን የወንዝ ዳርቻዎች መልሶ በማልማት የተፈጥሮ እና የከተማ ህይወትን ማጣመር በመቻሉ፣ እነዚህ ስፍራዎች አሁን ላይ ለቤተሰብ እረፍት፣ ለባህላዊና ጥበባዊ ዝግጅቶች፣ ለፎቶ ግራፍ እና ለተለያዩ መዝናኛዎች የሚያገለግሉ ውብ ፓርኮችና የህዝብ መዝናኛዎች ሆነዋል። ይህ ደግሞ በመስከረም ወር የሚከበሩትን ታላላቅ ባህላዊና ኃይማኖታዊ በዓላት ከተፈጥሮ ውበት ጋር ማስተሳሰር የሚያስችል ልዩ ዕድል የሚፈጥር ሲሆን፣ ጎብኚዎች በዓላቱን ካከበሩ በኋላ በተፈጥሮ ተደምመው የሚያስፈልጋቸውን የዕረፍት ጊዜ እንዲያሳልፉ መንገድ ይከፍታል።

የወንዝ ዳርቻዎችንና የኮሪደር ልማቶችን ከበዓላት ጋር በስልት ማገናኘት ከቀላል የመዝናኛ ቦታነት ባለፈ ለአጠቃላይ የቱሪዝም ሰንሰለቱ የጎላ ፋይዳ አለው። ባህላዊና ኃይማኖታዊ በዓላትን ከተፈጥሮና ከከተማዋ የታሪክ ስፍራዎች ጋር ማጣመር ጎብኚዎች በከተማዋ የሚያሳልፉትን አማካይ የቆይታ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ ያራዝመዋል። ለምሳሌ፣ አንድ ጎብኚ በመስከረም ወር ወደ አዲስ አበባ ከተማ ሲገባ በበዓላቱ ላይ ከታደመ በኋላ የወንዝ ዳርቻዎችን፣ ፓርኮችን፣ ታሪካዊ፣ ሙዚየሞችን፣ የባህል ገበያዎችንና የዕደ-ጥበብ ማዕከላትን እንዲሁም ባህላዊ የምግብ አዳራሾችን በአንድ ላይ የሚያካትት የተቀናጀ የቱሪዝም ጉብኝት መስመር ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት፣ በከተማዋ የሚኖረውን ቆይታ ያራዝማል፤ ይህም ለከተማዋ ኢኮኖሚ ዕድገት ተጨማሪ አቅም ይሆናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የ2018 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እና የ2019 በጀት ዓመት ዋና ዋና አቅጣጫዎችን ለከተማዋ ምክር ቤት ባቀረቡበት ወቅት በዓመቱ 6 ሺህ ሄክታር መሬት የሚሸፍኑ 16 ኮሪደሮች እና 8 ወንዞች 59 ኪሎ ሚትር ርዝመት መልማታቸውን አውስተዋል።፡ ልማቶቹ 2 ሺህ ሄክታር አረንጓዴ ሽፋን፣ 24 የውሃ ግድቦች፣ 3 ሰው ሰራሽ ሐይቆች፣ 51 የእግረኛ ድልድዮች እና መሰል መሰረተ ልማቶችን ያካተቱ እንደሆነም መግለፃቸው ይታወሳል፡፡

ከንቲባ አዳነች በማብራሪያቸው፣ በሶስት ዙር በተከናወነው የኮሪደር ልማት ስራ የከተማዋን የትራፊክ ፍሰት ለማቀላጠፍ፣ ፅዳትና ውበትን ለመጨመር ደረጃቸውን የጠበቁ 426 ኪሎ ሜትር የእግረኛ መንገድ፣ 223 ኪሎ ሜትር የተሽከርካሪ መንገድ፣ 255 ኪሎ ሜትር የሳይክል መንገድ፣ 62 ነጥብ 4 ኪሎ ሜትር የመሮጫ ትራክ፣ 106 የህፃናት መጫወቻ፣ 162 የስፖርት ሜዳዎች በተሳካ ሁኔታ ተገንብተዋል ብለዋል።

በተጨማሪ 202 ኪሎ ሜትር የፍሳሽ እና 238 ነጥብ 4 ኪሎ ሜትር የጎርፍ ማስወገጃ መስመሮች ተዘርግተው ከተማችንን ለኑሮ ምቹና ተወዳዳሪ ማድረግ ተችሏል። 180 የመኪና ማቆሚያ፣ 205 ፕላዛዎች፣ 110 አንፊ ቴአትር፣ አሬናዎች፣ የስፖርት ፓርክ፣ የህፃናት ዓለም፣ ኢኳሪየም፣ ከ5 ሺህ 500 በላይ ሱቆች፣ በርካታ ካፍቴሪያዎች፣ ሞሎች፣ 233 የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች ጥራታቸውን ጠብቀው ተገንብተዋል፡፡

ይህም ከተማዋ ቱሪስት የሚተላለፍባት ብቻ ሳትሆን ቱሪስት የሚቆይባት ማድረግ ችሏል። በዚሁ መሰረት የሀገር ውስጥ ጎብኚ ቁጥር ከነበረበት 4 ነጥብ 1 ሚሊዮን ወደ 10 ነጥብ 5 ሚሊዮን ማድረስ ሲቻል፣ ከተማዋን የጎበኙ የውጪ ቱሪስቶች ቁጥርም ከነበረበት 123 ሺህ 489 ወደ 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ማድረስ ተችሏል። በአምስቱ ዓመት ከውጪ ቱሪስቶችም ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ይፈስ የነበረውን 5 ነጥብ 63 ቢሊየን ብር ወደ 242 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ከፍ ማድረግ ተችሏል። እንዲሁም ከሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ደግሞ ወደ 63 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ተገኝቷል ሲሉ አክለዋል፡፡

ከፍተኛ የቱሪዝም ተመራማሪ እና አማካሪ አያለው ሲሳይ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ ይህ የተፈጠረው አዲስ የቱሪዝም አቅም በከተማዋ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል። የጎብኚዎች ቁጥርና የቆይታ ጊዜ እየጨመረ ሲመጣ በቱሪዝም ዘርፍ ውስጥ የተሰማሩ አነስተኛ የንግድ ተቋማት ቀጥተኛ ተጠቃሚ ይሆናሉ። የከፍተኛና መካከለኛ ደረጃ ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች፣ የባህል እደ-ጥበብ እና አልባሳት አቅራቢዎች፣ የታክሲና የመጓጓዣ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የጉብኝት መሪዎች እንዲሁም በአካባቢው የሚገኙ አነስተኛና ጥቃቅን የንግድ ስራዎች ሰፊ የገቢና የሥራ ዕድል ያገኛሉ። በዚህም ምክንያት የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት ቀላል የከተማ ውበት ማሻሻያ ብቻ ሳይሆን፣ አጠቃላይ የከተማዋን የቱሪዝም ኢኮኖሚ የሚያነቃቃና የሚያንቀሳቅስ ዋና መሠረተ ልማት ሆኖ ያገለግላል።

እነዚህ በከተማዋ የተገነቡት የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች በራሳቸው ገለልተኛ የቱሪዝም መስህብ ባይሆኑም፣ ወደ ከተማዋ ለሚመጡ የተለያዩ ጎብኚዎች፣ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰቦች እና የስብሰባ ተሳታፊዎች ትልቅ እርካታን የሚፈጥሩ ወሳኝ የመሰረተ ልማት ማሟያዎች ናቸው ሲሉ አያለው ሲሳይ (ዶ/ር) ገልጸዋል። ከቅርብ ከተሞች እንደ አዳማ፣ ቢሾፍቱና ደብረ ብርሃን ለበዓላትና ለእረፍት የሚመጡ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችም ሆኑ በአዲስ አበባ የሚኖሩ የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶች የከተማዋን አዲስና የዘመነ ገጽታ በቅርበት እንዲመለከቱ ሰፊ ዕድል ይከፍታል።

እንደ አያለው (ዶ/ር)፣ ከተማዋ በዚህ ልክ ከተዋበችና ለቱሪስት ምቹ ከሆነች፤ የበዓላቱንና የከተማዋን የቱሪዝም አቅም ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በዲጂታል ማስተዋወቅና የመረጃ ተደራሽነት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። የበዓላት ማክበሪያ ቀናትና ቦታዎች፣ የመጓጓዣ አማራጮች፣ የቱሪስት መስህብ ስፍራዎች፣ የሆቴልና የባህል ዝግጅቶች መረጃ በቀላሉ በዘመናዊ ዲጂታል መድረኮች፣ በሞባይል መተግበሪያዎች እና በድህረ ገጾች ሊቀርቡ ይገባል። ከበዓላት በፊት በታቀደ መልኩ በሚደረጉ የዲጂታል ማርኬቲንግ ስራዎች እና በክብር በዓላቱ ወቅት በሚፈጠሩ ማህበራዊ ሚዲያ ይዘቶች አዲስ አበባን በዓለም የቱሪዝም ካርታ ላይ ቀዳሚና ተመራጭ የበዓላትና የከተማ ቱሪዝም መዳረሻ አድርጎ ማውጣት ይቻላል።

በዓላቱ የሚፈጥሩት ህብረ ቀለም፣ የከተማዋ አዲስ የውበት ገጽታና የወንዞቿ ዳርቻ ልማት በአንድ ላይ ሲዋሃዱ፣ አዲስ አበባ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የምትጎበኝ የበዓላት ከተማ ሳትሆን፣ ዓመቱን ሙሉ እንግዶችን የምትጋብዝ፣ የምታስተናግድና የምታስደስት የባህልና የታሪክ መናገሻ ለመሆን የሚያስችላትን አቅም እያሳየች ነው። መስከረም ይዞት የሚመጣው ደማቅ የባህልና የኃይማኖት በዓላት ከፈጣን የከተማዋ ገጽታ ለውጥ ጋር ሲጣመር፣ አዲስ አበባ ታሪካዊና ባህላዊ እሴቷን ጠብቃ ወደ ዘመናዊ የቱሪዝም መዳረሻነት እንድትሸጋገር ምቹ አጋጣሚ ፈጥሮላታል።

# ልጆች፡- ከመስቀል ደመራ እሴቶች ምን ትማራላችሁ?

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? ኢትዮጵያ ከምትታወቅባቸው መካከል ኃይማኖታዊ በዓላት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ዛሬ እና ነገ የመስቀል ደመራ በዓል ይከበራል፡፡ ይህ በዓል በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ማዕከል በማይዳሰስ ቅርስነት ተመዝግቧል፡፡ በዚህ ምክንያት ሀብትነቱ ከሀገር የተሻገረ የዓለም ጭምር የሆነ ነው፡፡ ይህም ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች ጎብኚዎች የመታየት እድል ማግኘት ችሏል፡፡ ልጆች፤ ይህን መነሻ በማድረግ መስቀል ደመራ ምን እሴቶች እንዳለውና ከዚህ እናንተ ልጆች ምን መማር እንዳለባችሁ ያነጋገርናቸው የኃይማኖት አባት የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡



ፎቶ፡- ከገጾ ድር
የመስቀል ደመራ በዓል አከባበር ከፊል ገፅታ

መጋቤ ሀዲስ አስተሪያ ሃይሉ እባላለሁ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ደብረ ምጥማቅ ቅዱስ ፊሊጶስ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ኃላፊ ነኝ፡፡ ልጆች፣ መስቀል ደመራ የማስታረቅ በዓል ነው፡፡ ችቦ ይዞ ማብራትን እና መዝሙር ማቅረብን ጨምሮ በተለያየ መልኩ ይከበራል፡፡

ልጆች የእድሜ፣ የፆታ... ልዩነት ሳይኖር ከዘመዶቻችሁ ከጎረቤቶቻችሁ ጋር በዓሉን ስታከብሩ ማህበራዊ እሴታችሁ ይዳብራል፡፡ ይህን ደግሞ ዕርስ በዕርስ በመዋደድ፣ ለማንኛውም ነገር አንድ በመሆን በተግባር ማሳየት አለባችሁ፡፡

መስቀሉ የሚያስተምረን ትንንሽ ችቦዎች ተሰባስበው በመብራት ብርሃንን አጉልተው ያሳያሉ፡፡ ልጆች፣ እናንተ ደግሞ "ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ" እንደሚባለው አንድ ሆናችሁ መስራት የማትችሉትን ነገር በጋራ ሆናችሁ ከሰራችሁ ውጤታማ እንደምትሆኑ ያስተምረናል፡፡

ሌላኛው የመስቀል ደመራ እሴት ፍቅርና ይቅርታ ነው፡፡ እናንተም ከጓደኞቻችሁ፣ ከጎረቤቶቻችሁ እንዲሁም ከቤተሰቦቻችሁ ጋር በፍቅር በመዋደድ በመረዳዳት እሴቶቹን በተግባር ማሳየት አለባችሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዓሉ የምስጋና ነው፡፡ እናንተ በመዝሙር በፀሎት ፈጣሪያችሁን እንደምታመሰግኑት ሁሉ፣ የተለያዩ ነገሮችን የሚያደርጉላችሁን ሰዎች ማመስገን፣ ለእነሱም ታማኝና እውነተኛ መሆን ይገባችኋል፡፡

ባህልን ማክበርና መጠበቅ የበዓሉ ሌላኛው እሴት ነው፡፡ ባህላዊ አልባሳትም ይሁኑ ሌላ ቦታ የምትለብሷቸው ልብሶች

የሀገራችሁን ባህል፣ ታሪክና ልማድ የተከተሉ መሆን አለባቸው፡፡ እንደ መሰልጠን እየተቆጠሩ ልብሶችን ባለመልበስ በህይወታችሁ በሥነ ምግባር ታንፃችሁ መኖር አለባችሁ፡፡

ልጆች የነገ ሀገር ተረካቢ እንደመሆናችሁ ባህሉን፣ እሴቱንና ወጉን ተከትላችሁ ከትውልድ ትውልድ ማስተላለፍ መቻል ይጠበቅባችኋል፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ ኃይማኖታችሁ የሚያዝዛችሁን ነገሮች ተግባራዊ አድርጉ። ከመጥፎ ሥነ ምግባር መጠበቅ፤ በቤታችሁና በትምህርት ቤታችሁም ለሌሎች አርዓያ መሆን ይኖርባችኋል፡፡

መስቀል ፍቅርን፣ አንድነትን፣ መተባበርን፣ ይቅርታን፣ ባህል መጠበቅን የሚያስተምር በዓል ነው። ስለዚህ ልጆች በዓሉን በደስታ ከማክበር በተጨማሪ ከውስጡ የሚገኙትን መልካም እሴቶች በዕለት ተዕለት ሕይወታችሁ ልትተገብሩት ይገባል፡፡ መልካም የመስቀል ደመራ በዓል ይሁንላችሁ፡፡

## መስከረም



የመስከረም ወር በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር የዓመቱ መጀመሪያ እና አዲስ ተስፋ የሚበሰርበት ልዩ ወር ነው። መስከረም ከሌሎቹ ወራቶች በታሪክ፣ በተፈጥሮአዊ ይዘት እና በባህላዊ እሴቶቹ እጅግ ተለይቶ ይታወቃል።

የመስከረም ወርን ከሌሎች ወራቶች ልዩ ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ የዘመን መለወጫ(ርዕሰ ዐውደ ዓመት) መሆኑ ነው። ዓለም በጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር ጥርን መጀመሪያ ሲያደርግ፣ ኢትዮጵያ ግን ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ዑደታቸውን የሚጀምሩበትን መስከረምን ትመርጣለች።

የቀንና የሌሊት እኩልነት፡ በዚህ ወር (በተለይ ከመስከረም አጋማሽ ጀምሮ) ፀሐይ በምድር ወገብ አቅራቢያ ስለምትሆን ቀንና ሌሊት እኩል 12 ሰዓት ይሆናሉ። የተፈጥሮ መታደስና የክረምት መውጫ፤ የሦስት ወራቱ ከባድ የክረምት ዝናብና ጨለማ አልፎ ምድር በአደይ አበባ የምታጌጥበት፣ ወንዞች የሚጠሩበት እና ለምለም አረንጓዴነት የሚታይበት የወቅቱ (የመጸው) መጀመሪያ ነው።

የደማቅ ባህላዊና ኃይማኖታዊ በዓላት ማዕከል፤ መስከረም የብዝኃነት ውበት የሚታይበት ወር ነው። በዩኔስኮ የተመዘገበው የመስቀል ደመራ በዓል፣ የኦሮሞ ሕዝብ የምስጋና በዓል የሆነው ኢሬቻ፣ የሀድያ ሕዝብ ዮሆ፣ የዎላይታ ሕዝብ ጊፋታ እና ሌሎችም በርካታ የዘመን መለወጫ በዓላት የሚከበሩት በዚህ ወር ነው።

መስከረም የእሸትና የጥጋብ ወቅት መሆኑም በግብርናው ዘርፍ አዝርዕት አድገው ማሸት የሚጀምሩበት፣ አርሶ አደሩና እንስሳት ከክረምት መከራ ወጥተው ወደ ፍሬና ጥጋብ የሚሸጋገሩበት የምሥራች ወር ነው።

**ምንጭ፡- ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች**

# 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ሊሰርቅ ሲመጣ በስውር፤ ሰርቆ ሲወጣ በግርግር**

**መልስ፡- ሐ. ሞት**

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ሲወለድ የሚጠቁር፤ ሲያረጅ የሚቀላ**

ሀ. ቃሪያ
ለ. በርበሬ
ሐ.ሚጥሚጣ

**ልጆች፤ መልሱን ከጓደኞቻችሁ እና ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ተወያዩበት።**

MIDROC INVESTMENT GROUP
ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ

ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችሁ!
እያለ መልካም ምኞቱን ይገልፃል!

ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በማኒፋክቸሪንግ፣ በግብርና፣ በማዕድን፣ በንግድ ፣ በሆስፒታሊቲ እንዲሁም በኮንስትራክሽንና ሪል እስቴት ዘርፎች የተደራጁ 45 ኩባንያዎችን ያቀፈና ከ80 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር የቻለ ተቋም ነው። ማህበራዊ ኃላፊነቱንም ለመወጣት ከትርፉ 10 በመቶውን በመመደብ እየሰራ ይገኛል። በተለያዩ አከባቢዎች ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ተቋማትን፣ መንገድ፣ ንጹህ ውሃ፣ የወንዝ ዳር ልማት፣ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታና ሌሎች ስራዎችን እየሰራ ዜጎችን ተጠቃሚ አድርጓል።
ወደፊትም ለሀገራችን የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ አጠናክሮ ይቀጥላል።

መልካም የመስቀል በዓል ይሁንላችሁ!
ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ-የሀገር ሀብት

እንኳን
ለብርሃነ መስቀሉ
አደረሳችሁ!




## የቅጥር ማስታወቂያ

### የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ልዩ ሙያዎች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | ብዛት | የቅጥር ሁኔት | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ለቴሌቪዥን ዘርፍ** | | | | | | | | |
| 1 | የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን አቅራቢና አዘጋጅ | ዲግሪ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ ሆኖ በቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ ልዩ ችሎታ እና ክህሎት ያላቸውን ወጣቶች | በዘርፉ ልምድና ክህሎት ያላችሁ እንዲሁም ሞዴል አርቲስቶች ጭምር መሳተፍ ይችላሉ | በማንኛውም የትምህርት መስክ የተለያዩ ዓለም አቀፍም ሆነ ሀገራዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በብቃት የመተንተን፤ የማዘጋጀት እና የማቀነባበር ተሰጥኦ ያለው/ያላት እንዲሁም መደበኛ ቴሌ ፕሮምፕተር ከማንበብ ባለፈ ፕሮግራሞችን በእንቅስቃሴ እና በፈጠራ ማቅረብ የሚችል/የምትችል፤ በተለያዩ አግባቦች የተሰሩ የታለንት ወይም የፕሮግራም አቀራረብ ስራዎች ማቅረብ ላይ ልዩ ተሰጥኦ ያለዉ/ያላት | 4 | በታለንት ግዢ | በተቋሙ አሰራር እና ስምምነት | አ/አ |
| 2 | የቴክኖሎጂ ፕሮግራም አቅራቢና አዘጋጅ | ዲግሪ/ሁለተኛ ዲግሪ ሆኖ በቴሌቪዥን ቴክኖሎጂ ፕሮግራም ላይ ልዩ ችሎታ እና ክህሎት ያላቸውን ወጣቶች | ዜሮ ዓመት የስራ ልምድ ሆኖ | ኮምፒውተር ሳይንስ፣ ኮምፒውተር አፕሊኬሽን፣ ሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ፣ ኮምፒውተር ኢንጂነሪንግ፣ አርቴፊሻል ኢንተለጀንሲ፤ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም፣ በቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን አቅራቢ(Host) ሆስት ማድረግ ላይ ልዩ ተሰጥኦ ያለዉ/ያላት በተለያዩ አግባቦች የተሰሩ የታለንት ወይም የፕሮግራም አቀራረብ ስራዎችን (showreel/portfolio) ማቅረብ እና ማሳየት የሚችል | 1 | በታለንት ግዢ | በተቋሙ አሰራር እና ስምምነት | አ/አ |

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. አመልካቾች ያላቸውን ታለንት ወይም የፕሮግራም አቀራረብ ስራዎችን (showreel/portfolio) ማቅረብ እና ማሳየት የሚችሉ መሆን አለበት፡፡
4. ለቴሌቪዥን ፕሮግራም በሚመጥን መልኩ በብቃት የመተንተን፤ የማብራራት እና የማዘጋጀት ልዩ ተሰጥኦ ያለዉ/ያላት
5. የምዝገባው ቀን ከመስከረም 19 ቀን 2019 ዓ.ም እስከ መስከረም 30 ቀን 2019 ዓ.ም ድረስ
6. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
7. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስተ ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111551848

**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**




የኔሸት ፅምሩ ሃ/ማርያም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 1 የሚገኘው ካርታ / የይዞታ ልዩ መለያ/ ቁጥር AA000080117217 ሴሪ ቁጥር 0159198 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወረዳ 12 ፀሀይ ከበደ ሞገስ ስም የተመዘገበ ይዞታ የይዞታው ልዩ መለያ ቁጥር AA000051203762 የተሰጠበት ቀን 04/11/2011 ዓ/ም የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካፖ/ለ/ቀ/15/32/2/19 በቀን 11/01/2019 ዓ.ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አምልክተዋል፡፡

ይህን በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ የሚል በ90 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ምትክ ሰርተፊኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር 045429 ሴሪ ቁጥር 1516130 ሰብለ ምንዳ አድገህ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንዶሚንየም ቤት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸው ተደራጅቶ በመመሪያው መሠረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የይዞታ መለያ ቁጥር ሴሪ ቁጥር 008435 ይዞታ መለያ ቁጥር ቦሌ10/16/5017/00 ስም ሸዋዬ ኢለላ ጭጭሶ በተቋማችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን እስከ 30 ቀን ድረስ በጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ /ሰርተፊኬት/ እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አቶ ተስፋዬ አስፋው ባንቴ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 የይዞታ ልዩ መለያ AA000060300829 ሴሪ ቁጥር R 017300 ሴሪ ቁጥር የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር 529 በእነ ሄኖክ ኃይለማርያም 5(አምስት)ሰዎች ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ተነፃፃሪ የጋራ መኖሪያ ቤት ባለቤትነት ካርታ ቁጥሩ ወ12/ውዝ01/612/14710/00 የተሰጠበት ቀን 26/1/2006 ዓ/ም የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 12/01/2019 ዓ/ም ይህንኑ የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ በ 30 ቀን ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**<u>ጉዳዩ፡- የደረሰኝ መጥፋትን ማሳወቅ</u>**

በአዲስ አበባ ክልል የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 39 እና 40 4ተኛ ፎቅ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0003161018 የሚታወቀው ባዩስ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ቢዝነስ ኮሌጅ ኃ/የ/የግል/ማህበር በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ---- አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ያልተሰራበት የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 19651 እስከ 20000 ስለጠፋብን በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑ የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው --------- /ምዕራብ/ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ የሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡-ባዩስ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ቢዝነስ ኮሌጅ ኃ/የተ/የግል ማህበር**

ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የቢሮው የቴክኖሎጂ ልማት ተቋማትን በምን ልክ እያገዘ ነው?

**በደረጀ ታደሰ**

ትላንት ዛሬ አይደለም፡፡ ዛሬም በነገ ይተካል፡፡ ይህ የጊዜ ተፈጥሯዊ ዑደት ውጤት ነው፡፡ በጊዜ ዑደት ውስጥ ሁሉም ነገር ይለዋወጣል፡፡ የሠው ልጅ የሥልጣኔ ዕድገት ደረጃም በጊዜ ዑደት ውስጥ እንደ ወንዝ ሲፈስስ ኖሯል፤ ይኖራልም። ትላንት የድንጋይ ዘመን፣ የብረት ዘመን፣ የኢንዱስትሪ ዘመን በመሳሰሉ የሥልጣኔ ምዕራፎች አልፎ ዛሬ ላይ ደርሷል። በማያቋርጥ የአዲስ ነገር መሻት ጸጋ ተሞልቶ የተፈጠረው የሠው ልጅ፣ በረቀቀ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፈጠራው ታግዞ ዓለምን የቴክኖሎጂ ዘመን ላይ አድርሷታል፡፡ ነገ ደግሞ ከዛሬ የተሻለ እና አዲስ መልክ ያለው ሁኔታ እንደሚፈጠር ይጠበቃል፡፡

ቴክኖሎጂ የበላይነትን በያዘበት በዚህ ዘመን አጀንዳዎች በቴክኖሎጂ ላይ ሊያተኩሩ የተገባ ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍም የዝግጅት ክፍላችን ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጎራ በማለት፤ ከተቋሙ ሠፊ ተግባርና ኃላፊነት ውስጥ አንዱን ቅርንጫፍ ለመመልከት እንሞክራለን። ለዛሬው የመረጥነው የተቋሙ አንድ ዘርፍ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት እና የሶፍትዌር ሲስተም ልማት ነው፡፡ ይህ ዘርፍ ወይም ክፍል ከተቋሙ ባሻገር በከተማዋ ስሉጥነት (የስማርት ሲቲ) ዕድገት ውስጥ አይተኬ ሚና እንዲወጣ ይጠበቃል፡፡ በዚሁ መሰረት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት እና የሶፍትዌር ሲስተም ልማት ዘርፍ የሠራቸውን ሥራዎች፣ ያስገኛቸውን ውጤቶች እና መሰል ነጥቦችን ለሚመለከተው አካል በማንሳት ምላሽና ማብራሪያ እንዲሰጥ አድርገናል፡፡

አቶ ብርሃኑ ሚካኤል፤ በቢሮው የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ዲዛይንና ግንባታ ዳይሬክተር ናቸው፡፡ እሳቸው የሚመሩትና የሚያስተባብሩት ክፍል በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ትግበራ አኳያ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማትን እና የሶፍትዌር ሲስተም ልማትን የማሻሻል እና የማስፋፋት፣ የመጠገን እንዲሁም አዲስ የመገንባት ተግባራትን ያከናውናል። ለተግባራቱ ተፈጻሚነትና ስኬት የውስጥ እና የውጭ አቅምን ይጠቀማል፡፡

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ
Innovation and Technology Development Bureau

አዲስ አበባ በፈጣን ዕድገት ላይ ትገኛለች፡፡ ዕድገቷ ዘመኑን የዋጀ፣ የዓለምን ተሞክሮ ያገናዘበ፣ ሥምና ግብሯን የመጠነ፣ ለነዋሪዎቿ እና ለእንግዶቿ የተመቸች... እንዲሆን ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷል። ይህ ከተማዋን ስሉጥ ከተማ (ስማርት ሲቲ) የማድረጉ ጥረት አንዱ ማሳያ ነው። ለዚህ ደግሞ የስሉጥ ከተማ ወሳኝ አቅም የሆነውን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት እና የሶፍትዌር ሲስተም ልማት ላይ ውጤታማ ሥራ መሥራት ይገባል። በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ዲዛይንና ግንባታ ዳይሬክቶሬት፣ በጥናት ላይ በመመስረት የተለያዩ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶችን በማልማት ለአገልግሎት ማብቃቱን አቶ ብርሃኑ አስረድተዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ሥራ የሚጀመረው በጥናት ተመስርቶ ነው። የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ጥያቄ ወዳቀረቡና ቅድሚያ ወደተሰጣቸው ተቋማት፣ ከቢሮው የተመደቡ ባለሙያዎች እና በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ካሉ ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ የባለሙያዎች ቡድን ወደ ቦታው ከደረሰ በኋላ፤ ጥልቅ ጥናት በማድረግ የፍላጎት ልየታ ያደርጋሉ፣ ዲዛይኖች ይሠራሉ፣ ሰነዶች ይዘጋጃሉ። የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ጥያቄ ያቀረበው ተቋም ጥያቄዎቹ የሚመለሱበትን አቅም (ማለትም፡- በውስጥ አቅም ወይም በፕሮጀክት ተይዘው ከአልሚ ድርጅቶች ጋር የሚተገበሩ) መሆናቸውን ይወስናል፡፡

"የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ዲዛይንና ግንባታ ዳይሬክቶሬት በጥናት ላይ የተመሰረተውን ትግበራ ለማከናወን በቢሮው ያለውን የሠው ኃይል እና ግብዓት ይጠቀማል፡፡ ከውስጥ አቅም በላይ ሲሆን ትግበራው በውጭ አቅም እንዲከናወን ይደረጋል፡፡" ያሉት አቶ ብርሃኑ፤ በተለይ ሥራውን ለመተግበር ከውጭ የሚመጡ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ግብዓቶች (ፋየርዎል፣ ራውተር፣ ስዊች፣ ሰርቪሊያንስ ሲስተሞች...) አስፈላጊ ሲሆኑ፤ ተግባራቱን በፕሮጀክት በመያዝ እና አልሚ ድርጅቶችን በመጋበዝ ተፈፃሚ እንደሚደረጉ ገልጸዋል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ፣ በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ዲዛይንና ግንባታ ዘርፍ በተከናወኑ ተግባራት ላይ የውስጥ አቅምን በተሻለ ደረጃ ለመጠቀም ጥረት እየተደረገ መሆኑን የክፍሉ ዳይሬክተር አቶ ብርሃኑ ተናግረዋል፡፡ ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ የተሠሩ ሥራዎችን በምሳሌነት ጠቅሰዋል። ከዘረዘሯቸው ተጨባጭ ሥራዎች መካከል፡- የኔትዎርክ መሰረተ ልማት ዝርጋታ (የአዲስ አበባ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ቀድሞ ይጠቀምበት በነበረው ሕንጻ፣ የከነማ ፋርማሲ 45 ቅርንጫፎች፣ በየካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ፣ በአዲስ አበባ የህዳሴ ግድብ ማስተሳሰሪያ ጽህፈት ቤት ...) ይገኙበታል፡፡

በተጨማሪም፤ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማና በስሩ ያሉ ወረዳዎች የኔትዎርክ መሰረተ ልማት ዝርጋታ እና ካሜራዎች፣ ስዊቾች፣ ኬብሎች የመሳሰሉ ግብዓቶች ድጋፍ እና ገጠማ የተከናወነው በውስጥ አቅም ነው፡፡ የወንዝ ዳርቻ ልማት ሰርቪሊያንስ ሲስተሞች ድጋፍ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ሰርቪሊያንስ ሲስተሞች ዝርጋታ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ፣ ፋይናንስ ቢሮ ሲስተም ፍተሻ የተከናወነው በራስ አቅም ነው፡፡

በመዲናዋ የሚገኙ መንግስታዊ ተቋማት ለህብረተሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ፈጣን፣ ወጪ ቆጣቢ እና ፍትሐዊ እንዲሆኑ የሚያግዙ ሶፍትዌሮችን አልምቶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የተገነባው የውስጥ አቅም የማይተካ ሚና መጫወቱን አቶ ብርሃኑ አረጋግጠዋል፡፡ ከሶፍትዌር ልማት ጋር በተያያዘ ከተከናወኑ በርካታ ውጤታማ ሥራዎች መካከል፡- የንብረት አስተዳደር ሲስተም (ለአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ለምቶ በከተማ አስተዳደሩ ስር በሚገኙ 456 ተቋማት ላይ ተግባራዊ የተደረገ)፣ ፋይል ማኔጅመንት ሲስተም (ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት) አገልግሎት የዋለ፣ የክሊኒካል ማኔጅመንት ሲስተም (ለእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን)፣ የቦንድ ማኔጅመንት ሲስተም (ለህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት) በማሳያነት ዘርዝረዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽህፈት ቤትን ጨምሮ ለወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ ለስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና ለሌሎች ተቋማት የገጸ ድር (ዌብሳይት) ልማት ተተግብሯል፡፡

ከላይ የተጠቃቀሱት እና መሰል ተግባራት ለአዲስ አበባ ከተማ ዘመናዊነትን የተላበሰ ዕድገት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ሥራዎቹ፤ በተለያዩ የመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ በማዘመን ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለው፣ ወጪ ቆጣቢና እና ምቹ እንዲሆኑ አስችሏል፡፡ በዚህም የተገልጋዮች እርካታ እያደገ መጥቷል፡፡ የደህንነት ካሜራዎች እና ተያያዥ ቴክኖሎጂዎች መገጠማቸው የተቋማትን የምድረ ግቢ ደህንነት እንዲጠበቅ፣ በተቋማቱ ውስጥ ያለው አሠራር ግልጸኝነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን አግዟል፡፡ ሌብነትን እና መሰል ብልሹ አሠራሮችን ቀንሷል፡፡ ውስን ሃብትን በጋራ ለመጠቀም አስችሏል፡፡

የአዲስ አበባን የዕድገት ጉዞ ከዚህም በላይ የተፋጠነና በዓለም ከሚገኙ ስሉጥ ከተማች (ስማርት ሲቲስ) አንዷ እንድትሆን ለማስቻል የተጀመሩትን ውጤታማ ሥራዎች አጠናክሮ መሄድ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የሁላችን መዲና ለሆነችው አዲስ አበባ ሁሉም የራሱን ጡብ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡ ነዋሪው፣ ተቋማትና ባለሃብቶች ከከተማ አስተዳደሩ ጋር እንደሁልጊዜው ሁሉ ተቀናጅተውና ተባብረው ለውጤት የሚያበቃቸውን መንገድ አጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡

ከዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# የኮሌጁ የበጎነት አሻራ

• የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመማር-ማስተማርና የምርምር ተግባሩን ከበጎ አድራጎት ጋር በማጣመር አርአያነት ያለው አስተዋፅኦ እያበረከተ እንደሚገኝ ተጠቁሟል

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

በጎ ፈቃደኝነት የግለሰቦች መልካም ምኞትና በጎ ፈቃድ ብቻ ሳይሆን፣ ተቋማዊ መዋቅርና ዘመናዊ እውቀትን ሲታጠቅ የላቀ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ግዙፍ አቅም ነው። የተለያዩ ተቋማት ያላቸውን ቁሳቁሳዊ፣ የሰው ኃይል እና የሙያ ብቃት በማስተባበር ወደ ማህበረሰብ አገልግሎት ሲሰማሩ ዘላቂና ተጨባጭ ውጤት ማስመዝገብ ይችላሉ። በተለይም የሕክምና እና ትምህርት ተቋማት የሚያደርጓቸው ዘርፈ-ብዙ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች የማህበረሰቡን መሰረታዊ ፍላጎቶች ከመመለስ ባሻገር፣ አገራዊ የጤና እስትራቴጂዎችን ለማሳካትና ማህበራዊ ፍትሕን ለማረጋገጥ የሚጫወቱት ሚና የጎላ ነው።



ፎቶ፡- ከገፀ ድር
የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በዓመቱ ውስጥ ከተሳተፈባቸው የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች መካከል ጥቂቶቹ

በዚህ ተግባር ላይ ተሰላፊ በመሆን ደማቅ አሻራውን እያሳረፈ የሚገኘው የዳግማዊ ምኒልክ የሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ዘርፈ-ብዙ ማህበራዊ ተጠቃሚነቶችን እያረጋገጠ ይገኛል። ኮሌጁ የሕክምና፣ የትምህርትና የምርምር ማዕከልነቱን ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር በማጣመር የጤና አገልግሎት ተደራሽነታቸው አነስተኛ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል። በየጊዜው በሚያዘጋጃቸው የነፃ ሕክምና ዘመቻዎች፣ የዓይን ሕክምናና ቀዶ ህክምናዎች፣ የደም ልገሳ እና የጤና ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች አማካኝነት በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖችን ሕይወት የመታደግ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከተጣለባቸው ሀገራዊ ኃላፊነት አኳያ 60 በመቶ የመማር-ማስተማር፣ 15 በመቶ የጥናትና ምርምር፣ እንዲሁም 25 በመቶ የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን እንዲያከናውኑ እንደሚጠበቅባቸው መረጃዎች ያመላክታሉ። የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ይህንን ፖሊሲያዊና ሰው-ተኮር የመንግስት አቅጣጫ በመከተል የተጣለበትን ማህበራዊ ኃላፊነት በተግባር እየተወጣ ይገኛል።

የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ቺፍ ሪሰርች ክሊኒካልና ኮሚኒቲ ሰርቪስ ዳይሬክተር ዶክተር ፍቅርተ ወልደስላሴ እንደሚገልጹት፤ ተማሪዎች በንድፈ-ሐሳብ ከተማሩ በኋላ የክሊኒካል ልምምድና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን በስፋት ያከናውናሉ። የኮሌጁ ተማሪዎች፣ መምህራንና የኮሌጁ የአስተዳደር ሰራተኞች የተለያዩ ማህበረሰብ አቀፍ ተግባራትን ይተገብራሉ። ስራዎቹም በቀጥታ ማህበረሰቡ ውስጥ በመግባት ችግሮችን በጥናትና በምርምር በመለየት በእውቀት፣ በጉልበት፣ በሃብት ማሰባሰብና በኮሌጁ ሙሉ አቅም የሚከናወኑ ናቸው።

ኮሌጁ አቅም ለሌላቸውና የሕክምና አገልግሎት ተደራሽነት ለሚያንሳቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ትኩረት በመስጠት በርካታ የበጎ ፈቃድ ተግባራትን አከናውኗል፤ በቀጣይም አጠናክሮ ለማስቀጠል አቅዷል ያሉት ዶክተር ፍቅርተ፣ በተለያዩ ዓለም አቀፍ የጤና ቀናት (ለምሳሌ፡ የካንሰር፣ የስኳር፣ የልብ ቀናት) ሕብረተሰቡ ነፃ የደም ግፊት፣ የስኳርና የሰውነት ክብደት ምርመራ እንዲያገኝ ይደረጋል። በተጨማሪም ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙና ለጎዳና ተዳዳሪዎች ነፃ የመድኃኒትና የሕክምና ቁሳቁስ ድጋፎች ከተለያዩ ረዳት ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይቀርባሉ። በቅርቡም በገላን ጤና ጣቢያ አካባቢ ለሚገኝ ክሊኒክ የደም ግፊት መመርመሪያ ማሽንና ልዩ ልዩ ግብአቶችን በማሟላት ለሕግ ታራሚዎች የመጀመሪያ እርዳታ ተሰጥቷል ብለዋል።

በኮሌጁ መገኛ አካባቢ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ ተማሪዎች የደብተር፣ የብዕርና የደንብ ልብስ ድጋፍ ይደረጋል። የሴት ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታ መቅረት ለመቀነስና የወር አበባ ንፅህና አጠባበቅ ግንዛቤን ለማሳደግ የሞዴስ (የሴቶች ንፅህና መጠበቂያ) ድጋፍና ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች ይሰጣሉ።

> “የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ነፃ የሕክምና አገልግሎቶች፣ የትምህርት ቁሳቁስ እና የንፅህና መጠበቂያ ድጋፎች፣ የደም ልገሳ እንዲሁም ለአረጋውያንና ለተቸገሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ባደረጋቸው ድጋፎች በርካታ ዜጎችን ተጠቃሚ አድርጓል”

ተላላፊ ስላልሆኑ በሽታዎች (የልብ፣ ካንሰር፣ ስኳር)፣ ስለ እናቶችና ሕፃናት ጤና አጠባበቅ፣ እንዲሁም ስለ አዕምሮ ጤናና የመጀመሪያ እርዳታ አሰጣጥ በትምህርት ቤቶችና በማህበረሰብ ደረጃ ሰፊ ግንዛቤ ይፈጠራል። በተጨማሪም 90 በመቶ የሚሆነው የከተማዋ ማህበረሰብ የአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥሮችን እንደማያውቅ በጥናት በመለየቱ፣ ቁጥሮቹን የያዙ ባነሮች በከተማዋ ልዩ ልዩ አካባቢዎች እንዲለጠፉ ተደርጓል።

እንደ ዶክተር ፍቅርተ ገለፃ፣ በድንገተኛ አደጋና በወሊድ ምክንያት ደም ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ሕይወት ለማዳን ከብሔራዊ ደም ባንክ ጋር በመተባበር ተከታታይ ዘመቻዎች የሚካሄዱ ሲሆን፣ በቅርቡም 30 ዩኒት ደም ተለግሷል። በተጨማሪም ወደ ጤና ተቋማት የሚመጡ ታካሚዎችና አስታማሚዎች ከብርድ፣ ከፀሐይና ከንፋስ የሚከለሉባቸውና ነፃ ሆነው የሚያርፉባቸው ማቆያ ቦታዎች ተገንብተዋል።

አቅመ ደካማ አረጋውያንን በመለየት፣ እንዲሁም ለጌርጌስኖን የአዕምሮ መርጃ ማዕከል የአልባሳት፣ የምግብ ቁሳቁስ፣ የማዕድ ማጋራትና የበዓላት መደገፊያ ድጋፎች መደረጋቸውን ያስታወሱት ዶክተር ፍቅርተ፣ የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎትም በየዓመቱ በስፋት የሚከናወን ሲሆን፤ የተማሪዎች፣ የመምህራንና የሐኪሞች ቡድን በማደራጀት አካባቢን የማፅዳትና የፅዳት ዘመቻዎች ሲከናወኑ መቆየታቸውን ገልፀዋል፡፡

በቀጣይም በ11ዱም ክፍለ ከተሞች ባሉ አካባቢዎች መፀዳጃ ቤቶችን የማደስ፣ በማረሚያ ቤቶች ስለ ግልና አካባቢ ንፅህና አጠባበቅ እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ አሰጣጥ ትምህርት የመስጠት እቅድ መያዙን ዶክተር ፍቅርተ አክለው ገልፀዋል፡፡

በተጨማሪም የቅድመና ድህረ-ወሊድ ክትትል፣ የቅድመ-መደበኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንን የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና እርዳታ አሰጣጥ ላይ ማሰልጠን፣ እንዲሁም በከተማዋ 30 በመቶ በሚሆኑ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችንና የማህበረሰብ አንቂዎችን የማሰልጠን ስራዎች በጥናት ተለይተው ሊተገበሩ የተያዙ አቅጣጫዎች ናቸው።

የዳግማዊ ምኒልክ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመማር-ማስተማርና የምርምር ስራውን ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር በማጣመር እያከናወነ ያለው የበጎ ፈቃድ አድራጎት ተቋማዊ ኃላፊነትን ከመወጣት ባለፈ የበርካታ ዜጎችን ሕይወት እያደሰ ይገኛል። ኮሌጁ ይህን ተግባሩን አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን፣ ሌሎች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም ይህንን አርአያነት ያለው ተቋማዊ የበጎ ፈቃድ አሰራር ሊከተሉት የሚገባ መልካም ተሞክሮ ነው።

# “በበዓላት ጭምር ለሌሎች ደስታ አለኝታ መሆኔ ልዩ ስሜት ይሰጠኛል”

**በእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የአራዳ ቅርንጫፍ አደጋ ምላሽ ቡድን መሪ ትዕግስት ተክለአብ**

**በለይላ መሀመድ**

ወይዘሮ ትዕግስት ተክለአብ ይባላሉ። በእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የአራዳ ቅርንጫፍ አደጋ ምላሽ ቡድን መሪ ናቸው። በተቋሙ ለ18 ዓመታት አገልግለዋል። በእነዚህ ጊዜያት ታዲያ መስቀልን ጨምሮ የተለያዩ በዓላትን በስራ አሳልፈዋል። የዛሬውን የመስቀል ደመራ በዓል በዚሁ መንገድ ለማክበር መዘጋጀታቸውን ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡

በዓልን ከቤተሰብ ተነጥሎ በስራ ገበታ ማሳለፍ ያለውን ስሜት፣ “በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ትንሽ ከብዶኝ ነበር። የሴትነትና የእናትነት ኃላፊነቴን ለሚጠብቁ ቤተሰቦቼ በዕለቱ ተገኝቶ ያንን ማድረግ አለመቻል እንደ ግለሰብ የሚፈጥረው ስሜት አለ። በሂደት ግን እየተላመድኩት መጣሁ፡፡ በተለይ ደግሞ በነፍስ አድን ተልዕኮ ውስጥ ማሳለፌ የእያንዳንዷን ደቂቃ ትርጉም በደንብ እንድረዳ አድርጎኛል። ከዚህ በተጨማሪ ለሌሎች ደስታ አለኝታ መሆን ልዩ ስሜት የሚሰጥ ነው” ሲሉ ገልጸውታል።

“‘ባለቤቴ በበዓል ሴት የሌለችበት ቤት አይደምቅም’ የሚለውን የተለመደ አስተሳሰብ ሰብሮ ልጆቻችንን ሲንከባከብ ነው የሚውል፡፡” የሚሉት ወይዘሮ ትዕግስት፣ የከተማዋን ነዋሪ ለመታደግ የአደጋ ሳይረን ወደሚጮህበት አቅጣጫ ሮጦ በመሄድ በጭስ የታፈኑ፣ በጎርፍ የተከበቡ ነፍሶችን ከሞት አፋፍ ነጥቆ ማውጣት መቻል ለእሳቸው ከየትኛውም የበዓል ድግስ የሚበልጥ የአእምሮ እርካታ መሆኑን አብራርተዋል።

ምንም እንኳን ወይዘሮ ትዕግስት በመስቀል ደመራ ዋዜማ ከቤተሰብ ጋር ባያሳልፉም የእሳቸው እና መሰሎቻቸው ይህ መሰል ተግባር የበርካቶችን ደህንነት እና ጤና ይጠብቃል። የራሳቸውን የደስታ ጊዜ አሳልፈው በመስጠት የሌሎችን ህይወት ማትረፍ የህሊና ሰላም እና ወደር የሌለው ደስታ የሚሰጥ መሆኑን አብራርተዋል።




ፎቶ፦ በገነት ወንድሙ
በእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የአራዳ ቅርንጫፍ አደጋ ምላሽ ቡድን መሪ ትዕግስት ተክለአብ የስራ ስምሪት ላይ

## አይረሴ ገጠመኞች

ወይዘሮ ትዕግስት በ18 ዓመታት የአገልግሎት ዘመናቸው ካስተናገዷቸው እና በልባቸው ውስጥ ለዘላለም ተቀርጸው ከቀሩት የተለያዩ አጋጣሚዎች መካከል ከበዓል ጋር የተገናኙትን አጋርተውናል።

በአንድ የመስቀል ደመራ በዓል ዕለት ነዋሪነታቸው በተለምዶ ዮሐንስ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በተለኮሰ ችቦ ምክንያት ሁለት ረዳት የሌላቸው አቅመ ደካማ አዛውንቶች በመኝታ ቤታቸው ውስጥ እያሉ ድንገተኛ እሳት ተነሳ፡፡ በዚህም ቤታቸው በጭስ ታፈነ በእሳትም ተከበበ፡፡ በዚህ ጊዜ ወይዘሮ ትዕግስት ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ህይወታቸውን አደጋ ላይ ጥለው ዘልቀው በመግባት ሁለቱንም አቅፈው ወደ ውጭ ማውጣትና ከመቃጠል ማዳን ችለዋል፡፡

ከበዓሉ ጋር በተገናኘ ያጋጠማቸውን ሌላኛውን አጋጣሚም በሀዘን ስሜት ሆነው እንደሚከተለው አጋርተውናል፡፡ በወቅቱ የአሁኑ የኮሪደር ልማት ሰባ ደረጃን እንደዛሬው አልቀየረውም ነበር፡፡ አንድ ግለሰብ በዓሉን አክብሮ በስካር መንፈስ መኪናውን ሲያሽከረክር አደጋ ደረሰና የሰዎች ህይወት ተቀጠፈ፡፡

## ቴክኖሎጂን የታጠቀው የነፍስ አድን ጉዞ

እንደ ወይዘሮ ትዕግስት ገለጻ፤ ከዓመታት በፊት ከነበረው አሰራር በተለየ ተቋሙ አሁን ላይ ለእያንዳንዱ ሰዓት፣ ደቂቃና ሴኮንድ ዋጋ ከመስጠት ጀምሮ አቅሙን አሳድጓል። አደጋ የደረሰበት የህብረተሰብ ክፍል በስልክ ጥሪ ሲያደርግ ማዕከሉ በጂፒኤስ እና በዘመናዊ ካሜራዎች የታገዘ የቅርብ ክትትል በማድረግ ትክክለኛውን ቦታ በፍጥነት ይለያል። ይህም እንደነ ትዕግስት ላሉ የአደጋ ምላሽ ሰጪዎች በደቂቃዎች ውስጥ ቦታው ደርሰው የከፋ ጉዳት ሳይደርስ ሁኔታውን በቁጥጥር ስር ለማዋል አስችሏቸዋል።

በመጨረሻም ወይዘሮ ትዕግስት በዓላት የደስታ እንጂ የሀዘን እንዳይሆኑ ለመላው ህብረተሰብ ጥብቅ የጥንቃቄ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ እያንዳንዱ የመስቀል ደመራን የሚያከብር ግለሰብ ከችቦ ጋር ተያይዞ የሚመጡ አደጋዎችን መከላከል አለበት። በችቦ ወይም በደመራ ላይ ተቀጣጣይ ፈሳሾችን ወይም የመፈንዳት ባህሪ ያላቸውን ነገሮች በመጨመር የሚደረጉ አደገኛ ድርጊቶች ማቆም ይኖርባቸዋል። መጠጥ ጠጥቶ ማሽከርከር የራስንም ሆነ የንጹሃንን ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ ይህንን እኩይ ተግባር ፍጹም ማስወገድ ይገባል። መንገድ ላይ መኪናዎችን በዘፈቀደ ማቆም በተለይም ደግሞ አቁሞ ማሳደር የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች በፍጥነት እንዳይደርሱ እንቅፋት ስለሚሆን ከዚህ መቆጠብ ተገቢ ነው። “እኛ አደጋ ወደተከሰበት ቦታ በምንሄድበት ወቅት የምንቆምበት እያንዳንዱ ደቂቃ የሌላውን ሰው ህይወት ይቀማል” የሚሉት ወይዘሮ ትዕግስት ይህንን ሁሉም ተገንዝቦና ራስን፣ ማህበረሰብን አልፎ ተርፎም ሀገርን ከጉዳት ማዳን ይገባል” ብለዋል።

የከተማዋ ነዋሪዎች በዓላትን በቤታቸው በሰላም፣ በደስታና በድምቀት እንዲያከብሩ አለኝታ የሆኑት እንደ ወይዘሮ ትዕግስት ያሉ ጀግኖች ያልተቋረጠ ትጋትና መስዋዕትነት ይከፍላሉ። እነዚህ ‘ቤተሰቤ፤ በዓል’ ሳይሉ ህዝብን የሚያገለግሉ ሰዎች የከተማዋ ህያው መከታዎች በመሆናቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

# ማስታወቂያ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦ/አያ/08/1932/01 ሴሪ ቁጥር 005043 እንድሪስ መሀመድ አህመድ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የኮንዶሚንየም ቤት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸው ተደራጅቶ በመመሪያው መሠረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ**
**መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 25 ቀበሌ 16 በአዲሱ አደረጃጀት ወረዳ 14 የሚገኝ ቤት በካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/166/14536/00 በሴሪ ቁጥር 036238 በአቶ ሙባረክ አብራር ስም የይዞታ/የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ካርታው በመጥፋቱ ምክንያት የካርታ ኮፒ አገልግሎት የተጠየቀ ሲሆን አገልግሎቱን ለመስጠት በይዞታ አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 163/2016 መሰረት የባለይዞታው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ መጥፋቱ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ማስታወቂያ ወጥቶ በ20(ሃያ ቀን) ቀን ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ አገልግሎቱን መስጠት እንደሚቻል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ካርታውን ይዤዋለሁ የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ20 (ሃያ ቀን) ቀን ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ይዞ እንዲቀርብ እያሳስብን ይህ ካልሆነ ግን በመመሪያው መሰረት የጠፋውን ካርታ አምክነን በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ**
**መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በአቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ሀዳስ ዮሃንስ ገብረእግዚአብሔር ስም የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000080112304 የሴሪ ቁጥሩ 0229358 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ተለዋጭ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና**
**መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ወ/ሮ/ወ/ሪት/አቶ/እነ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 08 ክልል ውስጥ በግርማይ ተ/ሃይማኖት ማሐረካ በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070108789 በሴሪ ቁጥር L-0125862 የተመዘገበው የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ**
**ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 04 ክልል ውስጥ በአቶ መሀመድ ሰይድ ይመር ስም በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070404750 ሴሪ ቁጥር 019294 በሆነ የተመዘገበው ይዞታ፤ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ /የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን 11/01/2019 ዓ.ም ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ**
**ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አመልካች ስዩም አብዛ በርሄ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 08 በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070804619 በሴሪ ቁጥር L-0191646 በ ስዩም አብዛ በርሄ ስም የተመዘገበ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ**
**ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

## እንኳን ለ2019 ዓ.ም የመስቀል በዓል አደረሳችሁ!

**የድርጅታችን ተሸላሚዎች እንኳን ደስ ያላችሁ!**

ግራንድ አፍሪካን የተቋማትና የአመራር ሽልማት ድርጅት ህጋዊ ፈቃድ ኖሮት በሀገራችን በአምራችነትም ሆነ በአገልግሎት ሰጪነት የሰሩ ተቋማት ለሀገር እና ለህዝብ ለሰሩት ስራ ምስጋና፣ ሽልማትና እውቅና በመስጠት የላቀ ስራ በመስራት እንዲዘልቁ ለማድረግ የተቋቋመ ብቸኛ የሽልማት ድርጅት ነው። ድርጅታችን ላለፉት 32 ዓመታት በነበሩት ሽልማቶች የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ኦሮሚያ ባንክ፣ የካቲት12 ሆስፒታል፣አባሃዋ ትሬዲንግ፣ የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን፣ የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን፣ ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ፣ አድማስ ዩኒቨርስቲ፣ ሀሌሉያ ሆስፒታል፣ አዲስ የመድሃኒት ፋብሪካ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ አሰር ኮንስትራክሽን፣ ስቲሊአርኤም ብረታ ብረት፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ፣ ሙገር ሲሚንቶ፣ ቀርጫንሺ ግሩፕ፣ ሌሶ ኢትዮጵያ፣ ኤስሳራ ቡና ላኪ፣ ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ፣ አሚን ሆስፒታል፣ ዘመን ኢንሹራንስ፣ ታደሰ ደስታ አስመጪና ላኪ፣ ሮያል ፎም፣ ቲኬ ግሩፕ ማኑፋክቸሪንግ ኤንድ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ ኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የፓወር ኢክፕመንት ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ አስመን ኃ/የተ/የግ/ማ፣ የክርስቲያን በጎ አድራጎት እና ልማት ማኅበራት ህብረት፣ የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን፣ ኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን፣ ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል፣ ኢንዲያና ት/ቤት፣ የኦሮምያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል እና ኪነ-ጥበብ ቢሮ፣ ኦሮሚያ ግብርና ቢሮ፣ የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት፣ የኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ፣ፋና ሚዲያ ኮርፖሬሽን አ.ማ፣ የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማህበር፣ ኢፌድሪ የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር፣ ጸሜክስ ግሎባል ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ ኢፌድሪ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት፣ ቀስተ ደመና ፕላስቲክ ኢንደስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት፣ ቤዛ ፓስቴሪቲ የልማት ድርጅት እና ሌሎችም ተሸልመዋል።

የ2018 ዓ.ም ማጠናቀቂያም ዜና የተሰራላቸው የግራንድ አፍሪካን የተቋማትና አመራር ሽልማት ድርጅት ተሸላሚዎች ጥቅምት 1 ቀን 2019 ዓ.ም ይሸለማሉ። በተጨማሪም የእህት ኮባንያችን የወርልድ ክላስ የጥራት ሽልማት ድርጅት ተሸላሚዎች ጥቅምት 8 ቀን 2019 ዓ.ም ይሸለማሉ። ሌላው የሽልማት ድርጅታችን እህት ኩባንያ አቢሲኒያ የከፍተኛ ክብር የሎሬት ሽልማት ድርጅት በልዩ ድምቀት ህዳር 6 ቀን ግለሰብ ሎሬቶችን ይሸልማል።




መልካም የመስቀል ደመራ በዓል ይሁንላችሁ!
ግራንድ አፍሪካን የተቋማትና የአመራር ሽልማት ድርጅት!

**ለተጨማሪ መረጃ**
**+251911 – 24 83 68 / +251911 – 24 23 88 ይደውሉ።**



በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የይዞታ መለያ ቁጥር ሴሪ ቁጥር C 252949 ይዞታ መለያ ቁጥር AA000060502540050705 ኪሩቤል ዋለልኝ ከበደ ስም በተቋማችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን እስከ 30 ቀን ድረስ በጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ /ሰርተፊኬት/ እንደምሰጣቸው እናሳስባለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት አስተዳደር ቢሮ ቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ፀጋይ ታፈረ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ካርታ ቁጥር ቦሌ17/108/67-2834/00 ሴሪ ቁጥር 007171 የሆነ ኦርጂናል /ዋናው/ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው 30 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት የይዞታ አገልግሎትና ማስተካከል ዳይሬክቶሬት ካልቀረበ በምትኩ ሌላ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት አስተዳደር ቢሮ ቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች እነ ዘላለም ንጉሴ ደሜ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 02 በካርታ ቁጥር 044237 በሴሪ ቁጥር 0130023 በእነ ዘላለም ንጉሴ ደሜ ስም የተመዘገበ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑና እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ --------- ቀበሌ ------- በአዲሱ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር ------------ በካርታ ቁጥር 07/104/4096/65238/01 በአቶ/ወ/ሮ/እነ የመካኒሳ ጎፋ ሳሪስ የአትክልት አምራች የህ/ስ/ማ ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመቅረብ አቤቱታ እንዲቀርብ። ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን።

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ አዲስአለም አሰፋ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ካርታ ቁጥር ቦሌ01/43/1/3/2693/13302/02 ሴሪ ቁጥር 0115226 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤት ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 05 የካርታ ቁጥሩ w5/03-3-133-480-9081/00 ሴሪ ቁጥር 041411 የሆነው በወ/ሮ ደመቀች ወልደማርያም ጋዬ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 11/1/2019 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**




### የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በአቶ ይርጋ በላቸው ስም የተመዘገበ ይዞታ በካርታ ቁጥር የካ 101/178334/05 የተሰጠበት ቀን 09/07/05 ዓ/ም የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ/03/13/2018 ዓ.ም እንደጠፋባቸው የሚገልጽ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ በመሆኑ ካርታውን አግኝቼዋለሁ ወይም ሙብት አለኝ የሚል አካል ካለ በ90 ቀናት ውስጥ ከላይ በተጠቀሰው መስሪያ ቤት ማለትም በየካ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳወቅ ይህ ሳይሆን ቢቀር በምትኩ ለአመልካች ምትክ ሰርተፊኬት የምንሰጣቸው መሆኑን በማክበር እንጠይቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ እንዳሻው ሙላው ገበናው ስም የተመዘገበ የነባር ይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090506666 ሴሪ ቁጥር R 0123850 የጠፋባቸው መሆኑን በ07/01/2019 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ**
**ቀራኒዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ እመቤት አጋ ደበሌ ስም የተመዘገበ የኮንዶሚኒየም ይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA00009031199932031114 ሴሪ ቁጥር C 142326 የጠፋባቸው መሆኑን በ11/01/2019 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ**
**ቀራኒዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ወ/ሮ ብርቱካን ቱፋ የአቶ ቶማስ ዓብይ ህጋዊ ወኪል በቀን 02/13/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ክልል ውስጥ የካርታ ቁጥር ለ/ኩራ 10/4/1/4596/0032/2/00 ሴሪ 1621085 የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ይዞታ ኦርጂናል ካርታ የጠፉብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት**
**ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 07 ይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር ኮ/ቀ/7/01-19-222/234/22902/01 በአቶ ኸይሩ ሳቢር ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 02/13/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ**
**ቀራኒዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ዘካሪያስ የሱፍ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረደ 9 የቤት ቁጥር 181/1 በካርታ ቁጥር 9/96/378675/00 በስማቸው ተመዝግቦ በእጃቸው መገኘት የነበረበት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንን አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም ተቃዋሚ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎቱን የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር**
**ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# አዲስ አበባ በስፖርት ቱሪዝም ምዕራፍ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ስፖርት ከአካላዊ ብቃትና ከውድድርነት ባለፈ ድንበር ተሻጋሪ ሁለንተናዊ ቋንቋ ሲሆን፣ ቱሪዝም ደግሞ የሀገርን የተፈጥሮ ውበት፣ ታሪክና ባህል ለዓለም ማስተዋወቂያ አውድ ነው። የስፖርት ቱሪዝም በዓለም ላይ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣ የገቢ ምንጭ፣ የሀገር ገፅታ መገንቢያና የዲፕሎማሲ መሳሪያ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። የስፖርት ፌስቲቫሎችና ውድድሮች ማለትም እንደ ማራቶንና ኦሎምፒክ ጨዋታዎች ወይም የዓለም ዋንጫ አይነት ውድድሮች እንደዚሁ የአንድን ሀገር ወይም ከተማ መሠረተ ልማት፣ ባህል እና አጠቃላይ መስህብ በማጉላት ከተማን ከዓለም ጋር በማስተዋወቅ ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡

በተለያዩ የዓለም ከተሞች የሚከናወኑ ስፖርታዊ ውድድሮች ከጀርባቸው ያነገቡት ዓላማ ከስፖርታዊ ውድድር የሚሻገር ሲሆን በተለይም እነዚህ ከተሞች ያሏቸውን ገፀበረከቶች ለዓለም በማስተዋወቅ በዘላቂነት ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ መለያ ውድድር እውቅና የተሰጠው የዱባይ ማራቶን ውድድር ለዱባይ ዋና የቱሪዝም አሽከርካሪነት ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለውም በምሳሌነት ይጠቀሳል። ውድድሩ ዱባይን እንደ መሪ የቱሪስት እና የስፖርት ማዕከል በማስተዋወቅ ረገድ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወትና አትሌቲክስ አፍሪካ የተሰኘው ሚዲያም ባወጣው መረጃ በየዓመቱ በሺዎች የሚቆጠሩ አማተር ሯጮችን ይስባል ሲል ዘግቧል።

ስፖርት ቱሪዝም ማለት የስፖርት ውድድሮችን ለመመልከት ወይም በውድድሩ ላይ ለመሳተፍ ወደ አንድ የዝግጅት መዳረሻ መሄድ ነው፡፡ ይኸም በተለያዩ የስፖርታዊ ውድድሮች ላይ ለመሳተፍ ወይም ለመመልከት መሔድን ጨምሮ፣ የስፖርት ሙዚየሞችን፣ ስታዲየሞችና ሌሎች ልማቶችን መጎብኘትን ሁሉ ያጠቃልላል። በአላይድ የገበያ ጥናት (Allied Market Research) ሪፖርት መሰረት የዓለም ስፖርት ቱሪዝም ኢንዱስትሪ ከሶስት ዓመት በፊት በወጣ መረጃ 323 ነጥብ 42 ቢሊዮን ዶላር ደርሶ ነበር፡፡ በ2030 ደግሞ 1 ነጥብ 8 ትሪሊዮን ዶላር ይደርሳል ተብሎ ተገምቷል፡፡

"The Economic Effects of a Marathon as a Sport Tourism Event" ጥናታዊ ጽሑፍ ፀሐፊው ግሪጎሪ ፓፓኒኮስ በተለይም ባለፉት አሥርት ዓመታት እንደ ማራቶን ያሉ ስፖርታዊ ፌስቲቫሎች ብዙ ጎብኝዎችን ከመሳባቸው በተጨማሪ ሀገርን ማስተዋወቂያ መሳሪያ በመሆን ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው ይላሉ፡፡ ስፖርትና ቱሪዝም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ያህል ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ዘርፎች ናቸው የሚባለውም ለዚሁ ነው።







ፎቶ፦ ከገፀ ድር

አዲስ አበባ ለስፖርታዊ ማዘውተሪያ ስፍራዎች ግንባታ ትኩረት ሰጥታ በመስራቷ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስፖርታዊ ኩነቶችን የማዘጋጀት ዕድል አግኝታለች

ዛሬ ላይ ስፖርት ከመዝናኛነት ባለፈ መዳረሻዎችን በዓለም ካርታ ላይ የሚያስተዋውቅና የቱሪዝም መዳረሻዎችን ህያው የሚያደርግ ታላቅ ዲፕሎማሲያዊ መሳሪያ ሆኗል። አንድ ከተማ ዓለም አቀፍ ስፖርታዊ ሁነቶችን ማስተናገድ መቻሏ ከስፖርታዊ ድምቀት ባለፈ ብዙ ፋይዳ አለው። እንዲህ ያሉ መድረኮች የከተማዋን የመሠረተ-ልማት ግንባታ የሚያፋጥኑ፣ የቱሪስት ፍሰትን የሚጨምሩና የንግድ እንቅስቃሴን የሚያነቃቁ ሲሆኑ፣ ከተማዋን በዓለም መድረክ ተመራጭ መዳረሻ በማድረግ ረገድም ጉልህ ሚና ይጫወታሉ።

አዲስ አበባ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በተሰሩና እየተሰሩ ባሉ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ ፓርኮች፣ አደባባዮችና ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች መልኳ እየተቀየረ መጥቷል፡፡ መዲናዋ ይህንን ዕድል ለመጠቀም በከፍተኛ የለውጥና የዝግጅት እንቅስቃሴ ላይ ትገኛለች። በተለይም በከተማ ኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶች አማካኝነት መንገዶች ለሰውና ለተሽከርካሪ ምቹ እንዲሆኑ እየተደረገ ሲሆን፣ በዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም ዙሪያ ያሉ ዘመናዊና ሰፋፊ አደባባዮች መገንባታቸው ከተማዋ ለትልልቅ ህዝባዊና ስፖርታዊ ሁነቶች ያላትን ዝግጁነት ከፍ አድርጎታል። እንደዚሁም መዲናዋን በአፍሪካ ደረጃ ቀዳሚ የስፖርት ቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ እየተከናወነ ያለውን እንቅስቃሴ ያሳያሉ።

አዲስ አበባ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ታላላቅ ስፖርታዊ ውድድሮች እየተከናወኑባት ያለች መዲና ሆናለች። ለማሳያ ያህል ጥቂቶቹን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በየጊዜው ከሚያካሂዳቸው የማስ ስፖርት እንቅስቃሴ በተጨማሪ ከ14 ክለቦች የተውጣጡ 330 ተወዳዳሪዎች በሁለቱም ጾታ የተሳተፉበት ማራቶን ውድድር፣ የአዲስ አበባ ከተማ ብስክሌት ፌዴሬሽን ከኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ ሼር ካምፓኒ ጋር በመተባበር ያዘጋጁት የብስክሌት ውድድር እንደዚሁም ከቸርቸል ጎዳና እስከ ለገሀር በተሰራው የኮሪደር ልማት የተከናወነው ዓመታዊ የኮካ ኮላ የብስክሌት ውድድር ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በመዲናዋ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህብረተሰቡ በተለይም በወጣቱ ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነትን እያገኘ የመጣው የቅልቅል ማርሻል አርት (MMA) ውድድር የዚህ አዲስ የለውጥ ምዕራፍ ማሳያ ሆኗል።

የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አሰግደው ኃይለጊዮርጊስ እንደሚሉት የመዲናዋ ግዙፍ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ከተማዋን በአፍሪካ ተመራጭ የስፖርት መዳረሻ እያደረጋት ይገኛል። የስፖርቱ ዓለም ዓይን ያረፈባት በአዲስ አበባ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የዓለም አቀፍ ውድድሮች መገኛ እየሆነች መጥታለች፡፡ የግራንድ ፕሪ የጎዳና ላይ ሩጫ፣ የሼክ ዛይድ የበጎ አድራጎት ሩጫ፣ በአፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው የሲቲ ማውንቴን ባይክ (ተራራ ብስክሌት) ውድድር እና የምስራቅ አፍሪካ የእጅ ኳስ ውድድር በስኬት መጠናቀቃቸው ለዚህ ምስክር ናቸው። ይህም በስፖርት ቱሪዝም ዘርፍ አዲስ የዕድል በር ተከፍቶላታል።

በሌላ በኩል፣ የአዲስ አበባን የቱሪዝም ሳቢነት ከስፖርቱ ጋር አቆራኝተው የሚያዩ ከተማዋን የጎበኙ ሙያተኞች፣ ከተማዋ ያላት ዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ተሰሚነትና የአየር መንገዷ ግዙፍ ትስስር ለትልልቅ ውድድሮች ስኬት ዋስትና መሆኑን ያነሳሉ። አንድ ስፖርተኛ ወይም ቱሪስት አዲስ አበባ ሲመጣ የሚያገኘው የጸጥታ አስተማማኝነትና እያደገ የመጣው የሆቴሎች ጥራት፣ ከተማዋን ከስፖርት ማዘውተሪያነት ባለፈ የባህል መዳረሻ አድርጓታል ሲሉ ይመሰክራሉ።

በቅርቡ የተካሄዱት የ'ግራንድ ፕሪ' እና የ'ዛይድ የደግነት ሩጫ' ያስመዘገቡት የተመልካች ቁጥርና የሚዲያ ሽፋን፣ አዲስ አበባ የውድድር ድምቀት ብቻ ሳይሆን የንግድና የቱሪዝም ትርፍ የሚገኝባት 'አዲሷ የአፍሪካ የስፖርት መዲና' መሆኗን ለዓለም የስፖርት ማህበረሰብ በተግባር እያሳየች መሆኑን በሙያዊ ትንታኔያቸው ያስረዳሉ።

የወደፊት የቱሪዝም ዘርፉን ተስፋ ይበልጥ የሚያለመልሙት ደግሞ ግንባታቸው በመጠናቀቅ ላይ ያሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ናቸው። የአቃቂ ዓለም አቀፍ ስታዲየም ግንባታ ማጠናቀቂያ ደረጃ ላይ መድረሱ፣ እንዲሁም የታደሱት የአዲስ አበባ፣ የአደይ አበባ እና የአበበ ቢቂላ ስታዲየሞች ለአገልግሎት ዝግጁ መሆናቸው ተጠቅሷል። እነዚህ መሠረተ ልማቶች ኢትዮጵያ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ውድድሮችን የማስተናገድ አቅሟን በእጅጉ እንደሚያሳድጉላት ይታመናል። ዛሬ ላይ ራሷን ለዓለም እያሳየች ያለችው አዲስ አበባ በውበቷ፣ በንጽህናዋ እና በዘመናዊ መሠረተ ልማቶቿ የታጀበው የስፖርት እንቅስቃሴ፣ ከተማዋን በአፍሪካ ቀዳሚ የስፖርት መዳረሻ ለማድረግ በሚደረገው ጉዞ ላይ ትልቅ ምዕራፍ ከፍቷል።

አዲስ አበባ አሁን ላይ የጀመረችውን የስፖርት ቱሪዝም ግስጋሴ ስኬታማነት ለመረዳት፣ እንደ ባርሴሎና፣ ኬፕ ታውን፣ ኪጋሊ ያሉ ከተሞችን ተሞክሮ እንደ ማሳያ መመልከት ይቻላል። ባርሴሎና እ.ኤ.አ በ1992 የኦሊምፒክ ጨዋታዎችን ማስተናገዷ ከተማዋን ከነበረችበት ተራ የኢንዱስትሪ ማዕከልነት አውጥቶ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ እንድትሆን አስችሏታል።

የደቡብ አፍሪካዊቷ ኬፕ ታውን የተፈጥሮ ውበቷን ከዘመናዊ ስታዲየሞች ጋር በማዋሃድ የዓለምን ትኩረት መሳብ ችላለች፡፡ እንደ ኪጋሊ ሁሉ ንጽህናን እና የዲጂታል አሰራርን በማስቀደም፣ እንዲሁም እንደ ካይሮ ታሪካዊ እሴቶችን ከስፖርታዊ ሁነቶች ጋር በማቀናጀት ከተሞቻቸውን የስፖርት ቱሪዝም መዳረሻ ማድረግ ችለዋል።